አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

በአማራ ክልል የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ለአማራጭ መሠረታዊ እና ለመደበኛው ትምህርት መርሐግብር በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ንጽጽራዊ ጥናት

ብርሃኑ አራጋው

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ሰኔ 2000 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በአማራ ክልል የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ለአማራጭ መሠረታዊ እና ለመደበኛው ትምህርት መርሐግብር በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ንጽጽራዊ ጥናት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

ለአማርኛ ማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጽሑፍ

ብርሃኑ አራጋው

ሰኔ 2000 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

በአማራ ክልል የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ለአማራጭ መሠረታዊ እና ለመደበኛው ትምህርት መርሐግብር በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ንጽጽራዊ ጥናት

ብርሃኑ አራጋው

ቋንቋዎች ጥናት ተቋም



የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ	ፈርማ
ፈታኝ	ፈርማ
ፈታኝ	ፈርማ

ማውጫ

ርዕስ ገጽ

የሰንጠረዥ ማውጫ ..... ሀ

ምስጋና ..... ለ

አጠቃሎ ..... ሐ

ክፍል አንድ 1

መግቢያ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ 1

1.2. የጥናቱ ዓላማ 5

1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት 6

1.4. የጥናቱ ወሰን 6

ክፍል ሁለት 8

ክለሳ ድርሳን 8

2.1. የንግግር ምንነት 8

2.2. የንግግር ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት 10

2.3. የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አዘገጃጀት (በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ሲታይ) 15

2.3.1. የንግግር ክሂል ትምህርት የይዘት አመራረጥ 17

2.3.2. የንግግር ክሂል ትምህርት የይዘት አደረጃጀት 20

2.3.3. የንግግር ክሂል ትምህርት የይዘት አቀራረብ 22

ክፍል ሶስት 26

የአጠናን ዘዴ 26

3.1. የጥናቱ ዘዴ 26

3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች 26

3.3. የናሙና አወሳሰድ 27

3.4. የመረጃዎች አተናተን ዘዴ 27

ክፍል አራት 29

የጥናቱ ውጤት ትንተናና ንጽጽር 29

4.1. የደረጃ አንድ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ 29

4.1.1. የደረጃ አንድ መማሪያ መጽሐፍ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ ስለመቅረቡ 29

4.1.2. የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች በበቂ መጠን ተዘጋጅተው ስለመቅረባቸው 31

4.1.3. የትምህርት ይዘቶቹ ሳቢና ማራኪ ስለመሆናቸው 32

4.1.4. የይዘቶቹ አቀራረብ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያለው ስለመሆኑ 33

4.1.5. የአዘጋጆችና ተተኳሪ አመቻቾች የጽሑፍ መጠይቅ መልሶች 33

4.2. የደረጃ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ 34

4.2.1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ተመሥርቶ ስለመዘጋጀቱ 35

4.2.2. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በቂ የንግግር መለማመጃዎች ስለመዘጋጀታቸው 39

4.2.3. የንግግር ትምህርት ይዘቶች ሳቢና ማራኪ ስለመሆናቸው 40

4.2.4. ይዘቶቹ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያላቸው ስለመሆናቸው 41

4.2.5. የአዘጋጆችና የተተኳሪ አመቻቾች የጽሑፍ መጠይቅ መልሶች 41

4.3. የደረጃ ሦስት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ 42
4.3.1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ተመሥርቶ ስለመቅረቡ 43
4.3.2. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች በበቂ መጠን ስለመዘጋጀታቸው 48
4.3.3. የትምህርት ይዘቶቹን ሳቢነትና ማራኪነት በተመለከተ 50
4.3.4. የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶቹ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያላቸው ስለመሆናቸው 51
4.3.5. የጽሑፍ መጠይቅ መልሶች 51
4.4. የአንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ 52
4.4.1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ ስለመቅረቡ 52
4.4.2. የንግግር ክሂል ትምህርት መለማመጃ ይዘቶች በበቂ መጠን ስለመጋጀታቸው 54
4.4.3. የትምህርቱ ይዘቶች ሳቢነትና ማራኪነት ያላቸው ስለመሆናቸው 55
4.4.4. የይዘቶቹን ተከታታየነትና ተለጣጣቂነት በተመለከተ 56
4.4.5. ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መልሶች 56
4.5. የሁለተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ 57
4.5.1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀ ስለመሆኑ 57
4.5.2. የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ የሚያዳብሩ መልመጃዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በበቂ መጠን ስለመዘጋጀታቸው 60
4.5.3. የትምህርቱ ይዘቶች ሳቢነትና ማራኪነት ያላቸው ስለመሆናቸው 60
4.5.4. የትምህርቱ ይዘቶች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያላቸው ስለመሆናቸው 61
4.5.5. ከጽሑፍ መጠይቆች የተገኙ መልሶች 62
4.6. የ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ 63
4.6.1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመስርቶ ስለመዘጋጀቱ 63
4.6.2. የንግግር ክሂል ትምህርት መለማመጃ ይዘቶች በበቂ መጠነ ስለመዘጋጀታቸው 65
4.6.3. የትምህርቱ ይዘቶች ሳቢና ማራኪ ስለመሆናቸው 66
4.6.4. የትምህርቱ ይዘቶች ተከታታይነት ተለጣጣቂነት ያላቸው ስለመሆኑ 67
4.6.5. የጽሑፍ መጠይቆች መልስ 67
4.7. የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት አመራረጥ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ 68
4.7.1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀ ስለመሆኑ 68
4.7.2. የንግግር ክሂል መለማመጃዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በበቂ መጠን ስለመቅረባቸው 74
4.7.3. የትምህርቱ ይዘቶችን ሳቢነትና ማራኪነት በተመለከተ 75
4.7.4. የንግግር ክሂል የትምህርቱ ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተከታታይነትንና ተላጣጣቂነትን በተመለከተ 77
4.7.5. የጽሑፍ መጠይቆች መልስ 77
4.8. ከደረጃ 1-3 እና ከ1-4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ ተተኳሪ አመቻቾችና መምህራን ዳራ 78

4.9. በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ ሥር በሚገኙ ትምህርት ተቋማት የሚያገለግሉት /ከደረጃ 1-3/ እና /ከ1-4ኛ ክፍል/ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትን ያዘጋጁ ባለሙያዎች ዳራ 79
4.10. የመማሪያ መጻሕፍቱ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀት እና አቀራረብ በቃት በንጽጽር ሲተነተን 80
4.10.1. ደረጃ 1 ከ1ኛ እና 2ኛ ክፍሎች ጋር ሲነጻጸር 80
4.10.2. ደረጃ 2 ከ3ኛ ክፍል ጋር ሲነጻጸር 82
4.10.3. ደረጃ 3 ከ4ኛ ክፍል ጋር ሲነጻጸር 84
ክፍል አምስት 86
ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳብ 86
5.1. ማጠቃለያ 86
5.2. የመፍትሔ ሐሳብ 87
ዋቢ መጻሕፍት 91
አባሪዎች 95

የሠንጠረዥ ማውጫ

ገጽ

ሠንጠረዥ አንድ:- የንግግር ክሂልን ለማስተማር በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ ተዘጋጅተው የቀረቡ ይዘቶች 30

ሠንጠረዥ ሁለት በደረጃ 1 የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ክፍሎች መለማመጃ ጥያቄዎች መጠን 31

ሠንረጠዥ ሦስት:- ንግግርን ለማስተማር በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ ተዘጋጅተው የቀረቡ ይዘቶች 36

ሠንጠረዥ አራት:- በደረጃ 2 አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ክፍሎች /ክሂሎች/ መለማመጃ ጥያቄዎች..... 39

ሠንጠረዥ አምስት፣ በደረጃ 3 መርሐ ትምህርት ውስጥ ንግግርን ለማስተማር የተመረጡና ደራጅተው የቀረቡ ይዘቶች 43

ሠንጠረዥ ስድስት:- በደረጃ 3 አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ክፍሎች /ክሂሎች/ መለማመጃ ጥያቄዎች 49

ሠንጠረዥ ሰባት:- በአንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ የቀረቡ የንግግር ትምህርት ይዘቶች 53

ሠንጠረዥ ስምንት:- በአንደኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ክፍሎች መለማመጃ ጥያቄዎች..... 55

ሠንጠረዥ ዘጠኝ:- የንግግር ክሂል ይዘቶች መጠን በ2ኛ በክል መርህ ትምህርት 58

ሠንጠረዥ አስር:- በሁለተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ክፍሎች መለማመጃ ጥያቄዎች 60

ሠንረጠዥ አስራ አንድ:- በ3ኛ ክፍል መርሐ ትምህርት ውስጥ ለንግግር ክሂል ትምህርት የተመረጡ ይዘቶች 64

ሠንጠረዥ አስራ ሁለት:- በሦስተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ክፍሎች መለማመጃ ጥያቄዎች መግለጫ 66

ሠንጠረዥ አስራ ሶስት:- በ4ኛ ክፍል መርሐ ትምህርት ውስጥ የተጠቀሱ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች 69

ሠንጠረዥ አስራ አራት:- በሶስተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ክፍሎች መለመጃመጃ ጥያቄዎች.....75

ምሥጋና

ይህን ጥናት በምሠራበት ጊዜ ውጤቱ የተቃና እንዲሆን ባለመሠልቸት በማረምና በማስተካከል ለረዱኝ አማካሪዬ ለዶ/ር አረጋ ኃይለሚካኤል ከፍ ያለ ምሥጋና ሳቀርብ በታላቅ ትህትና ነው።

አሣድገው፣ አስተምረው ከዚህ ያደረሱኝ አባቴ አቶ አራጋው አበይ፣ እናቴ እማሆይ መልኪቱ ጠመረ፣ ወንድሞቼና እህቶቼ ባውለውለታዎቼ ስለሆኑ አመሰግናቸዋለሁ።

ባለቤቴ ወ/ሮ ወርቁ መሐመድ፣ ልጆቼ መዘክር፣ ኀሊና፣ ኢትዮጵያ፣ ኢዮኤል ከቤት በመራቁ ሳይከፉ ድጋፋቸው ስላልተለየኝ ሳመሰግናቸው ከልብ ነው።

ግምገማ ያካሄድሁባቸውን መማሪያ መጻሕፍትና መርሐ-ትምህርት በማዋስ የተባበሩኝን የደፊርጌ ኪቢቃሎ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያና የእቴጌ ጣይቱ ብጡል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተዳደር ሠራተኞችን፣ የጽሑፍ መጠይቆችን በመሙላት የተባበሩኝን የደሴና የደብረ ብርሃን መምህራን ትምህንርት ኮሌጅና የወሎ ዩኒቨርስቲ መምህራንን፣ በግዳን፣ በቆቦና በሀብሩ ወረዳዎች በማስተማር ላይ የሚገኙ ተተኳሪ አመቻቾችንና መምህራንን እንደዚሁም የእነዚህን ወረዳዎች ትምህርት ባለሙያዎች ከልብ አመሰግናለሁ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር ጥናቱን እንዲያካሂድ በጀት ስለፈቀደልኝ፣ የወልዲያ ከተማ አስተዳደርና ትምህርት ጽሕፈት ቤት ነፃ የትምህርት ዕድል ስለሰጠኝ ለሁሉም ምሥጋናዬ ይድረሳቸው።

ጽሑፌን ለተየበችልኝ ለወ/ሪት ዘውድነሽ አማረም ምሥጋናዬ ይድረሳት።

አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማራ ክልል በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው እርከን ለመደበኛውና ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መርሐ ግብሮች በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በቀረበው የንግግር ትምህርት ላይ የይዘት አመራረጥ አደረጃጀትና አቀራረብን በተመለከተ ንጽጽራዊ ግምገማ በማድረግ ደካማ ገፅታ ያለው እንዲሻሻልና ጠንካራ ገፅታ የታየበትም ይበልጥ ይጠናከር ዘንድ የመፍትሔ ሐሳብ ማቅረብ ነው:: ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ንጽጽራዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን በተለይም የዚሁ ዘዴ አንዱ አካል የሆነውን የመዛግብት ምርመራ ስልትን በዋናነት ተጠቀሟል:: ይህም ሲደረግ በመማሪያ መጻሕፍቱና በመርሐ ትምህርቶቹ ላይ ጥልቅ ንባብ በማድረግ የንግግር ክሂል ይዘቶቹን ከየመጻሕፈቱ ለቅሞ በማውጣትና በንዑሳን ክፍሎቹ መሠረት በየወገናቸው በመቦደን ትንተናው ተካሂዷል:: በቡደናው መሠረት ትንተና ሲደረግም ከአዘጋጆች ከአመቻቾችና ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት ከተገኘው መረጃ ጋር እየተመሳከረ የትንተና ውጤቱ ተገልጿል:: በዚህ ትንተና መሠረት የተገኘው ውጤትም ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መርሐ ግብር የተዘጋጁት መማሪያ መጻሕፈት ከይዘት አመራረጥ አዘገጃጀትና አቀራረብ አንጻር ከመደበኛዎቹ መማሪያ መጻሕፍት የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል::

ክፍል አንድ

መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ

የጥናቱ መነሻ የሆኑት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የተዘጋጁት የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ናቸው:: የእነዚህ መጻሕፍት ዝግጅታቸው ሁለት አይነት ነው:: አንደኛው ለአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው እርከን ለመደበኛው መርሐ ግብር (ከ1ኛ-4ኛ ክፍል) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህረት (Alternative Basic Education) መርሐ ግብር (ከደረጃ 1-3) መማሪያነት የተዘጋጀ ነው:: ለእነዚህ መርሐ- ግብሮች የተዘጋጁት መጻሕፍት ከ1ኛ-4ኛ የሚያገለግሉት በ1996 ዓ.ም፣ ከደረጃ 1-3 የሚያገለግሉት ደግሞ በ1998 ዓ.ም የታተሙ ናቸው::

በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መርሐ ግብር ለደረጃ አንድ የተዘጋጀው መጽሐፍ ለአንደኛና ለሁለተኛ ክፍል፣ ለደረጃ ሁለት የተዘጋጀው ለሶስተኛ ክፍል፣ ለደረጃ ሦስት የተዘጋጀው ደግሞ ለአራተኛ ክፍል ተመጣጣኝ እንዲሆኑ ታስቦ ነው:: የአማራጩ መርሐ ግብር በሶስት ዓመታት ውስጥ የሚጠናቀቅና ለተማሪው አመች በሆነ ጊዜ በቀን ከ3-4 ሰዓት የሚሰጥ ነው:: የመማሪያ ቀናቱም ከሰኞ እስከ ዓርብ የሚሰጠውን የመደበኛውን ትምህርት ቀናት የተከተለ ሳይሆን ለተማሪዎቹ አመቺ በሆኑ በሳምንት አምስት ቀናት ተመርጠው ነው:: ተማሪዎቹ የአዝመራ ወራትን በሥራ ማሳለፍ የሚፈልጉ ከሆነም ሁለቱን የክረምት ወራት ለትምህርት ጊዜያት ማድረግ እንደሚቻል የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ስትራቴጂ ይፈቅዳል (Amhara Riginal Education Bureau 2003:10-11)::

አማራጭ መሠረታዊ ትምህረት መርሐ ግብር ከመደበኛው መሠረታዊ ትምህርት መርሐ ግብር በተለየ መልክ እንዲዘጋጅ የተፈለገበት ምክንያት ታዳጊ /ደሀ/ ሀገሮች መሠረታዊ ትምህርትን ዕድሜያቸው ለትምህርት ለደረሱ ሕጻናት ሁሉ ለማዳረስ በመደበኛው መርሐ ግብር አቅማቸው ስለማይፈቅድ ነው (Wube 2003:76):: የመደበኛው መርሐ ግብር የተቋም ግንባታው በርካታ ገንዘብን፣ የመምህራን ሥልጠና ረዥም ጊዜን፣ ለመምህራን የሚከፈለው ገንዘብ አንጻራዊ በሆነ መልኩ ሲታይ ከፍ ያለ፣ የአርሶ አደሩን ልጆች የግብርና ሥራ ጊዜ በአብዛኛው የሚሻማ፣ ቋሚ የሆነ የትምህርት መስጫ ጊዜያትን የሚከተል፣ ወዘተ. በመሆኑ ትምህርትን ለሁሉም ሕጻናት ማዳረስ አይችሉም (አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ 1995፣5)::

ለሁሉም ሕጻናት ለማዳረስ በጣም ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን በአካባቢ ቁሳቁስ በመገንባት ከሃያ ቀናት ያልበለጠ ሥልጠና የወሰዱ አመቻቾችን (Facilitators) ከመደበኛ ገቢያቸው በተጨማሪ መጠነኛ የድጎማ ገንዘብ በመክፈል ሕጻናቱ ከግብርና ሥራቸው ሳይነጠሉ በሚመቻቸው ጊዜ (ማታ፣ ጠዋት ወይም ቀን) በሳምንቱ ቀናት ውስጥ እሑድና ቅዳሜን ጨምሮ እንዲማሩ ለማድረግ የተዘረጋ መርሐ ግብር ነው:: የትምህርት ወራትንም በተመለከተ ከአሉት አስራ ሁለት ወራት መካከል የተመቻቸውን መርጠው ከስምንት ወራት ያላነሰ ትምህርት እንዲያገኙ የሚያደርግ በአርሶ አደሩ አካባቢ የሚዘረጋ የትምህርት መርሐ ግብር ነው (አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ 1995:15፣ 1997: 3)::

የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያው፣ የትምህርት አመራሩና አስተዳደሩ ለአካባቢው ኅብረተሰብ ኃላፊነት የሚሰጥ ነው:: አመቻቾቹን መከታተል፣ ግቢውን ማጠርና መጠበቅ፣ የተማሪዎቹን የመማሪያ ወራት፣ ቀናትና ሰዓት መወሰን ሁሉ ለህብረተሰቡ የተሰጠ ኃላፊነት ነው (የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ 1995፣1-3 Knowles and Others 1998:198-199):: በሁለቱም መርሐ ግብሮች ያለፈ ተማሪ ቀጥሎ የሚጠብቀው ክፍል አምስት ነው::

በዚህ ጥናት ውስጥ ለማየት የሚሞከረው በእነዚህ በሁለቱ የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው እርከን የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻፍት የንግግር ክሂልን ለማዳበር ምን ያህል በብቃት ተዘጋጅተዋል ወይም ለንግግር ክሂል የተሰጠው ትኩረት ምን ያህል ነው የሚለውን መማሪያ መጻሕፍቱን በማነጻጸር ነው:: በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የንግግር ክሂል እንዲቀርብ የሚደረግበት ምክንያት ተማሪዎች ድምፆችን በትክክል ከመጥራት ጀምሮ የተወሳሰቡ (ጥልቀት የላቸው) ሐሳቦችን ቃላዊ በሆነ የመግባባት ሂደት ለመግለጽ እስከሚያስችል የደረሰ ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው (Echeverria 1987:5, Cunningsworth 1995:69):: የቋንቋው ተናጋሪ የሆነው ኅብረተሰብ የሚከተለውን የቋንቋ አጠቃቀም በመገንዘብ በክፍል ውስጥ እንዲለማመዱት በማድረግ ሥርዓቱን በጠበቀና በተሟላ መልኩ እንዲገለገሉበት ለማስቻል ነው::

የንጽጽሩ አስፈላጊነት የተማሪዎቹን የንግግር ክሂል ለማዳበር የተሻለ የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ የተከተለውን በመምረጥ ደካማ አዘገጃጀት ለሚከተለው ምጋቤ ምላሽ (Feedback) ለመስጠትና የተሻለውን አዘገጃጀት እንዲከተል ለማድረግ ነው:: በንጽጽሩ ጊዜ ለለቱም መርሐ ግብሮች የተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ የንግግር ክሂል የተሰጠው

ትኩረት ደካማ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ለንግግር ክሂል ትኩረት በመስጠት ዝግጅቱ እንዲስተካከል ሀሳብ ለመሰንዘር አጥኝው የሞክራል::

በሁለቱም መርሐ ግብሮች ተሳታፊ የሚሆኑት ሕጻናት (ተማሪዎች) የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር መሠረት መጣል የሚገባቸው በእነዚህ የክፍል ደረጃዎች ነው (Brown and Yule 1983:9):: ሕጻናቱ ሳይጨነቁ በጨዋታ መልክ ክሂሎችን እንዲያዳብሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: በሚና ጨዋታ፣ በቃለ ምልልስ፣ በክርክር፣ በውይይትና በቡድን ስራ መልክ ሊነጋገሩበት የሚገባውን ጉዳይ በማመልከት ወይም ወስኖ በመሰጠት ማሳተፍ ትምህርቱን እንዳይሰለች ያደርገዋል:: በተለይም የንግግር ክሂል የአፍልቆት ክሂል በመሆኑ የተማሪዎች ችሎታና የውስጥ ማንነት የሚገለፅበት በመሆኑ ለመማሪያ የሚዘጋጁት መጻሕፍት ለዚሁ ክሂል መዳበር ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል (Brown and Yule 1983:1):: ከዚህ አንጻር መማሪያ መጻሕፍቱ ለንግግር ክሂል ትምህርት አመቺ ሊሆኑ የሚችሉት ተማሪውን ያማከሉ ተግባራትን ማካተት ሲችሉ ነው:: ይህንን ለማድረግ ደግሞ በመማሪያ መጻሕፍቱ ዝግጅት ወቅት ለይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ጥንቃቄ ማድረግን ይጠይቃል:: ስለዚህ ሁሉንም ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) አኩል ትኩረት በመሰጠት የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ማሳደግ ያስፈልጋል:: ነገር ግን በተወሰኑ የክሂል ዘርፎች ላይ ትኩረት አድርጎ ሌሎችን በቂ ትኩረት አለመስጠት ወይም ከነጭራሹ መተው የቋንቋ ትምህርት አቀራረቡን ጎደሎ ያደርገዋል (Brown and Yule 1983:1)::

√ንግግር በቋንቋ አማካኝነት ሐሳብን በቃል መግለፅ እንደሆነ የመስኩ ባለሙያዎች አረጋግጠዋል (Widdowson 1977:48):: ሐሳብ በንግግር በሚገለጽበት ወቅት መታየት የሚገባቸውና ከንግግር ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጉዳዮች አሉ:: እነዚህም ሀሳብን በትክክለኛ የዐረፍተ ነገር አሰካክ መግለጽና የሚገለጸው ሐሳብ በንግግሩ ወቅት ከሚታየው አካላዊ እንቅስቃሴ ጋር የተደጋገፈና የተጣጣመ መሆን አለበት የሚሉት ናቸው (Widdowson 1977:59-60):: በቋንቋ አማካኝነት ሐሳቡን በንግግር የሚገልጸው ሰው የሚያሳየው አካላዊ እንቅስቃሴና (የእጅ እንቅስቃሴ በፊት ላይ የሚታዩ ገጽታዎች) የንግግሩ ፍሬ ሐሳብ የሚያተኩርበት ጉዳይ የሚናበቡ መሆን ይኖርባቸዋል:: ስለዓላማ ንግግር ወይም ገለፃ የሚያደርግ ሰው የማንቀላፋትን ሁኔታ የሚያሳላይ ከሆነ ሐሳቡን በትክክል ለማስተላለፍ ይቸገራል (ተክለማርያም 1965 182-183)::

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ንግግር በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ተሳታፊዎች አማካኝነት የሚከናወን ነው (Ur 1996):: ተሳታፊዎች በየተራ በሚነጋገሩበት ወቅት በመካከላቸው የሚፈጠር የሐሳብ መዛነፍ (Misunderstanding) በዚያው ሂደት ውስጥ ወደተስተካከለውና ወደሚያግባባው ሁኔታ እንዲመለስ ይደረጋል:: ንግግር ስህተትን ለማረምም ሆነ ሐሳብን በተለያዩ መንገዶች ግልጽ ለማድረግ የሚያስችል እድልን ይፈጥራል (በድሉ 1996 57 ተክለማርያም 1965 180 widdowson 1977:64)::

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎችንም ማህበራዊ መስተጋብሮችን ሊፈጥር የሚችለው የንግግር ክሂል በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በውል በተደራጁና በተዘጋጁ ይዘቶች ትኩረት ተሰጥቶበት ሊቀርብ ይገባል:: ተማሪዎች በጓደኞቻቸው ወይም በሌሎች ሰዎች ፊት ቀርበው ሳይፈሩና ሳይሸማቀቁ ሀሳባቸውን መግለፅ በሚያስችል መልኩ ንግግርን መለማመድ በቋንቋ ትምህርት አማካኝነት መማር ይኖርባቸዋል (Widdowson 1977:60-61 ተክለማርያም 1965 186)::

Cunningsworth (1995:70) እንደሚገልጹት አንድ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ የንግግር ቋንቋን ለማስተማር ምን ያህል ትኩረተ ተሰጥቷል? ለንግግር ትምህርቱ ምን አይነት ምቹ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል? ማለትም በቃል ዘገባን ለማቅረብ የሚያበረታቱ ንግግርን እንዲያደርጉ የሚጋብዙ ይዘቶች ተመርጠዋል? በምልልስ በጨዋታና በክርክር የንግግር ክሂላቸውን ከፍ የሚያደርጉበት ዝግጅት ተካቶላቸዋል? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ መገኘት አለበት:: ከዚህም በተጨማሪ ንግግርን የሚበረታቱ መሣሪያዎች በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ መጠቀስ ያለባቸው መሆኑን አበክረው ያስገነዝባሉ::

- Celce-Murcia (1991:8) ሲገልጹ ደግሞ የንግግርን ክሂል ማስተማር ያለብን ከሌሎቹ ክሂሎች በመነጠል ሳይሆን ሁሉንም እኩል ትኩረት በመስጠትና በተቀናጀ መልክ በየደረጃው እያሳደጉ በመሄድ ነው ይላሉ:: አክለውም ሲያብራሩ ለተወሰኑ ክሂሎች ብቻ ትኩረት ሰጥቶ በተለይ የቋንቋ ትምህርት ጽሕፈትና ንባብ ለሚመስላቸው ሌሎቹን እንደንግግርና ማዳመጥ ያሉትን የክሂል ዘርፎች ችላ ማለት ተገቢ አይደለም ይላሉ::

ይህንንም ጥናት ያነሳሳው ምክንያት በመማሪያ መጻሕፍቱ (በአማራጩና በመደበኛው) የቀረቡት ይዘቶች ምን ያህል የንግግር ክሂልን ለማዳበር ብቃት አላቸው የሚለውን በንጽጽር ለማየት ነው:: ለእነዚህ ደረጃዎች በተዘጋጁት በመማሪያ መጻሕፍቱም ሆነ በመርሐ ትምህርቶቹ ላይ እንደተጠቀሰው የቋንቋ ትምህርቱ ዓላማ ተማሪዎቹን ያለምንም ፍረሐትና ሐፍረት ሐሳባቸውን መግለጽ እንዲችሉ ማብቃት ነው (አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ 1996::)

ከዚህ ዓላማ አንጻር በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ያሉት ይዘቶች ሲመረጡና ሲደራጁ የንግግር ክሂልን ለማስተማር ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች እኩል ትኩረተ ተሰጥቷል ወይ የሚለውንና ተመሳሳይ ጥያቄዎች በንጽጽር መመርመርና የተሻለውን ለይቶ ማውጣት ዋና የጥናቱ ትኩረት ነው:: ከሚገኘው ውጤት (ምላሽ) በመነሳት ለንግግር ክሂል ትምህርት ትኩረተ ያልሰጡት የተሻለ ትኩረት ከሰጡት ልምድ እንዲያገኙና ዝግጅታቸውን ተመልሰው እንዲያዩ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል::

የንግግር ክሂልን በተመለከተ እስካሁን ድረስ የተደረገው ጥናት አንድ ብቻ ነው:: በመንግሥቱ ታደሰ (1997) በአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር በ9ኛ ክፍል ላይ የሚያተኩር ሲሆን ይሄኛው ጥናት ግን የመማሪያ መጻሕፍቱን አቀራረብ በንጽጽር በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው እርከን የመደበኛውና የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን የሚቃኝ ነው::

1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ በአማራ ብሄራዊ ክልል በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው እርከን ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርትና (Alternative Basic Education) ለመደበኛው ትምህርት መርሐ ግብር በተዘጋጁ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ በንጽጽር በማጥናት የትኛው መማሪያ መጽሐፍ ጠንካራ ጎን፣ የትኛው ደግሞ ደካማ ጎን እንዳለው በመለየት ደካማ ጎኖቹ የሚስተካከሉበትን ለመጠቆም ነው::

ይህንን ዐቢይ ዓላማ መሰረት አድርጎ የተነሳው ይህ ጥናት የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎችም አሉት

- የንግግር ክሂል ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ማለትም ከማዳመጥ ከማንበብና ከመፃፍ ክሂሎች ጋር እኩል ትኩረት ተሰጥቶት በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ እንዴት እንደተዘጋጁ መቃኘት፤
- በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የንግግር ክሂልን ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች አመራረጣቸው፣ አደረጃጀታቸውና አቀራረባቸው ከተማሪዎቹ ፍላጎት፣ ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ባህል፣ እምነት፣ ወዘተ. አንጻር ተቃኝተው ቀርበዋል ወይስ አልቀረቡም? የሚለውን በመተንተን ታይቷል::

እነዚህን ዓላማዎች መሠረት በማድረግ ተማሪዎች የንግግር ክሂላቸው ሊያዳብሩ የሚችሉባቸው የንግግር መለማመጃዎች በአግባቡ ተሰናድተው በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ መካተታቸውን በዚህ ጥናት ለማረጋገጥና ለመፈተሽ ተሞክሯል::

ከዓላማው ጋር በተያያዘም በሁሉም መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የንግግር ክሂል አጠቃላይ አዘገጃጀት ምን ይመስላል? የሚለው ዓቢይ ጥያቄ መልስ እንዲያገኝ ተደርጓል::

1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት

የጥናቱን አስፈላጊነት ሲነሳ ይህ ጥናት ከተጠናቀቀ በኋላ በዚህ ጥናት ተጠቃሚ የሚሆኑ ክፍሎች እነማን ይሆናሉ? ለምን አገልግሎት ሊውል ይችላል? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ የተሰጠበት ነው:: በዚህ መሠረት ይህ ጥናተ ለሚከተሉት ክፍሎች ጠቀሜታ ይሆረዋል ብሎ አጥኝው ያሰባል::

1. የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮና በዚያው ክልል ውስጥ የሚገኙ የትምህረት ተቋማት ተጠቃሚ ይሆናሉ:: ግልጋሎት እየሰጡ የሚገኙት በክልሉ ውስጥ በሚገኙ አንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው እረከን ትምህርት ተቋማት ነው:: በእነዚህ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ ተማሪዎች (የአማራጨም የመደበኛውም) እንዲማሩባቸው ተደርገዋል:: ስለዚህ እነዚህ ክፍሎች ተጠቃሚ ይሆናሉ::
2. የንግግር ክሂልንም ሆነ ሌሎችን ክሂሎች አቀናጅቶ ለማጥናት ለሚፈልግ ተመራማሪ ይህንን ጥናት የመነሻ ሀሳብ ሊያቀርብ ይችላል::

እነዚህ አጠቃላይ የሆኑ የጥናቱ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ፤ በክልሉ ውስጥ በየትምህርት እርከን የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎች (ከ1-4ኛ እና ከደረጃ 1-3) እና የትምህርት ባለሙያዎች ተጠቃሚዎች ይሆናሉ::

1.4. የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ መነሻ የሆኑት መጻሕፍት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የተዘጋጁት የአንደኛ ደረጃ መጀመሪያው እርከን የመደበኛውና የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ናቸው:: የሚገመገሙት መጻሕፍት በመማሪያነት ከሚያገለግሉባቸው ዞኖችና ወረዳዎች ውስጥ በሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙ ሶስት ወረዳዎች ላይ ብቻ ትኩረት ይደረጋል::

የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍቱ ንጽጽራዊ ጥናት ሲደረግ የንግግር ክሂልን ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ይፈተሻል:: የንግግር ክሂል አፈላቂ ክሂል በመሆኑ ከእሱ ጋር የአፈላቂ ክሂል ሆኖ የሚመደበው የጽሕፈት ክሂልም ሆነ

ማዳመጥና ማንበብ በመፃህፍቱ ውስጥ ያላቸው የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ በዚህ ጥናት ውስጥ አይታዩም:: የመማሪያ መጻሕፍቱ የንግግር ክሂልን ለማስተማር ያላቸውን የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ሲፈተሽ የመምህራን የአመቻቾችና የአዘጋጆች አስተያየት የጽሑፍ መጠይቆች ተሰብስቧል በተጨማሪም መርሐ ትምህርቶቹ ከመማሪያ መጻሕፍቱ ጋር መጣጣማቸውን ለመፈተሽ ይሞክራል:: ይህ ሲደረግ የማስተማሪያ መጻሕፈት /የመምህሩ መምሪያ በዚህ ጥናት አይታይም::

ክፍል ሁለት

ክለሳ ድርሳን

2.1. የንግግር ምንነት

ንግግር አንድ ቋንቋ ቃላዊ (aural) በሆነ መንገድ ለተግባቦታዊ አገልግሎት የሚውልበት የቋንቋ ክሂል አይነት ነው (Widdowson 1992:58):: ንግግር በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚከናወን የሁለተዮሽ ሂደት ነው:: ንግግር ከማዳመጥ ተነጥሎ ተግባራዊ ሊሆነ የማይችል ሐሳብን፣ አመለካከትን፣ ምኞትን፣ ፍላጎትን፣ ወዘተ. ለመግለጽ የሚያገለግል ቃላዊ የቋንቋ መግባቢያ ነው:: በንግግር ችግር ይቀላል፣ ጓደኝነት ይመሠረታል፣ ጥላቻ የፈጠራል፣ ማህበራዊ ግንኙነት ይጠባል ወይም ይሰፋል (Mc-Donought and Shaw 1994 152-153):: ከማቀበያ ክሂሎች (Productive Skill) አንዱ አካል የሆነው የንግግር ችሎታ ይዳብር ዘንድመቀበያ ክሂል (Receptive Skill) መዳበር አለበት:: የሁለቱም ክሂሎች መዳበር በተናጠል የሚከናወን ሳይነሆን አንዱ ከሌላው ጋር አብሮ ነው:: ንግግር በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚካሄድ በመሆኑ ቃላዊ ተግባቦቱ በትክክል እንዲካሄድ የሁለቱም ክሂሎች መዳበር ተቀራራቢ ሊሆን ይገባል (በድሉ 1996 57)::

Widdowson (1992፣60) ንግግር ሲባል ብዙ ጊዜ የሚታሰበው ገጽ ለገጽ በመቀራረብ ወይም በተለያዩ ቦታዎች ሆኖ ንግግርን ማስተላለፍ በሚያስችሉ መሳሪያዎችን በመጠቀም ቃላዊ የሀሳብ ልውውጥ የሚከናወንበት ነው በማለት የንግግርን ምንነት ከአብራሩ በኋላ ንግግር ወደ አድማጭ ሲደርስ ምስል ፈጥሮ መልዕክትን ማስተላለፍ እንዲችል ቃላዊ ከሆነው መግባቢያ በተጨማሪ በሌሎችም መንገዶች ሀሳብ እንዲጎላ ማድረግ ይቻላል ይላሉ:: እነዚህ የሐሳብ ማጉያዎች በተናጋሪው የፊት ገጽታ ላይ የሚታዩ ሁኔታዎች፣ የእጅና የተለያዩ የአካል ክፍሎች እንቅስቃሴዎች መሆናቸውን ያስረዳሉ::

Echeverria (1987፣ 6-7) የተባሉ ጸሐፊ ደግሞ የንግግርን ምንነት በሚከተለው መልኩ ገልፀውታል

> *ንግግር በሰው ልጆች የመግባባት ሂደት ውስጥ ቁልፍ የሆነ ክሂል ነው:: ንግግር ሀሳብን ወይም መልእክትን ወደተቀባይ ዘንድ ለማድረስ ከጽሁፍ የላቀ ጎልቶ ያለው የክሂል አይነት ነው:: ምክንያቱም ብዙው ሰው በየቋንቋው በንግግር መግባባት የሚችል ሲሆን ጽሑፍን ተጠቅሞ መግባባት የሚችለው ግን አናሳ ቁጥር ያለው ነው::*

ንግግር ሁለትና ከዚያም በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚከናወን ተግባቦታዊ ሂደት ነው:: በንግግሩ ሂደት ተናጋሪና አድማጭ ይሳተፋሉ:: ክንዋኔው የሚካሄደው በየተራና ሚና በመለዋወጥ ነው:: ተናጋሪ የነበረው አድማጭ፣ አድማጭ የነበረው ደግሞ ተናጋሪ የሆናል:: ንግግር እውቀትን፣ ፍላጎትን፣ አመለካከትን፣ ግንዛቤን፣ ስሜትን፣ ወዘተ. ለሌላ ሰው መግለጫ ክሂል ነው:: ይህ ሁኔታ በንግግር ሲከናወን በንግግሩ ውስጥ አምስት ክፍሎች (components) ተጠቃለው ይገኛሉ:: እነሱም መልዕክቱን አፍላቂ (source) የሚተላለፈው መልዕክት (message) መልዕክቱ የሚተላለፈበት መንገድ (channel) (ገጽ ለገጽ በመነገናኘት በስልክ በቴሌቪዥን ወዘተ.) ሊሆን ይችላል ማስተላለፊያው (medium) (በድምፅ ሞገድ በብረሃን ሞገድ) እና መልዕክት ተቀባይ (receiver) ናቸው (Echeverria 1987 6-7)::

አክለው Echeverria *1987:8)* ከእነዚህ ክፍሎች አንዱ በሌለበት ሁኔታ ንግግር ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችልና ንግግርን ተግባራዊ ለማድረግ እንኳ ቢሞክር ትርጉም የሌለውና ርባና ቢስ እንደሚሆን ይገልፃሉ:: ለምሳሌ ተናጋሪው በሌለበት ንግግርን ለማቅረብ ፈጽሞ አይቻልም ይላሉ::

ሌላው ስለንግግር ምንነት ብያኔ የሰጡት Bygate (1995:14) ናቸው:: እንደሳቸው አገላለጽ ንግግር በጣም ውስን በሆነ ጊዜ ውስጥ እንዴት እንደምንናገር? ምን እንደምንናገር፣ ወዘተ. አገናዝበን መልዕክት የምናስተላልፍበት የመግባቢያ መንገድ መሆኑን በመግለጽ በዚያች አጭር ጊዜ ውስጥ መልዕክቱን ሙሉ በሙሉ ለማስተላለፍ ከመፈለግ የተነሳ የዐረፍተ ነገሮቹ ሰዋስው የተፋለሰ፣ የሚዘለሉ ቃላት የሚበረክቱበት፣ የሐሳብ መያያዙ የላላና የተቆራረጠ ሆኖ እነደሚቀርብ ያስገናዝባሉ::

እንደዚሁም ንግግር ማለት ስሜታችንና ፍላጎታችንን በቃላት አማካኝነት መግለፅ የሚያስችል መልዕክትን ማመንጨት ማገናዘብንና ማውጠንጠንን የሚያጠቃልል፣ በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚከናወን ተግባቦት መሆኑን የሚገልጹት ደግሞ Harmer (2001:269-271) እና Florez and Marry (1999:55) ናቸው::

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የተለያዩ ጽሑፍት ስለንግግር ምንነት የሰጧቸው ብያኔዎች ተደጋጋፊነት ያላቸው ናቸው:: በአጠቃላይ ንግግር ተራን በመጠበቅ የሚናወን፣ ተግባቡ አድማጭንና ተናጋሪን ገጽ ለገጽ ለማገናኘት የሚያስችል፣ ወዘተ. መግባቢያ ነው:: ሰዎች ከሰዎች ጋር በሚያደርጉት ንግግር አማካኝነት ማንነታቸው ይታወቃል፤ ጠላቻን ያፈራሉ፤

ፍቅርን ይመሠርታሉ:: በሀገራችን እነዚህን የሚያጠናክሩ አባባሎች አሉ:: ለምሳሌ "በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ"፣ ጥላቻ መፈጠሩን ሲያመለክት፤ "መልካም ምላስ ቁጣን ታበርዳለች"፣ ጥላቻ መወገዱንና ሰላም መውረዱን ለማመልከት "ከአያያዘ ይቀደዳል፣ ከአነጋገር ይፈረዳለ፣" ከአነጋገር ማንነት መታወቅ እንደሚችል ለመግለጽ የሚያገለግሉ ምሳሌያዊ ንግግሮች ናቸው::

አንደ ሰው በአንድ ቋንቋ የንግግር ክሂሉ ከፍ ያለ ነው ሲባል፤ በቋንቋው አማካኝነት ሐሳቡን በግልጽና አሳማኝ በሆነ መንገድ ማስተላለፍ ይችላል ማለት ብቻ አይደለም:: ሌሎች የሚናገሩትንም መረዳት የሚያስችል ችሎታ አለው ማለት ነው የሚሉት ደግሞ Rechards (1994:82-83) ናቸው:: እንደ እርሳቸው አገላለጽ በንግግር አማካኝነት መግባባት አይገደውም ሲባል ንግግር ሚናዊ በመሆኑ የራሱን ተናግሮ ሌሎች ሲናገሩ አድማጭ ስለሚሆን በአድማጭነት ሚናውም የሌሎች ያልተሟላ ንግግር እያስተካከለለ ሐሳቡን የተሟላ አድርጎ መቀበል ይችላል ማለት ነው::

ቃላዊ በሆነ መልኩ በቋንቋ (በንግግር) ስንግባባ የንግግር ችሎታችን የሚለካው የቋንቋውን የአወቃቀር ስርዓት ጠብቀን መናገር በመቻላችን ብቻ አይደለም (Cunningsworth 1989:43):: የዚያ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነው ኅብረተሰብ በቋንቋው ሲናገር እንዴት ይናገራል? በየትኛው ቦታ ላይ ምን ይናገራል? ማን ለማን ምን ይናገራል? ወዘተ. የሚሉትን ለይቶ በማወቅም ጭምር ነው:: ወጣቶች ከወጣቶች፣ ሴቶች ከሴቶች፣ ሴቶችና ወንዶች ወጣቶችና ሽማግሌዎች፣ ወዘተ. እርስ በእርሳቸው ሲነጋገሩ ምን ሁኔታ ይታያል? አነጋገራቸው ምን ይመስላል? የሚለውን በመለየት በንግግር ተግባቡቱ ጊዜ መግለጽ ሲችል የንግግር ክሂሉ በዚያ ቋንቋ አማካኝነት በተሟላ ሁኔታ መግባባት ያስችለዋል እንላለን::

የንግግር ክሂል ትምህርት የተማሪዎችን የማሰብ አድማሰ ያሰፋል፣ የመግባባት ብቃታቸውን ከቀደመው ችሎታቸው ከፍ እንዲል ያደርጋል (Burton and Dimbleby 1990:12-17):: የንግግር ክሂላቸው እንዲዳብር በቂ የመነጋገሪያ ዓውዶችን በመፍጠር ንግግርን እንዲለማመዱ ማድረግ በተጓዳኝም ለአፍላቂ ክሂል ግብአት የሚሰጡት የማዳመጥና የማንበብ ክሂሎች አብረው እንዲያድጉ ማድረግ ያስፈልጋል (Botsman 1971:38-39)::

2.2. የንግግር ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት

የንግግር ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት ተማሪዎች ሐሳባቸውን ያለምንም መደናቀፍና መደናገር በንግግር ማስተላለፍ እንዲችሉ የሚያደርጋቸውን ዕውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ነው:: የቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ ቋንቋውን በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚጠቀምበት ዕውቀትና ክህሎት ማግኘት የሚቻለው በንግግር ክሂል ትምህርት ነው::

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ቋንቋው ጎብረተሰቡ በሚጠቀምበት መልኩ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ እንዲጠቀሙበት ለማስቻል የንግግር ክሂል ትምህርት አስፈላጊ ነው (Mac Donough and Shaw 1994:154, Riggebach and Lazarto 1991:126, Ur 1996:120)::

ተማሪዎች ሳያፍሩና ሳይፈሩ በክፍል ጓደኞቻቸውና በመምህራቸው ፊት ሐሳባቸውን በትክክል መግለጽ የሚያስችላቸውን ችሎታ አግኝተው በማህበራዊ ሕይወታቸው የሚፈልጉትን ጉዳይ በንግግር ማስተላለፍ እንዲችሉ የንግግር ክሂል ትምህርትን በትምህርት ቤት ቀስመው መውጣት ይኖርባቸዋል:: ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ ይዘቶች ተመርጠውና ተደራጅተው መቅረብ ይገባቸዋል:: ይህንኑ አስመልክቶ Echeverria (1987:10) እንደሚከተለው ይገልፁታል:-

> *ተማሪዎች የንግግር ክሂልን ትምህርት እንዲማሩ የሚያስፈልግበት ምክንያት ሐሳባቸውን ለአድማጫቸው ተስማሚና ተቀባይነት ባለው መልኩ ማቅረብን እንዲለማመዱ ለማድረግ ነው:: ይህንን ልምምድ በትምህርት ቤት እንዲያደርጉ ለማስቻል በቋንቋ መማሪያ መጻሐፎቻቸው ውስጥ የሚቀርቡ የንግግር ትምህርት ይዘቶች ለዚሁ ተስማሚ ሆነው መመረጥና መደራጀት ይገባቸዋል:: መጻሐፎቹ አንደኛ ለሚና አከራካሪ ጉዳዮችን በማንሳት ተማሪዎቹ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር አንዱን በመደገፍ ሌላው በመቃወም ሀሳባቸውን ያለሐፍረትና ፍርሐት መግለጽ በሚያስችል ሁኔታ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል:: ሁለተኛ አንድን ርዕሰ ጉዳይ መሠረት በማድረግ ማብራሪያና መግለጫ አንዲሰጡ የሚያበረታቱ ሊሆኑ ይገባቸዋል:: ሶስተኛ የሐሳቦችን ቅደም ተከተል በመጠበቅ አድማጭን ሊያሳምን በሚችል መልኩ ንግግር እንዲያደርጉ የሚጋብዙ መሆን ይጠበቅባቸዋል:: አራተኛ በጋራ በመወያየትና በመደማመጥ /ተራን ጠብቆ በመነጋገር/ ለችግሮች መፍትሄ መስጠትን የሚያለማምዱ ይዘቶችን ይዘው መቅረብ አለባቸው ይላሉ::*

ከቀረበው የንግግር ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት መረዳት እንደሚቻው ተማሪዎች ንግግርን ሲያቀርቡ ማስተዋል የሚገባቸው ነገር የምናገረው ጉዳይ ተቀባይነት አለው ወይ? የሚለውን ነው:: ንግግር ለመናገር ብቻ የሚቀርብ መሆን የለበትም:: ለአድማጭ የሚሰጠው አንዳች ጥቅም መኖር አለበት:: ትምህርተ ሰጪ ሆኖ እውቀትን የሚገነባ አስደሳች ሆኖ የሚያዝናና ወዘተ. ሊሆን ይገባዋል::

በተጨማሪም በደሉ (1996 59) የBlock (1997)ን ስራ መሠረት በማድረግ የንግግር ክሂልን አስፈላጊነት እንደሚከተለው አቅርበውታል

አብዛኞቹ ተማሪዎች የክፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁት ጥሩ የንግግር ችሎታ ሳያዳብሩ ነው:: በመሆኑም ከትምህረት ቤት በኋላ ባለው ሕይወታቸው ያለምንም ችግር ሐሳባቸውን በንግግር ለመግለጽ ይቸገራሉ:: በራስ ያለመተማመን /ዓይናፋርነት/ መልዕክትን በምክንያትና በውጤት አቀናጅቶ ያለማቅረብና የቋንቋውን ሥርዓት ያለመጠበቅ ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ የማስተማር አስፈላጊነት እነዚህን ንዑሳን ክሂሎች በማዳበር ተማሪዎቹ ጥሩ የመናገር ችሎታ ያላቸው /የማያፍሩና የማይፈሩ፣ የማይደነጋገሩ፣ ሀሳባቸውን መግለጽ የሚችሉ፣.../ ለማድረግ ነው::

በድሉ የጠቀሱት ችግር ተማሪዎች ከመጀመሪያዎቹ የክፍል ደረጃዎች ጀምሮ ንግግርን እየተለማመዱ ካለመምጣት የሚመነጭ ነው:: ከመጀመሪያው ጀምሮ ደረጃ በደረጃ እያደገ ሊመጣ የሚገባው ነው:: ከስር ጀምሮ እያደገ ካልመጣ በመጨረሻዎቹ ደረጃዎች ላይ ንግግር ለማድረግ ብቃት ያላቸውን ተማሪዎች ለማገኘት ይገዳል::

የመማሪያ መጻሕፍቱ ንዑሳን የንግግር ክሂሎችን ለማዳበር በሚያስችል መልኩ መዘጋጀት ቢችሉ እንኳ ክሂሎቹን በማጎልበቱ ተግባራዊ ሂደት ላይ ችግሮች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ Ur (1996 121) እና በደሉ (1996 59-60) ያስረዳሉ:: የእነዚህ ችግሮች ምንጭ ተማሪዎቹ ከመሆናቸው የተነሳ የንግግር ክሂልን ለማዳበር በሚደረገው ጥረት ተሳታፊ ያለመሆን ባህሪ ይታይባቸዋል:: ከተሳትፎ ውጪ መሆናቸው የሚገለጹባቸው ሁኔታዎች የሚከተሉት እንደሆኑ ይዘረዝሯቸዋል፤

1. **በመታቀብ** (Inhibition):- ተማሪዎች ንግግሩን በክፍል በሚያቀርቡበት ወቅት የአድማጭን ትኩረት መሳብ አልችልም በሚል ፍርሐት ይሰማቸውና ለመናገር ፈቃደኛ አለመሆን ይታይባቸዋል:: በቡድን ተደራጅተው በሚወያዩበት ጊዜ እንኳ ቢሆን የተሻለ ነገር አላቀርብም በሚል መታቀብን ይመርጣሉ::
2. **የሚናገሩት ነገር በማጣት** (Nothing to say):- ለውይይት በቀረበው ጉዳይ ግንዛቤ የለኝም በሚል ሰበብ ለመናገር ፈቃደኛ ያለመሆን ሌላው ችግር ነው:: የዚህ ችግር መንሥኤ በሁለት መንገድ ሊታይ ይችላል:: አንደኛው ለመናገር ካለመፈለግ የተነሳ

ሰበበ ሲሆን ሁለተኛው በተነሳው ጉዳይ ላይ በቂ ግንዛቤ ካለመኖርም ሊሆን ይችላል::

3. **ዝቅተኛ ወይም ያልተስተካከለ ተሳትፎ በማድረግ** (Low or Uneven Participation):- አብዛኛውን ጊዜ የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባራት ላይ በአንድ ጊዜ የሚሳተፈው አንድ ተማሪ ብቻ ነው:: በዚህ አይነት ሁኔታ በርካታ ተማሪዎችን በንግግር ተግባር ላይ ማሳተፍ ለቋንቋ ትምህርት ከተመደበው ጊዜ ጋር ሊጣጣም የማይችል ይሆናል:: በእንዲህ ዓይነቱ የክፍል ወስጥ የንግግር ተግባር አብዛኛውን ጊዜ ተጠቃሚ የሚሆኑት በባህሪያቸው ተሳታፊ (Extrovert) የሆኑ ተማሪዎች ናቸው:: ጭምት (Introvert) ተማሪዎች በዚህ ዓይነቱ የክፍል ውስጥ ንግግር ተግባር ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት ስለማይኖራቸው ተጠቃሚ አይሆኑም ይላሉ::

ከዚህ በላይ ለተዘረዘሩትና ለሌሎችም የንግግር ክሂልን ለማዳበር በሚደረግ የትምህርት ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመቅረፍ መፍትሄ የሚሏቸውን ሌሎች ጸሐፊዎች አቅረበዋል:: የጸሐፊዎቹን አጠቃላይ ሐሳብ ወስደን ስንመለከተው ተማሪዎች ቃላዊ ተገባቦታቸውን ከፍ የሚያደርጉ ይዘቶች በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ቀርበውቸው ሲለማመዱ ከመናገር የሚገታቸውንና ተሳትፎአቸውን ዝቅ የሚያደርጉባቸውን ተላውጠዎች ለማስወገድ መጀመሪያ ንግግር የሚያደርጉለትን አድማጭ እንዲለዩ ማስቻል ነው:: ንግግር የሚያደርጉበትን አድማጭ ከለዩ በኋላ በዚያ አድማጭ ንግግር እንዲደረግ ያስፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው የሚለውን ጥያቄ እንዲመልሱ ማድረግ ያስፈልጋል:: ይህን ጥያቄ ከመለሱ በኋላ ንግግሩን በምን ርዕስ ላይ ባደርግ የአድማጭ ስሜት መግዛት እችላለሁ? ብለው ራሳቸውን እንዲፈትሹ መገፋፋት ነው:: ከዚህ በኋላ ተማሪዎቹ ከመናገር መታቀብ፣ የሚናገሩት ሀሳብ መጥፋት፣ ... ችግር ይላቀቃሉ (Echeverria 1987:28 billows 1964:18-19)::

በድኃረ ገጽ የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን የንግግር ክሂል እንዲማሩ ማድረግ መታለፍ የማይገባው ተግባር ነው ይልና የመማራቸውንም አስፈላጊነት ሲገልፅ እንደሚከተለው ያቀርበዋል::

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት (Elementary School) ህፃናት የንግግር ክሂልን እንዲማሩ የሚፈለግባቸው ምክንያቶች በርካታ ናቸው:: ከበርካታዎቹ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው:-

1. ሕጻናቱ በልበ ሙሉነት በራስ በመተማመንና በድፍረት ሐሳበቸውን ከሰዎች ፊት ቀርበው መግለፅ እንዲችሉ፤

2. ድምፆችንና ቃላትን ሲያወጡ ድምፃቸው ጎላ ብሎ ለሰዎች ጆሮ በቀላሉ እንዲደርስ ለማለማመድ በሚኖሩበት አካባቢ ህብረተሰብ ዘንድ በቋንቋ አጠቃቀማቸው (በንግግር አቀራረባቸው) ምክንያት ተቀባይነትን እንዳያጡ ወይም እንዲገኙ ለማድረግ፤
3. በሰዎች ፊት ንግግርን በሚያቀርቡበት ወቅት ሐሳባቸው ሳይፋለስና ሳይበታተን የማቅረብ ችሎታን እንዲያዳብሩ፤
4. በቡድን ውይይት ንቁ ተሳታፊዎች ሆነው እንዲገኙ
5. ስድ ጽሑፎችንም (prose) ሆነ ግጥሞችን ሲያቀርቡ ቅላጼው በሚማርክ ሁኔታ የማቅረብ ችሎታን እንዲያጎለብቱና በአድማጭ ዘንድ ተቀባይነትን እንዲያገኙ ለማድረግ ነው (http://www.jstor.orgpromoost1950:31) ::

ይኽው ምንጭ የንግግርን ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት በዚህ መልኩ ከገለፀ በኋላ እነዚህን ልምዶች ተማሪዎቹ እንዲያዳብሩ ለማስቻል በመማሪያ መጽሀፎቻቸው ውስጥ የሚቀርቡ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች ሊያካትቷቸው የሚገቧቸውን ነጥቦች ያመለክታል::

1. የተማሪዎችን ስሜትና ፍላጎት ሊቀሰቅሱ የሚችሉ፣ ከእድሜያቸውና ከደረጃቸው ጋር የሚመጣጠኑ የንግግር ማለማመጃ ይዘቶችን መርጦ ማዘጋጀትና አስልቺ ባልሆነ መልኩ ማቅረብ
2. ሕጻናቱ /ተማሪዎቹ/ የንግግር ችሎታቸው በየጊዜው በሚያደርጉት የንግግር ልምምድ እያደገ መሄዱን መገምገም የሚያስችሉ መመዘኛዎችንም ጭምር መማሪያ መጻሕፍቱ መያዝ ይኖርባቸዋል:: በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የንግግር ችሎታ አድገት ራሳቸው ተማሪዎቹም ሆኑ መምህሩ የሚለኩበትን መንገድ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል::
3. ንግግርን የሚለማመዱበት ጊዜ አጭር ቢሆንም ከነጭራሹ እንዳይዘለል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል::
4. ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ባልተናነሰ ሁኔታ የንግግር ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ መለማመጃዎች መገኘት ይኖርባቸዋል::

በተለይ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሆነውን ቋንቋ የሚማሩ ሕጻናት ቋንቋውን እንዲማሩ የሚደረግበት ምክንያት እንደባህልና እምነታቸው ተራን ጠብቀው መናገርን፣ የንግግር መክፈቻና መዝጊያ ሂደትን እንዲያውቁ አፅንኦት የሚሰጥባቸውን ጉዳዮች እንዲለዩ፣ ያታዊ ጉዳዮችን አክብረው እንዲገልጹ፣ የአካል እንቅስቃሴዎቻቸውን ከንግግራቸው ጋር ማጣጣም እንዲችሉ፣

የሚናገሩበትን ርዕሰ ጉዳይ ጠብቀው እንዲናገሩ ወዘተ. ለማስቻል መሆኑን የሚገልፁት ደግሞ Nolasco and Arther (1989:9-12) ናቸው::

በአጠቃላይ የንግግር ክሂል ትምህርት አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት የንግግር ክሂልን ንዑሳን ክሂሎች እንዲዳብሩ ለማድረግ ነው:: ከሰዎች ፊት ሳያፍሩና ሳይፈሩ ለመናገር ሀሳብን ሀሳብን ሳያዛንፉና ሳይደባልቁ ለመግለጽ፣ ለአድማጭ አስደሳችና ተስማሚ የሆነ ርዕሰ ጉዳይን መምረጥ እንዲችሉ ለማድረግ የሚሉትንና ሌሎችንም እንዱያሟሉ ለማድረግ ነው::

2.3. የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አዘገጃጀት (በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ሲታይ)

በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አዘገጃጀትን ከመመልከታችን በፊት የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አዘገጃጀት ምን መምሰል እንዳበት የተለያዩ ጸሐፊዎች የሰጡትን አስተያየት በአጭሩ እንቃኝ::

የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ አስቀድሞ ከግምት ውስጥ መግባት የሚገባቸው ጉዳዮች እንዳሉ Skierso (1999:432) ሲዘረዝሩ:-

1. የተማሪዎችን ዳራ ማወቅ፤ ተማሪዎቹ እነማን ናቸው? የሚለውን ጥያቄ በማንሳት ስለተማሪዎቹ እድሜ፣ ፆታ፣ የክፍል ደረጃ፣ በቋንቋው ያላቸው የቀደመ ችሎታ፣ የመጡበት ጎብረተሰብ /ባህሉ፣ እምነቱ፣ የኢኮኖሚ ሁኔታ/ የመጡበት አካባቢ. /ገጠር ከተማ/ እና ቋንቋውን የሚማሩት ለምን ግልጋሎት ነው? የሚለውን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይገባዋል::
2. ትምህርቱን የሚያስተምሩትን መምህራን ዳራ ማወቅ፤ በተመረጠው የክፍል ደረጃ የሚቀርበውን የቋንቋ ትምህርት ለማስተማር የሚመደቡት መምህራን የሚጠበቅባቸው ስልጠናና ትምህርት እንዳላቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ያንን የሚፈለግ ስልጠናና ትምህርተ ተከታትለው የሚመደቡ መምህራንን ታሳቢ ተደርጎ መጽሐፉ ሊዘጋጅ ይገባዋል::
3. የመርሐ ትምህርቱን ዓላማዎች የሚያሳካና በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ይዘቶች መሰረት ያደረገ ሆኖ መዘጋጀት ይኖርበታል:: መርሐ ትምህርቱ የቋንቋውን ትምህርት ዓላማዎችና ይዘቶች የያዘ ከመሆኑም ባሻገር ይዘቶቹ በምን ዓይነት መንገድ ለተማሪው መቅረብ እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው:: በዚህ መሠረት የመማሪያ መጻሕፍቱም በመርሐ-ትምህርቱ ከግብ ለማድረስ የተፈለገውን ዓላማ መሠረት በማድረግ መነሳት ይኖርባቸዋል:: የሚመረጡትም ይዘቶች የዚያን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ለማሳካት የሚረዱ ሊሆኑ ይገባል::

4. ተቋማዊ መረጃዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል፤ የቋንቋ ትምህርቱ ለምን ያህል ጊዜ /ክፍለ ጊዜው፣ በሳምንት፣ በወር፣ በዓመት/ እንደሆነ? የሚሰጠው መቼና የት እንደሆነ? ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚቀርበውን /የሚዘጋጀውን/ ይዘት ከተቋሙ /ከትምህርት ቤቱ/ የሥራ ዘመን አንጻር መጥኖ ማቅረብ ያስፈልጋል በማለት እንዚህን ሁኔታዎች ባገናዘበ መልኩ የሚዘጋጅ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ቋንቋውን ለማስተማር አመቺ ሊሆን እንደሚችል ይገለጻሉ:: ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ ብዙ ባልተለየ ሁኔታ Grant (1989:118) በበኩላቸው ስለቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አዘገጃጀት የሚከተለውን ሐሳብ ያቀርባሉ የቋንቋ መማረያ መጽሀፍ በሚዘጋጅበት ወቅት ትኩረት ሊደርግባቸው የሚገቡ ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮች አሉ:: እነሱም

1ኛ. የተማሪውን ፍላጎት ስሜት ችሎታ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን፣

2ኛ. መምህራኑን በማስተማር ሥራቸው ላይ ቀና መንገድ የሚከፍትላቸው መሆን፣

3ኛ. የቋንቋው ትምህርት የሚሰጥበትን ሀገር የትምህርት መርሐ የተከተለና ከወቅቱ፣ የትምህርት ፖሊሲና ሥርዓተ ትምህርት አንጻር የተቃኘ መሆን ይኖርበታል ይላሉ::

እንደዚሁም Ur (1996:183) የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ሲዘጋጅ በቋንቋ ትምህርት ሂደት መምህሩና ተማሪው ሊይዙት የሚገባውን ትክክለኛ የመማር ማስተማር አቅጣጫ ቁልጭ አድረጎ እንዲያሳይ ተነባቢነቱ ከፍተኛ እንዲሆን አዳዲስ እውቀቶችን እንዲያሰርጽ ሆኖ መዘጋጀት እንዳለበት ያስገነዝባሉ::

ከዚህ በላይ የተመለከተናቸው የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ ታሳቢ የሚሆኑ አጠቃላይ የሆኑ ጉዳዮችን ነው:: ቀጥለን ደግሞ በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አዘገጃጀት ምን መምሰል እንዳለበት እንመለከታለን::

የንግግር ክሂልን ለማስተማር የሚዘጋጅ መማሪያ መጽሐፍ በዝግጅቱ ወቅት ከግምት ውስጥ ሊያስገባቸው የሚገቡትን ነጥቦች Grant (1989:34-35) ሲጠቀሙ እንዲህ ይላሉ

ለንግግር ክሂል ትምህርት ተብሎ የሚዘጋጅ የመማሪያ መጽሐፍ ሦስት ዓይነት የንግግር ተግባራትን አካቶ መያዝ ይኖርበታል:: ተግባራቱም ድግግሞሽ (Drills)፣ ተግባቦታዊ ልምምድ (መልመጃዎችን ጭምር የያዙ) (communicative practice exercise) እና ተፈጥራዊ የቋንቋ አጠቃቀም (Natural language use) ናቸው ይሉና እነዚህ ተግባራት የተማሪውን የንግግር ክሂል ትምህርት በተፋጠነ ሁኔታ ከፍ ሊያደርጉለትም እንደሚችሉ ይጠቁማሉ:: ይሁን እንጅ በርካታ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ምንም ዓይነት ተግባቦታዊ

ተግባራትን ያለማካተት፣ በጣም አነስተኛና በቂ ያልሆኑ ተግባቦታዊ ተግባራትን መያዝ፣ ለተማሪዎች በሚመጥን መልኩ የተግባቦት ይዘቶችን አለመምረጥ፣ የተማረዎችን ዳራ ያላገናዘቡ ድግግሞሾችን ልምምዶችን ወዘተ. ይዘው የመገኘት ሁኔታ ብዙ ጊዜ እነደሚታይ ያስረዳሉ::

የሶስቱን ተግባራት ምንነትም በሚከተለው ሁኔታ ሠፋ አድርገው አብራርተዋቸዋል::

ሀ. ድግግሞሽ (Drills):- የአንድን ድምጽ ወይም ቃል አባባልና ሰዋስውን ተማሪዎች በንግግር የሚያጠኑበት ነው:: ምንም ብዙ መሰላሰልና ማውጣት ማውረድ የማይጠይቅ በሚቀርቡ ምሳሌዎች መሰረት የተወሰኑ ክፍሎችን በመለዋወጥ ልምምድን የሚሰሩበት ነው::

ለ. ተግባቦታዊ ልምምድ /ተግባር/ (communicative practice exercise):- የንግግር ክሂልን ለማስተማር የተዘጋጀ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሊይዘው የሚገባው ሁለተኛው ተግባቦታዊ ተግባር ነው:: በዚህ ተግባር ከተማሪዎች የሚጠበቀው ቋንቋውን ለመግባቢያነት መጠቀም እንጅ ትክክለኝነትን ማምጣት አይደለም:: ይህ የልምምድ ተግባር ሲከናወን ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን አየሆኑ እንዲነጋገሩ ይደረጋል:: የመምህሩ ተግባር የሚያደርጉትን ተግባቦታዊ ተግባራት መከታተል ነው:: ከተማሪዎች የሚጠበቀር ቋንቋውን ተጠቅመው ሐሳቦቸውን በትክክል ከማስተላለፍ ላይ እንጅ በቋንቋው /ቅርጽ/ ሰዋስው ትክክለኝነት ላይ አይደለም::

ሐ. ተፈጥሯዊ የቋንቋ አጠቃቀም (Natural language use):- ተማሪዎች የንግግር ክሂል ትምህርት ሲማሩ ተፈጥሯዊና እውነተኛ የሆነውን የቋንቋ አጠቃቀም ከነዓውዱ የሚለማመዱበትን ዕድል ማግኘት አለባቸው:: በዝግጅቱ ጊዜ ዓውድ በመፍጠር ተግባራዊ እንዲሆን የሚያስችል አካሄድን መከተል ያስፈልጋል:: አንዳንድ ጊዜ ተማሪዎች አጠቃቀሙን በዓውድ ለመተግበር የሚቸገሩበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል:: እንዲህ ሲሆን መምህሩ የቅርብ አጋዥ ሆኖ የሚያለማምድበት ፋታ ማሳየት የዝግጅቱ ድርሻ ነው::

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦት ንግግር ለማስተማር የሚዘጋጅ መጽሐፍ ሊያካትታቸው የሚገባ አጠቃላይ ነጥቦች ናቸው:: ከዚህ በኋላ በንግግር ክሂል ትምህርት ሂደት ውስጥ በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ መታየት የሚገባቸው የንግግር ክሂል ትምህርት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ የሚሉትን ዘርዘር አድርገን እንመለከታለን::

2.3.1. የንግግር ክሂል ትምህርት የይዘት አመራረጥ

ምርጫ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ካሉ ቁሶች፣ ነገሮች ወይም ጉዳዮች መካከል የተሻለ የሚባለውን መውሰድን ያመለክታል /ወንደወሰን፣ 1995፣37/:: የንግግር ክሂልን ለማስተማር የሚመረጡት ይዘቶች የቋንቋው ተናጋሪ የሆነው ኅብረተሰብ በንግግር ተግባቦቱ ጊዜ

ከሚጠቀምባቸው ውስጥ በመምረጥ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በማካተት ለትምህርት እንዲውሉ ይደረጋል:: ምርጫው በሚደረግበት ወቅት ታሳቢ ሊሆኑ የሚገባቸውን በጥሞና ማየት ይገባል::

ቋንቋውን ለማስተማር የሚመረጠው ይዘት ተማሪው እንዲማረው የሚፈለገውን የቋንቋ ዕውቀትና ክህሎት ለማዳበር ይችላል ተብሎ የሚገመተው ነው (Nunan 1988:10):: ይህ ዕውቀትና ክህሎት ደግሞ አስቀድሞ የተነደፈውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ለማሳካት መቻል አለበት:: ዓላማውን ከግብ ማድረስ የማይችሉ ይዘቶች በምርጫው ማጣሪያ እንዲቀሩ ይደረጋል (Taba 1962:282)::

ምንም እንኳ የተለያዩ ምሁራን ተቀራራቢነት ያላቸውን የይዘት መምረጫ መስፈርቶችን ያቀረቡ ቢሆንም Smith (1950) እና Mackey (1962) ዘርዘር ያሉ መስፈርቶችን አስቀምጠዋል:: በተለይም Smith (1950:132-137) አምስት ያህል መስፈርቶችን ዘርዝረዋል:: እነሱም:-

- አስፈላጊነት:- የተመረጠው ይዘት ተማሪው እንዲያውቀው የተደረገበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስም ሆነ ለተማሪው ሕይወት አስፈላጊ ሆኖ መገኘት መቻሉን መሳያ ነው::
- ዘላቂነት:- ይዘቱ በቀጣይ የተማሪው ህይወት አብሮ የሚቆይና እውነተኛ የሆነ መሆኑን የሚይሳይ ነው::
- ጠቃሚነት:- በተማሪው ሕይወት ውስጥ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውል የክሂል ዘርፍ መምረጫ መሆኑን አመላካች ነው::
- አስደሳች:- የተማሪውን ፍላጎት ለማሟላት፣ ችግሩን ለመፍታት የሚያስችለውና ለስሜቱ የቀረበ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘት መምረጥ እንደሚገባ የሚያመለክት ነው::
- ወቅታዊነት:- ተማሪው ለማሕበራዊ ሕይወቱና ተግባራቱ መከወኛ፣ ተሳታፊነቱን ከፍ የሚያደርግ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘት በመምረጥ አስፈላጊነት ላይ የሚያተኩር መስፈርት ነው::

Mackey (1962:176-187) በበኩላቸው አምስት የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘት መምረጫ መስፈርቶችን አቅርበዋል::

- ተደጋጋሚነት:- በአንድ በተመረጠ ንግግር ውስጥ ተደጋግሞ ሊመጣ የሚችለውን ክፍል መምረጥ፤ ያንን የተመረጠውን ደጋግሞ ማለማመድ፤
- የፍቺ ስፋት:- በርካታ ሊገለጹ የሚችሉ ጉዳዮችን አካቶ ለመግለጽ የሚችለውንና ሌሎችም ተክቶ በመግባት ሊገልጽ የሚችለውን የቋንቋ ክፍል መምረጥ፤

- ለመማር አመቺነት ያለው:- የመማር ጫናው ከትምህርቱ በኋላ ከሚሰጠው ጠቀሜታ የቀለለውን አጭርና ቀላል አቀራረብ ያለውን የቋንቋውን ሕግጋት የሚያፋልስ አካሄዶች የማይታዩበትን መምረጥ፤
- ልቀት (Range):- ተደጋግመው ከሚመጡት ውስጥ ላቅ ያለ ብልጫ ያሳየውን መርጦ ማቅረብና ከዚያም በተዋረድ መሄድ፤
- አመቺነት (availability) በቀላሉ ሊገኝ የሚችለውንና ተግባራዊ ሊደረግ የሚችለውን ዘርፍ መመረጥ ይገባል በማለት የመምረጫ መስፈርቶቻቸውን አስቀምጠዋል::

እነዚህ በሁለቱ ጸሐፊዎች አማካኝነት የቀረቡት የይዘት መምረጫ መስፈርቶች የሚደጋገፉ በመሆናቸው በመማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት ጊዜ ትኩረተ ሊደረግባቸው ይገባል:: የሁለቱን አስተያየቶች በማጣመር እንዲሰሩ ቢደረግ የሚሻል ይመስላል::

ለዚህ ጥናተ መነሻ የሆኑት ቀደም ሲል በተጠቀሱት ክልልና ዞን የቀረበው የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ለአማርኛ ቋንቋ መማሪያነት የሚገለግሉት መጻሕፍት የንግግር ክሂልን ለመማር የሚመረጡት ይዘቶች ምን መምሰል ይገባቸዋል? ብለን መቃኘት አስፈላጊ ይሆናል:: ስለዚህ ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ትውረቶች በማንሣት እንመለከታለን::

በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች ንግግርን የሚማሩ ተማሪዎች የሚመረጡላቸው ይዘቶች አዝናኝነት ያላቸው በተረት፣ በእንቆቅልሽ፣ በሥዕል መልክ የሚቀርቡ ሆነው የሚያሰለቹ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል የሚሉት Bygate (1995:3-4) ናቸው:: እኒሁ ጸሐፊ በመቀጠልም በዚህ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች ቋንቋው የአፍ መፍቻቸው ስለሆነ መግባባት የሚችሉበት ቢሆንም ቋንቋውን ለንግግር ሲያውሉት በምን ዓይነት ዓውድ ውስጥ ሆነው መነጋገር እንዳባቸው ግንዛቤ የሚያስጨብጡ መሆን ይኖርባቸዋል:: ይዘቶች በጨዋታ መልክ፣ በቡድን የሚከናወኑ ተግባራትን መያዝ አለባቸው ይላሉ::

Ur (1996:131) ደግሞ ለንግግር ክሂል ትምህርት የሚቀርቡ ይዘቶች ሲመረጡ በቅድሚያ ሊያሙዋሉዋቸው የሚገቡ መመዘኛዎች የሚከተሉት ናቸው ይላሉ፤

- ተማሪዎች የንግግር ችሎታቸውን ለማዳበር ሐሳባቸውን በንግግር ለመግለጽ የሚያስችሉ፣
- ፈጥኖ የመናገር ችሎታን ከፍ ለማድረግና ሐፍረትን ለማስወገድ የሚረዱ እና
- ሐሳብ የመግለጽን አቅም በማጎልበት ተጠየቃዊ በሆነ አካሄድ ነገሮችን መተንተን የሚያስችሉ የሚሉት መሆን እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ::

ትምህርት ሚኒስቴር የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲና አተገባበሩ በሚለው ጽሑፉ ከላይ የቀረቡትን ሐሳቦች በማጠናከር እንደሚከተለው አቅርቦታል::

የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው እርከን ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ ተደርጓል:: ይህ ከተደረገባቸው ምክንያቶች ውስጥ ሕጻናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማካኝነት ሐሳባቸውን ነጻ ሆነው መግለጽ እንዲችሉ ነው:: በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀሳባቸውን በሰው ፊት የመግለጽ ችሎታውን እያዳበሩ ሲሄዱ በሁለተኛ ቋንቋዎቻቸው እንዲማሩ ቢደረጉም በየክፍል ደረጃው የንግግር ችሎታ ከፍ እያለ ይሄዳል (ት/ሚ1994:24-44)::

2.3.2. የንግግር ክሂል ትምህርት የይዘት አደረጃጀት

ይዘቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ አደራጅቶ የቋንቋውን ትምህርት ለመስጠት ይቻል ዘንድ በርካታ ምሁራን የሚስማሙባቸው የይዘት አደረጃጀት መርሆዎች አሉ:: እነዚህን መርሆዎች በማውጣት ከሚጠቀሱት ውስጥ Tyler (1949) Taba (1920) ይገኙበታል:: መስፈርቶቹ የሚከተሉት ናቸው፤

1. ተከታታይነት:- አንድ ይዘት በተከታታይ ጊዜያት ውስጥ ሊከሰት የሚችለበትን ቀጥተኛ ሁኔታ ያመለክታል:: ተከታታየነት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የንግግር ክሂል ወይም ሌላ የክሂል ዓይነት /ዕውቀት/ ተደጋግሞ የሚመጣበትና በልምምድ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ይገልጻል:: Tyler (1949:85) እንደሚገልፁት ተከታታየነት በትምህርት ክፍሎች መሃል ያለውን ቀጥተኛ ግንኙነት የሚገልጽ ሲሆን ይህም በአንድ የትምህርት ዓይነት የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ተደጋግሞ ይዘቱ መከሰቱን የሚያስረዳ ነው::
2. ተለጣጣቂነት:- ተለጣጣቂነት ከተከታታይነት ጋር የተዛመደ ቢሆንም ተከታታየነትን አልፎ የሚሄድ የይዘቶች በየደረጃው እየተደጋገፈና አንዱ ከአንድ ላይ እየተመሠረተ፣ አንዱ ሌላው እየደገፈና እያሳደገ የሚሄድበት ነው (ተስፋዬ 1981:9):: እያንዳንዱ የክሂል ይዘት በቀዳሚው ላይ ተመሥርቶ ስፋትና ጥልቀት እያገኘ፣ ከቅርብ ወደሩቅ፣ ከቀላል ወደከባድ፣ እያደገ፣ ጥልቅ የንግግር ዕውቀትን ለማስጨበጥ በሚያስችል መልኩ የሚደራጅ ነው::
3. ተቀናጂነት:-በአንድ ክፍል የተገኘው ዕውቀትና ክህሎት ከሌላው የክሂል ይዘት ጋር ተዛማጅነትና ተደጋጋፊነት እንዲኖረው ማድረግን የሚያመለክት የአደረጃጀት መስፈርት ነው (Taba 1962:298)::

በአጠቃላይ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች ሲዋቀሩ ሁለት የግንኙነት ትስስር መስመሮችን መከተል ይገባል:: እነዚህ የግንኙነት መስመሮች ቀጥተኛና ጎናዊ ናቸው (Tyler 1949:83):: ቀጥተኛው መስመር የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘት በተከታታይ የክፍል ደረጃዎችም ሆነ በአንድ የክፍል ደረጃ ውስጥ ያለውን ግንኙነት የሚያመለክት ነው:: ጎናዊ የግንኙነት መስመር ደግሞ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከሌሎች የክሂል ትምህርት ይዘቶች ጋር ያለውን ተደጋጋፊነት የሚያመለክት ነው::

ለንግግር ክሂል ትምህርት የሚመረጡት ይዘቶች ከተራ ወደ ውስብስብ፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከሚታወቅ ወደማይታወቅ እየተሸጋገሩ ማደራጀትም ሌላው በንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ጊዜ ሊታይ የሚገባው መርሐ ነው (Buny 1995:142)::

በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች የሚቀርቡ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተመርጠው ሲደራጁ መከተል ያለባቸው ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ትውረቶች የተለየ አይደለም:: ለሕጻናት ተመርጠው የሚቀርቡና የንግግር ክሂልን ትምህርት ለማዳበር የሚረዱ ይዘቶች ሲደራጁ ሕጻናቱ ከሚያውቋቸው በመነሳት ወደማያውቋቸውና ሊለማመዱዋቸው ወደሚገቡ ይዘቶች መሸጋገር አለባቸው (Bygate 1995:8-9):: የእርስ በርስ ሰላምታ መለዋወጥ ሥርዓትን የሚያስተዋውቁና ሠላምታ እንዲለዋወጡ የሚያደርጉ የንግግር ክሂል ትምህርት በማስቀደም፣ ሥለራሳቸውና ቤተሰባቸው እንዲናገሩ የሚያደርጉ ይዘቶችን ማቅረብ፣ ቀጥሎ በአካባቢያቸው የሰሟቸውን ተረቶች፣ እንቆቅልሾችና ሌሎችም በቃል የሚነገሩ ኪናዊ አባባሎችን እንዲናገሩ የሚያስችሉ ይዘቶችን ማደራጀት ይገባል:: ከዚህ በኋላ ሥዕሎችን አይተው ግንዛቤያቸውን የሚገልፁበትን የቡድን ውይይት የሚያደርጉበትን፣ የሐሳብ ልውውጦችን በክርክር፣ በቃል ምልልስ፣ በጥያቄ፣ ወዘተ. መልክ እየተለማመዱ የሚሄዱበትን የይዘት አደረጃጀት መከተል ጠቃሚ እንሚሆን ይታመናል (ተስፋዬ 1981 1981:10፣ Bygate 1995:341፣ Grant 1989:47-6፣ Conningsworth (1989:43)::

የተመረጡትን የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከማደራጀት አንጻር ሌላው ሊታይ የሚገባው የጊዜ ጉዳይ መሆኑን Conningsworth (1989:24-26) ያስገነዝባሉ:: የንግግር ክሂል ለማስተማር የተመረጡት ይዘቶች ለእያንዳንዳቸው ሊሰጣቸው የሚገባው ጊዜ የተማሪዎችን የመቀበል ችሎታ ከእድሜያቸውና ከደረጃቸው አንጻር መመጠን ያስፈልጋል ይላሉ:: ለሁሉም የተመረጡ ይዘቶች የትምህርት ጊዜያትን እኩል ከመሸንሸን ባለፈ ሁኔታ ጥናት በማድረግ እንደይዘቶቹ ስፋትና ጥበት፣ ቀለትና ክብደት የሚያስፈልገውን ጊዜ አደረጃጀቱ ላይ ማሳየት ያስፈልጋል::

2.3.3. የንግግር ክሂል ትምህርት የይዘት አቀራረብ

የንግግር ክሂልን አቀራረብ የሚወስነው ተማሪው ቋንቋውን /ንግግር/ የሚማርበት ዓላማ ነው (Annsnow 1991:316):: ተማሪው ቋንቋውን የሚማርበት ዓላማ በሦስት ጉዳዮች ሊወሰን ይችላል:: በተማሪው በራሱ ፍላጎት፣ በሀገሪቱ የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲና በቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት ይወሰናል:: እነዚህ ሁኔታዎች ወሳኝነት ያላቸው ቢሆኑም ከቋንቋ ትምህርት ትውረት አንጻር በርከት ያሉ የቋንቋ ትምህርት የማስተማር አቀራረቦች በየዘመኑ ሲነሱ ቆይተዋል:: ከመምህር ተኮር እስከ ተማሪ ተኮር የቋንቋውን ሕግጋት ከማጥናት እስከ ቋንቋውን ለተግባቦት የሚውልበት ታይተዋል::

/ የመማር ማስተማር አቀራረብ የሚወሰነው የተነደፈውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሚደረገው ፍላጎት ነው (Knott and Mutunga 1995:163-166):: ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ሁለት ነጥቦችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል (Buny 1995:143)::

- የሚመረጠው የቋንቋ ማስተማር አቀራረብ ተማሪዎች በዓላማው የተጠቆመውን የባህርይ ገጽታ ያመጡ ዘንድ የልምምድ እድል የሚሰጣቸው ሊሆን ይገባል::
- ተማሪዎች አዲስ ያገኙትን የባህርይ ገጽታ ይዘውት ይቀጥሉ ዘንድ ልምምዱ እርካታ የሚያገኙበት መሆን ይኖርበታል::
- ከእነዚህ በተጨማሪም ይላሉ Buny በአቀራረቡ መረጣ ጊዜ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ሌሎች ሁኔታዎች መኖራቸው መዘንጋት የለበትም:: እነዚህም ሁኔታዎች
- በአንድ ክፍል ውስጥ ይኖራል ተብሎ የሚገመተው የተማሪዎች ብዛት፣
- ለመማር ማስተማሩ የተመደበው ጊዜና የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ፣
- በትምህርት ቤቱ ሊገኙ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ ሚዲያዎች፣
- በአቀራረቡ ተጠቅመው ሊያስተምሩ የሚችሉ መምህራን መኖር የሚሉት ናቸው::

በአጠቃላይ ሁሉም አቀራረቦች የራሳቸው የሆኑ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ያሏቸው ስለሆነ አንዱን ብቻ መዞ አውጥቶ ወደተግባር ከመግባት ይልቅ እየቀላቀሉ መጠቀሙ ጠቀሜታ እንዳለው Knott and Mutunga (1995:164) ይመክራሉ::

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡት አቀራረቦች በተመለከተ የተሻለው ይህ ብቻ ነው ብሎ ከመወሰኑ በፊት የሚከተሉት ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ግንዛቤ ሊያገባቸው እንደሚገባ የሚያስረዱት ደግሞ Stern (1994:471-472) ናቸው:: ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ያሏቸውም የሚከተሉት ናቸው::

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

- ተማሪው ቋንቋውን ለመማር ይበጀዋል ተብሎ በተመረጠለት የማስተማር ዘዴ ተጠቅሞ ከተማረ በኋላ የሀገሪቱን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ያሳካ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል::
- የተመረጠው ዘዴ በቋንቋ ትምህርቱ አቀባበል ላይ ምቹና ቀልጣፋ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል::
- ቋንቋውን የሚያስተምሩትን መምህራን በአዲስ አሰራር ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ ከቀደመው የተሻለ አቀራረብን በመያዝ ትምህርቱን እንዲያቀርቡ የሚረዱ መሆን አለባቸው በማለት ያስረዳሉ:: አክለውም እስካሁን ድረስ ቋንቋን ለማስረማር በየዘመኑ /በየጊዜው/ የፈለቁት አቀራረቦችና ዘዴዎች (Approaches and Methods) እንዳቅማቸውና እንዘመኑ ሁኔታ ከላይ የተጠቀሱትን ጉዳዮች አንጻራዊ በሆነ መልኩ እያሟሉ መጥተዋል::

Grant (1989:34) ስለ ንግግር ትምህርት አቀራረበ ሲገልጹ የአብዛኞቹ የቋንቋ ተማሪዎች የንግግር ችሎታ ከፍ ያደርጋል ተብሎ የተሰጠውን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ተማሪዎች ሐሳባቸውን መግለጽ የማይችሉ ሆነው ይገኛሉ:: ይህ የሚሆንበት ምክንያት የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረቡ መምህሩን እንጅ ተማሪውን ያማከለ ስላልነበረ ነው:: ተማሪው በሰኮንድ ለሚቆጠሩ ጊዜያት እንኳ ቢሆን ለመናገር ዕድል ሳያገኝ መምህሩ ብቻ ተናግሮ ጊዜው ይጠናቀቃል:: ከዚህ በኋላ ተማሪው የንግግር ችሎታው ሳይዳብር ይቀራል፤ ካሉ በኋላ ይህንን ሁኔታ ለማስወገድ የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ መለወጥ ይኖርበታል ይላሉ:: አቀራረቡም እንዲለወጥና ተማሪውን ያማከለ እንዲሆን የሚከተሉትን ሶስት የአቀራረብ መርሆዎች መከተል እንደሚገባ ያስገነዝባሉ

- ተማሪ ተኮር የሆነና ተማሪው የበለጠውን ጊዜ እንዲናገር የሚያበረታታ መሆን ይኖርበታል፤
- በቋንቋ ሥርዓት /ህግ/ ላይ ብቻ ሳይመሠረት የቋንቋ አጠቃቀሙን ከማህበራዊ ዓውዱ ጋር የሚያቀርብ መሆን ይገባዋል፤
- የተማሪውን ፍላጎትና ስሜት ማነሳሳት የሚችሉ አሳታፊ የሆኑ ዘርፈ ብዙ ልምምዶችን፣ ድግግሞሾችን፣ አጠቃቀሞችን፣ ወዘተ. ይዘው መገኘት ይኖርባቸዋል ይላሉ::

የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚቀርብ ትምህርት ግቡን እንዲመታ የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችን /ብልሃቶችን/ የመማሪያ መጻሕፍቱ አካተው መያዝ እንዳለባቸው የሚገልጹት ደግሞ በድሉ /1996/ ናቸው:: እንደእሳቸው አገላለጽ የመማሪያ መጻሕፍቱ እንደተማሪዎች የክፍል

ደረጃ፣ እድሜና ፍላጎት ተስማሚ የሆኑ የአቀራረብ ዓይነቶችን አካተው መቅረብ ይኖርባቸዋል:: የአቀራረበ ብልሀቶቹም:-

- በጭውውት ማስተማር:- ጭውውት የንግግር ክሂልን ለማዳበር ተመራጭነት ያለው ዘዴ ነው:: ተማሪዎች እንደየክፍል ደረጃቸው በተመረጡ ቅንጫቢዎች በመጠቀም የሚያካሂዱት የጭውውት ተግባር ዕውነተኛ የንግግር ዓውድን ይፈጥራል::
- ቃላዊ ሪፖርት በማቅረብ:- ተማሪዎች ያነበቡትን፣ ያዳመጡትንና ያዩትን ጉዳይ በራሳቸው የቃላት አጠቃቀምና የአገላለጽ ችሎታ በንግግር የሚያቀርቡበት ነው::
- ቃለመጠይቅ በማድረግ:- ተማሪዎች አንድን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክተው በቃለ መጠይቅ አማካኝነት ከሰዎች መረጃ የሚሰበስቡበትና ያገኙትን መረጃ አቀናብረው በክፍል ውስጥ በንግግር የሚያቀርቡበት ነው:: ይህንን ተግባር መማር ከመጀመራቸው አስቀድሞ ስለቃለመጠይቅ አዘገጃጀትና አቀራረብ እንደየደረጃው የሚመጠን ዕውቀት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ማስታወሻን /መመሪያን/ መማሪያ መጽሐፉ መያዝ ይገባዋል::
- በሥዕል አማካኝነት:- በሚቀርበው ሥዕል መሠረት ተማሪዎች እርሰ በርስ እንዲወያዩና የግል አመለካከታቸውን እንዲገልጹ ለማድረግ የሚቻልበት የአቀራረብ ብልሃት ነው::
- በጥያቄ አማካኝነት:- የተማሪዎችን ዳራዊ ዕውቀት ወይም ለትምህርቱ የተመረጠውን ቅንጫቢ መሠረት በማድረግ የተለያዩ አነጋጋሪ ጥያቄዎችን በማቅረብ እንዲናገሩ የሚያስችል ነው:: ጥያቄዎች መፍትሄ የሚሹ፣ የሚያከራክሩና ምናባዊ ጉልበትን (power of imagination) የሚጠይቁ ሊሆኑ ይችላሉ /በድሉ 1996:65-68/::

የንግግር ክሂልንም ሆነ ሌሎችን የቋንቋ ክሂሎች ለማስተማር አንድ የተወሰነ አቀራረብን መከተል አስፈላጊ ላይሆን ይችላል የሚሉት ደግሞ Richards (1994:10-11) ናቸው:: የምናስተምርበትን ዘዴ ወይም የትምህርቱን አቀራረብ የሚወስነው ተማሪው ቋንቋን የሚማርበት ዓላማ ነው:: ክሂሉን እንዲማር የሚፈልገው ለምን ያህል ጊዜ? እስከምን ደረጃ? ለምን ግልጋሎት? የሚሉት ጥያቄዎች መልስ ከታወቀ በኋላ የትምህርቱ አቀራረብ ምን መምሰል እንደለበት መወሰን ይቻላል ይላሉ::

ከዚህ አንጻር በዚህ ጥናት የሚታዩት የመማሪያ መጻሕፍት ለአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው እርከን አማርኛን ለመማር የቀረቡ ናቸው:: በእነዚህ መጻሕፍት የተማረ /ተማሪ/ በንግግር አማካኝነት ሐሳቡን መግለጽ የሚችል፣ በውይይቶችና ክርክሮች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን፣ ወዘተ. ይጠበቃል:: የቋንቋው ተናጋሪ ኅብረተሰብ ቋንቋውን ለንግግር ተግባቦት ሲገለገልበት ከባህሉ፣ ከእምነቱ፣ ከእድሜው፣ ከደረጃው፣ ወዘተ. አንጻር እንዴት

እንደሚጠቀምበት ለይቶ በማወቅ በትክክል እንድጠቀምበት ከትምህርቱ በኋላ ይጠበቃል /አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ 1996:5/::

በመማሪያ መጽሐፉ የሚገለገሉት ተማሪዎች አፋቸውን የፈቱት በአማርኛ እንደሆነ ይታሰባል:: በተለይ ጥናቱ የሚካሄድባቸው ሦስት ወረዳዎች /ሀብሩ፣ ቆቦና ግዳን/ አማርኛ የሚነገርባቸው አካባቢዎች ናቸው:: ተማሪዎችም የሚማሩት አፍ በፈቱበት ቋንቋ ነው:: በዚህ አፍ በፈቱበት ቋንቋ የንግግር ክሂል ትምህርት ሲቀርብላቸው ዓላማው ምንድን ነው? የሚለውን ስናነሳ የአካባቢውን ባህልና ወግ በጠበቀ ሁኔታ የንግግር ተግባርን እንዲያከናውኑ ለማድረግ ነው:: ከዚህም አልፎ መደበኛ የሆነውን የቋንቋውን አጠቃቀም /አነጋገር/ እንዲከተሉ ለማስቻል ነው:: ከዚህ አንጻር ተማሪዎቹ የቋንቋውን መዋቅርና በቋንቋው መግባባትን በተሻለ ሁኔታ እንዲለምዱ ይፈለጋል ማለት ነው:: ይህንን ዓላማ ለማሳካት ደግሞ አንድ ወጥ የሆነ አቀራረብን ወይም ዘዴን መምረጥ የለብንም:: ከሁሉም በተውጣጣው ዘዴ በመጠቀም መጻሕፍቱን ማዘጋጀት የሚጠበቅ ይሆናል::

ክፍል ሶስት

የአጠናን ዘዴ

3.1. የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ ዓላማው አድርጎ የተነሳው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው እርከን ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት እና ለመደበኛው ትምህርት መርሐ ግብር በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ንጽጽራዊ ጥናት በማድረግ የንግግር ክሂል ትምህርትን ለመማር ያላቸውን ጠንካራና ደካማ ጎነ ማሳየት፣ የተሻውንና ደካማ አዘገጃጀት የተከተለውን በመለየት ደካማ አዘገጃጀት የተከተለው ከተሻለው ልምድ እንዲያገኝ ማስቻል ነው::

በዚህ መሠረት ጥናቱ ንጽጽራዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም መረጃዎችን በመተንተን ንጽጽራቸውን ይገልፃል:: የተደረሰበትንም ማጠቃለያ ያቀርባል::

3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት የተመረጠው አንደኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሰነድ ምርመራ (Document Analysis) ነው:: ከ1-4ኛ ክፍልና ከደረጃ 1-3 ለማስተማሪያነት የተዘጋጁት መጻሕፈት ዋናዎቹ ሰነዶች ናቸው:: ለእነዚሁ የክፍል ደረጃዎች የተዘጋጁተ መርሐ-ትምህርቶችም እንዲሁ ለመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግለዋል::

በሁለተኛ ደረጃ የመረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ የሚያገለግለው የጽሑፍ መጠይቅ ነው:: የጽሑፍ መጠይቁ የቀረበው መጻሕፍቱን ላዘጋጁ ባለሙያዎች፣ ትምህርቱን በማስተማር ላይ ለሚገኙ አመቻቾችና መምህራን ነው::

ለመጻሕፍቱ ሰባት አዘጋጆች መጠይቆችን በማቅረብ በመማሪያ መጻሕፍቱ ዝግጅት ጊዜ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች ምን ያህል ከግምት ውስጥ ገብተው እንደቀረቡ ሰባቱም ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጓል::

በስድስት መደበኛና በስድስት አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ትምህርት ተቋማት ለሚያስተምሩ 69 አመቻቾችና መምህራን መማሪያ መጻሕፍቱ የንግግር ክሂልን ለማስተማር ምን ያህል እንደጠቀሟቸው ከተማሪዎች ዳራ አንጻር ታይተው የተዘጋጁ ስለመሆናቸው ወይም አለመሆናቸው አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ተደርጓል::

3.3. የናሙና አወሳሰድ

ጥናቱ የሚያተኩርባቸው የመማሪያ መጻሕፍት አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ ሥር በሚገኙ በሁሉም የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ ነው:: በሰሜን ወሎ ዞን ውስጥ በሚገኙ ሦስት ወረዳዎች ላይ ጥናቱ እንዲያተኩር የተደረገበት ምክንያት የዓላማ ተኮር ንሞና (Purposeful) መሠረት በማድረግ ነው:: አላማ ተኮር ንሞና የተመረጠበት ምክንያቶችም:-

- አሁን የሚሠራበት ትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ወዲህ በአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ ስር ከሚገኙት ዞኖች ውስጥ በተደራጀ መልኩ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የተጀመረበት ዞን ሰሜን ወሎ ነው::
- ከዚህ ዞን ውስጥ ሀብሩና ቆቦ በአንድ ጊዜ፣ ግዳን ደግሞ ከሁለቱ ወረዳዎች ቀጥሎ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የተካሄደባቸው ናቸው::
- ስለዚህ በእነዚህ ወረዳዎች ረዘም ላለ ጊዜ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን ሲያስተምሩ የቆዩ አመቻቾች ይገኛሉ ብሎ አጥኝው ስለሚያምን መርጧቸዋል::
- አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች የተመረጡት ለትራንስፖርት አመቺ የሆኑንና በቅርብ ሊገኙ የሚችሉትን ሲሆን መደበኛ ትምህርት ቤቶቹም በእነዚህ አማራጮች አካባቢ የሚገኙትን ነው::
- መምህራኑና አመቻቾቹ በተመረጡት ስድስት የመደበኛና የአማራጭ ትምህርት ተቋማት የሚያስተምሩትን የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያውን እርከን በሙሉ ነው::

3.4. የመረጃዎች አተናተን ዘዴ

ከመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የንግግር ክሂል አዘገጃጀት ምን እንደሚመስል በንጽጽር ታይቷል:: በእያንዳንዱ ለመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ከንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አዘገጃጀት አንጻር ተደሷል:: የንግግር ትምህርት ይዘት አዘገጃጀትን መርህ ተከትለው መቅረብ አለ መቅረባቸውም አብሮ ተቃዕቷል::

እያንዳንዱ የክፍል ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በተናጠል ከታየ በኋላ ተመሳሳይ የክፍል ደረጃዎች ለንጽጽር ቀርበዋል:: አንደኛና ሁለተኛ ክፍሎች ከደረጃ አንድ፣ ሶስተኛ ክፍል ከደረጃ ሁለት፣ አራተኛ ክፍል ከደረጃ ሶስት ጋር ተነጻጽረዋል:: በንጽጽሩ ወቅት የተሻለ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አዘገጃጀት የተከተለው ተለይቶ ወጥቷል::

AU LIBRARY

ከመጻሕፍቱ አዘጋጆችና ከመምህራን /አመቻቾች/ የተሰበሰበው መረጃ ከመማሪያ መጻሕፍቱ ዝግጅት አንጻር ደጋፊ ሆኖ ቀርቧል:: በየትኛው የክፍል ደረጃና መርሐ ግብር መጻሕፍቱ ሲዘጋጁ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች ትኩረት እንደተሰጠባቸውና ለማስተማር አመቺ እንደሆኑ አስተያየታቸውን እንዲገልጹ ተደርጓል::

ከእነዚህ ከሁለት አቅጣጫዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች በማጣመር ንጽጽሩ ተካሂዷል:: ቀጥሎም የተሻለና ደካማ አዘገጃጀት ያላቸው የመማሪያ መጻህፍት ተለይተዋል::

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ክፍል አራት

የጥናቱ ውጤት ትንተናና ንጽጽር

በዚህ ጥናት ትንተና የተደረገባቸው መማሪያ መጻሕፍት መጀመሪያ እያንዳንዳቸው ያላቸውን የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀት አቀራረብ ተፈትሿል:: በመቀጠል የአማራጩና የመደበኛው መማሪያ መጻሕፍት በንጽጽር ተተንትነዋልል::

4.1. የደረጃ አንድ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥስት ትምህርት ቢሮ ሥር ለሚገኙ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች (Alternative Basic Education center/ የተዘጋጀውን የደረጃ አንድ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ከማየታችን በፊት የመማሪያ መጽሐፉንና የመርሐ ትምህርቱን አጠቃላይ ገጽታዎች እናያለን::

"የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አማርኛ ደረጃ 1 የመማሪያ መጽሐፍ" በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንሥስት ትምህርት ቢሮ እና በኖርዌና ዴንማርክ ሕጻናት አድን ድርጅት ትብብር እንዲዘጋጅ የተደረገ ሲሆን አዘጋጆቹ የደሴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህራን ናቸው:: መጽሐፉ 198 ገጾችና በእነዚህ ገጾች ውስጥ የተካተቱ 25 ርዕሶች ይዟል::

ቀጥሎ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመስርቶ መዘጋጀቱን፣ በውስጡ ተዘጋጅተው የቀረቡት የንግግር ክሂል ማለማመጃ ጥያቄዎች ከሌሎቹ የቋንቋው ክሂሎች አንጻር ሲታዩ በበቂ መጠን ተዘጋጅተው መቅረባቸውን፣ ተዘጋጅተው የቀረቡት መለማመጃዎች ሳቢነትና ማራኪነት ባለው መልኩ የተማሪዎችን፣ የመምህራንንና የትምህርት መስጫ ተቋማቱን ሁኔታ አገናዝበው እንዲሁም ተከታታይነታቸውንና ተለጣጣቂነታቸውን ጠብቀው መቅረባቸውን፣ የንግግርን ንዑሳን ክሂሎች ለማዳበር በሚያስችል ሁኔታ መደራጃታቸውን እንፈትሻለን::

4.1.1. የደረጃ አንድ መማሪያ መጽሐፍ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ ስለመቅረቡ

ለደረጃ አንድም ሆነ ለደረጃ 2 እና 3 የተዘጋጁት መርሐ ትምህርቶች በየትኛው ዓመተ ምህረት እንደተዘጋጁ የሚገልጽ የላቸውም:: ይሁን እንጂ በሁሉም መርሐ ትምህርቶች መግቢያ ላይ የመርሐ ትምህርቱ መሻሻል መሠረት ያደረገው በ1996 ዓ.ም በሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ኢንስቲትዩት ተሻሽሎ በተዘጋጀው የመደበኛው /ከ1-4ኛ ክፍሎች/ መርሐ ትምህርት በ1993 ዓ.ም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮና በኖርዌ ህፃናት አድን ድርጅት

ትብብር በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ላይ ነው ይላሉ:: ከዚህ መረዳት እንደሚቻው የመርሐ ትምህርቶቹ ዝግጅት ከ1996 ዓ.ም ወዲህ መሆኑን ነው:: መርሐ ትምህርቱ 34 ገጾች ያሉት ሲሆን በእነዚህ ገጾች የተካተቱ 21 ይዘቶች ይገኛሉ::

እነዚህን ይዘቶች ለማስተማር 198 ክፍለ ጊዜያት ተመድበዋል:: ስለመርሐ ትምህርቱ ይህንን ያህል ካልን መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ መቅረብ አለመቅረቡን ወደምንፈትሽበት እንሸጋገር::

ሠንጠረዥ አንድ:- የንግግር ክሂልን ለማስተማር በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ ተዘጋጅተው የቀረቡ ይዘቶች

ተ.ቁ	የቋንቋ ትምህርት ክፍል	ዝርዝር ዓላማዎች	ይዘት	ክፍለ ጊዜ	ገጽ	ምርመራ
1	ማዳመጥና ንግግር	የተለያየ ጊዜና ሁኔታን ያገናዘበ የሰላምታ ልውውጥ ያደርጋሉ	የሰላምታ ልውውጥ	4	17-18	4 ለንግግር ክሂል
2	ማዳመጥ፣ መናገር ማንበብ	የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቀው የሚፈልጉትን ይገልጻሉ	ተጠያቃዊ አስተሳሰብ	6	26-28	2 ለንግግር ክሂል
3	ማዳመጥና ንግግር	በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ጭውውት ያደርጋሉ	ጭውውት	7	33	5 ለንግግር ክሂል
	ድምር	-	-	17	-	11 ለንግግር ክሂል

በሠንጠረዡ እንደተገለጸው የንግግር ክሂል ለብቻው ተለይቶ ክፍለ ጊዜም ሆነ ይዘት አልቀረበለትም:: ይሁን እንጂ ለንግግር ክፍለ ጊዜ የዋለውን ለይቶ ለማውጣት የመማርጠ ማስተማሩን ክንውን በመመልከት በየክሂሎቹ የተደረገውን ክንዋኔ በማየት ለመለየት ተሞክሯል::

እነዚህኑ በመርሐ ትምህርቱ የንግግር ክሂልን ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ መኖር አለመኖራቸውን ስንፈትሽ

ሀ. "የሰላምታ ልውውጥ" የሚለው ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ ከገጽ 110-112 ላይ ይገኛል:: በእነዚህ ገፆች ሰዎች ሰላምታን እንዴት እንደሚለዋወጡ በሥዕል ከመገለጹም በተጨማሪ የንግግር መለማመጃ ጥያቄዎችም ቀርበውበታል::

ለምሳሌ:- "ቤተሰቦቻችሁ ወይም በአካቢያችሁ የምታገኙዋቸውን ሰዎች ጧት፣ ቀንና ማታ ሲገናኙ ምን ብለው ሰላምታ እንደሚለዋወጡና እንደሚሰነባበቱ ጠይቃችሁ አስረዱ::

ሀ. ጠዋት

ለ. ቀን

ሐ. ማታ" /ገጽ 111 መልመጃ 1/

ለ. "ተጠያቃዊ አስተሳሰብ /የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን መግለጽና ማወዳደር/" የሚለው ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ ከገጽ 168-174 ይገኛል:: ተማሪዎች የክንዋኔዎችንና የጊዜያት ቅደም ተከተል ጠብቀው እንዲናገሩ በሚያለማምዱ መልኩ ቀርበዋል::

ምሳሌ:- "ሥዕሎችን አይታችሁ ጥያቄዎችን መልሱ:: አዜብ ምን እያደረገች ነው? በቅደም ተከተል ተናገሩ::" /ገጽ 169 መልመጃ አንድ ፊደል ሀ/

ሐ. "ጭውውት" የሚለው ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ ከገጽ 193-198 ተዘጋጅቶ ቀርቧል:: በዚህ "ጭውውት" በሚለው ርዕስ በመርሐ ትምህርቱ ላይ እንደተገለጸው የቀረቡት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ማዳመጥና ንግግር ብቻ ሳይሆኑ ንባብና ሰዋስውም ጭምር ናቸው:: ለንግግር ክሂል መዳበር የሚረዱትና ተማሪዎችን ንግግር እንዲለማመዱ የሚያደርጉት የሚገኙት ገጽ 198 ላይ ነው::

ለምሳሌ:- በተለያዩ ጉዳዮች ከጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን ጭውውት አዘጋጅታችሁ ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ:: /ገጽ 198 መልመጃ 2 ፊደል ሠ/

በእነዚህና በሌሎችም በመጽሐፉ ውስጥ በተጠቀሱ መረጃዎች መሠረት "የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አማርኛ ደረጃ 1 የመማሪያ መጽሐፍ" በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል::

4.1.2. የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች በበቂ መጠን ተዘጋጅተው ስለመቅረባቸው

የተማሪዎችን የንግግር ችሎ ለማዳበር የሚያስችሉ መለማመጃዎች በምን ያህል ደረጃ ተዘጋጅተው እንደቀረቡ ለማየት እንዲቻል በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተዘጋጅተው የቀረቡትን ሌሎችን ክሂሎች የትምህርት ይዘቶች መለማመጃዎችና የንግግር ክሂልን መለማመጃዎች ከሌሎቹ ጋር በማጻጸር ደረጃቸውን መለየት ነው:: ለዚህ ይረዳ ዘንድ የቋንቋውን ትምህርት ይዘቶች /ክፍሎች/ መለማመጃዎች በሠንጠረዥ አውጥቶ ማሳየቱ ይጠቅማል::

ሠንጠረዥ ሁለት:- በደረጃ 1 የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ክፍሎች መለማመጃ ጥያቄዎች መጠን

ተ.ቁ	የመለማመጃ ትምህርት ክፍል /ክሂል/	የጥያቄ ብዛት	ከመቶኛ የሚኖራቸው ድርሻ	የትኩረት ደረጃው	ምርመራ
1	ማዳመጥ	31	3.68%	5ኛ	
2	ንግግር	36	4.27%	4ኛ	
3	ንባብ	301	35.7%	1ኛ	
4	ጽሕፈት	234	27.76%	3ኛ	
5	ሰዋስው	241	28.59%	2ኛ	
6	ሥነ ጽሑፍ	-	-	-	የለውም
7	ጠቅላላ	843	100%		

ከዚህ በላይ በቀረበው ሠንጠረዥ መሠረት ለንግግር ትምህርት የቀረቡት መለማመጃዎች 36 ናቸው:: ይህም ጠቅላላ ከቀረቡት 843 የመለማመጃ ጥያቄዎች ከመቶ እጅ 4.27/4.27%/ ያህሉን ይይዛሉ:: የተሰጠው የትኩረት ደረጃም 4ኛ /ዝቅተኛ/ ነው:: ለሁሉም የቋንቋው ትምህርት ክፍሎች እኩል ትኩት ቢሰጥ ኖሮ አማካይ የጥያቄዎች ብዛት 140.5 ወይም 16.67% ይሆን ነበር:: የንግግር ክሂል መለማመጃዎችን ስንመለከት ከአማካይ የጥያቄዎች ብዛትም ሆነ ከመቶ እጅ ከሚኖረው ድርሻ በጣም ዝቅ ያለ ነው::

ስለዚህ በቂ የንግግር መለማመጃ ጥያቄዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተዘጋጅተው አለመቅረባቸውን መገንዘብ ይቻላል:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ አንድ "ሀ"ን ይመልከቱ/::

4.1.3. የትምህርት ይዘቶቹ ሳቢና ማራኪ ስለመሆናቸው

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር ተዘጋጅተው የቀረቡት መለማመጃዎች ከሌላዎቹ የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች አንፃር ሲታዩ በጣም አነስተኛ መሆናቸውን ለመገንዘብ ተችሏል:: በመቀጠል እነዚሁ በአነስተኛ መጠን ያላቸው መለማመጃዎች ተመርጠውና ተዘጋጅተው ሲቀርቡ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት /ንግግርን የመማር/ ለመቀስቀስ በሚችል ሁኔታ ሳቢና ማራኪ ሆነው ቀርበዋል? የተማሪዎችን የክፍል ደረጃና እድሜ ያገናዘቡ ናቸው? ትምህርቱን የሚያስተምሩት መምህራን /አመቻቾች/ ለማስተማር የሚያስችላቸው ሁኔታ አለ? ይህንን ትምህርት በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች ተግባራዊ ለማድረግ ይቻላል? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በማንሳት ምላሽ እንዲያገኙ ተደርጓል::

ለንግግር ክሂሎች ማስተማሪያነት ተመርጠውና ተዘጋጅተው የቀረቡትን መለማመጃዎች ስንመለከት በጭውውት፣ በተረት፣ በውይይት፣ በሚና ጨዋታዎች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎችን በማየት፣ ወዘተ... ተማሪዎች የንግግር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚያደርጉ ናቸው::

ምሳሌ:- 1. "በሚከተለው ሥዕል የፀሐይዋን አቀማመጥ መሠረት አድርጋችሁ ለክፍት ቦታው የሚሆነውን ሰላምታ በቃላችሁ ተናገሩ::" /ገጽ 111 መልመጃ ሁለት/

2. "ከክፍሉ ተማሪዎች ውስጥ አምስት ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው ፊት ለፊት በመሆን የአምስቱን ጣቶች ንግግር በሚና ጨዋታ ተናገሩ::" /ገጽ 67 መልመጃ አስር/

እነዚህ ምሳሌዎችና ሌሎቹንም በመማሪያ መጽሐፉ ተመርጠው የቀረቡትን የንግግር ችሎታን ለማዳበር የሚረዱ መለማመጃዎች መሠረት በማድረግ ምንም እንኳ ብዛታቸው አናሳ ቢሆንም የተማሪዎችን የመናገር ፍላጎት የሚያነሳሱ ከዕድሜያቸውና ከክፍል ደረጃዎቻቸው ጋር ሊሄድ የሚችሉ ናቸው::

ከአመቻቾቹም ዳራ አንጻር ሲታይ ከ10ኛ ወይም ከ12ኛ ክፍል በኋላ የአንድ ዓመት የማስተማር ሥልጠና የወሰዱ በመሆናቸው ትምህርቱን ለማስተማር አይቸገሩም::

ከትምህርት ተቋማቱም አንጻር እነዚህ የንግግር ማለማመጃ ይዘቶች ብዙ ወጪን የማይጠየቁ በመሆናቸው ተግባራዊ ለማድግ ችግር አይገጥማቸውም:: በአነስተኛ መጠንም ቢሆንም ንዑሳን የንግግር ክሂሎችን ከማዳበር አንጻር /ከሰው ፊት ቆሞ መናገር፤ አለመፍራት፣ አለማፈር፣ ሀሳብን በትክክል መግለጽ፣ ወዘተ./ ትምህርቱ በጨዋታ፣ በተረት፣ በቡድን ውይይት፣ የቀረበ በመሆኑ ውጤታማ ይመስላል::

4.1.4. የይዘቶቹ አቀራረብ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያለው ስለመሆኑ

"የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አማርኛ መማሪያ የደረጃ 1 መጽሐፍ" ቀድሞት የሚቀርብ የክፍል ደረጃ ስለሌለ ካለፈው የክፍል ደረጃ ተከታታይና ተለጣጣቂ ሆኖ መምጣቱን መናገር አይቻልም:: በራሱ በመጽሐፉ ውስጥ ያለው የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተያያዥነትና ከቀላል ወደ ከባድ የመደራጀት ሁኔታ ግን ጥሩ አቀራረብን የተከተለ ነው:: የንግግር ክሂል ትምህርት መቅረብ ከጀመረበት ከገጽ 82 ጀምሮ የመጨረሻው የንግግር መለማመጃ እስከ ሚቀርብበት ገጽ 198 ድረስ ያሉት ከቀላሉ ወደ ተወሳሰበውና ከበድ ወደሚለው መለማመጃ በመሸጋገር ቀርበዋል::

ምሳሌ:- "ተረት" /ገጽ 163፣ 167፣ 192፣ 198/

"ጭውውት" /ገጽ 167፣ 138

"ሥዕልን አይቶ መናገር" /ገጽ 169፣ 175፣ 176፣ 191/

በቀጣዩ የክፍል ደረጃ ማለትም በደረጃ ሁለት መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ እነዚህ መለማመጃዎች በተመሳሳይ መንገድ ቀርበው ይገኛሉ::

4.1.5. የአዘጋጆችና ተተኳሪ አመቻቾች የጽሑፍ መጠይቅ መልሶች

ደረጃ አንድ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍን ያዘጋጁት በደሴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅና በወሎ ዩኒቨርሲቲ በማስተማር ላይ የሚገኙ 4 መምህራን ናቸው:: አመቻቾቹም በሰሜን ወሎ ዞን በ3 ወረዳዎች /ሀብሩ፣ ቆቦና ግዳን/ በሚገኙ 5 አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች በማስተማር ላይ ያሉ ናቸው:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ አራት "ሀ" እና አባሪ አምስት "ለ"ን ይመልከቱ/::

የመጽሐፉን የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ በተመለከተ ለቀረቡላቸው የጽሑፍ መጠይቆች የሚከተሉትን መልሶች ሰጥተዋል::

ሀ. የአዘጋጆች መልስ

1. የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶችን አመራረጥ በተመለከተ፤ የተመረጡት ይዘቶች የተማሪዎችን፣ የአመቻቾችንና የትምህርት ተቋማትን ሁኔታ ያገናዘቡ እንደሆኑ ገልጸዋል:: የተማሪዎችን እድሜ፣ ክፍል ደረጃ፣ የአመቻቾችን የሥልጠና ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመረጡ መሆናቸውን አረጋግጠዋል::
2. አዘገጋጃጀቱን በተመለከተ፤ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች ሲዘጋጁ በመርሐ ትምህረቱ ላይ ተመሥርተው በመማሪያ መጽሐፉ አለመዘጋጀታቸውን፣ ከመርሐ ትምህርቱ ውጪ የተዘጋጁትም ቢሆኑ በበቂ መጠን አለመቅረባቸውን ገልጸዋል
3. አቀራረቡን በተመለከተ፤ የተዘጋጁ የንግግር ክሂል መለማመጃ ይዘቶች አነስተኛ ቢሆኑም የተማሪዎችን የንግግር ትምህርት የመማር ፍላጎትን በሚያነሳሳ መልኩ የቀረቡ፣ ሳቢና ማራኪነት ያለውን አቀራረብ የተከተሉ እንደሆኑ በመልሶቻቸው ላይ አሳይተዋል::

ለ. የአመቻቾች መልስ

የአመቻቾቹንም መልስ ስንመለከት ከአዘጋጆቹ የተለየ አይደለም:: መማሪያ መጽሐፉ ሲዘጋጅ ለንግግር ክሂል ትምህርት የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ እንደሆነ፣ የቀረቡት ይዘቶች /ለመለማመጃዎች/ አነስተኛ ቢሆኑም የተማሪዎችን ንዑሳን የንግግር ክሂሎች ለማዳበር የሚችሉ እንደሆኑ፤ የተማሪዎችን፣ የአመቻቾችንና የትምህርት ተቋማትን ሁኔታ ያገናዘቡ እንደሆኑ ገልጸዋል::

ሁለቱም /አዘጋጆቹና አመቻቾቹ/ የሰጡት መልስ በመማሪያ መጽሐፉ ግምገማ የተገኘውን ውጤት የሚያጠናክር ነው:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ ሶስት ሀ እና ለ ን ይመልከቱ/::

4.2. የደረጃ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ ስር በሚገኙ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች በደረጃ ሁለት አማርኛ ቋንቋን ለማስተማ የተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂልን ለማስተማር የይዘት አመራረጡን፣ አዘገጃጀቱንና አቀራረቡን ከማየታችን በፊት የመማሪያ መጽሐፉንና የመርሐ ትምህርቱን አጠቃላይ ገጽታዎች እንመለከታለን::

በደረጃ ሁለት ለሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማስተማሪያነት የሚያገለግለው መጽሐፍ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮና በኖርዌና ዴንማርክ ሕጻናት

አድን ድርጅት ትብብር በደሴ መምህራን ኮሌጅ መምህራን በ1998 ዓ.ም የተዘጋጀ ነው:: በውስጡ 150 ገጾችና በእንዚህ ገጾች የተካተቱ 28 ይዘቶች አሉት::

መርሐ ትህምርቱ 28 ገጾች አሉት:: በእነዚህ ገጾች 6ቱን የቋንቋው ትምህርት ክሂሎች /ማዳመጥ፣ ንግግር፣ ማንበብ፣ ጽሕፈት፣ ሰዋስው እና ሥነ ጽሑፍ/ 28 ይዘቶችና ዓላማዎች ከመማር ማስተማር ክንዋኔዎች ጋር ይገኛሉ:: ያዘጋጀው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ መሆኑን ከሽፋኑ ላይ ከተጻፈው ጽሑፍ መረዳት የሚቻል ቢሆንም በየትኛው ዓመተ ምህረት እንደታተመ የሚገልጽ መረጃ የለውም:: ይሁን እንጂ ሲዘጋጅ 1996 ዓ.ም. የተዘጋጀውን የመደበኛውን ከ1-4ኛ ክፍል መርሐ ትምህርትና በ1993 ዓ.ም የተዘጋጀውን የዚህኑ ደረጃ /የደረጃ ሁለት/ መርሐ ትምህርት መሠረት እንዳደረገ በመግቢያው ላይ ተገልጿል:: ይህን ፍንጭ በመያዝ ዝግጅቱ የተደረገው ከ1996 ዓ.ም ወዲህ ባሉት ዓመታት ውስጥ እንደሆነ መረዳት ይቻላል::

ከዚህ በመቀጠል የደረጃ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት አመራረጡን፣ አደረጃጀቱንና አቀራረቡን ለመፈተሽ እንዲያስችለን መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ ተዘጋጅቷል? በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥስ የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚያስችሉ በቂ መለማመጃዎች አሉ? የንግግር ክሂልን ለማዳበር የተዘጋጁት መለማመጃዎች ሳቢነትና ማራኪነት አላቸው? የተማሪዎችን የመምህራንና የትምህርት ቤቶችን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገቡ ናቸው? ወዘተ. የሚሉትን ጥያቄዎች መልስ ወደምናገኝበት የጥናቱ ክፍል እናመራለን::

4.2.1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ተመሥርቶ ስለመዘጋጀቱ

መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ተመሥርቶ መዘጋጀቱን ወይም አለመዘጋጀቱን ለመፈተሽ በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ የንግግር ክሂልን ለማዳበር የቀረቡትን ይዘቶች ከዓላማዎቻቸውና ከተመደበላቸው ክፍለ ጊዜያት ጋር ለይተን በማውጣት ማየት ይኖርብናል:: ይህንንም በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ውስጥ እንመለከታለን

ሠንረጠዥ ሦስት ንግግርን ለማስተማር በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ ተዘጋጅተው የቀረቡ ይዘቶች

ተ. ቁ	የቋንቋ ትምህርት ክሂሎች	ዝርዝር ዓላማዎች	ይዘት	ክፍለ ጊዜ	ገጽ	ምርመራ
1	ንግግር	ገጠመኛቸውን አስመልክተው ንግግር ያደርጋሉ	ንግግር ማድረግ	6	1-2	6
2	ማዳመጥና ንግግር	በተለያየ ጉዳዮች ጭውውት ያደርጋሉ	ጭውውት	6	12	4 ክፍለ ጊዜ በንግግር
3	ንግግር	ውይይት ያካሂዳሉ	ውይይት	8	12-13	8
4	ንግግር	ስርዓቱን ጠብቀው ይከራከራሉ	ክርክር	8	15	8
5	ማዳመጥና ንግግር	ያዳመጡትን ንግግር ይዘት በራሳቸው አባባል ይገልጻሉ	የአንድን ንግግር ይዘት በራስ አባባል ማቅረብ	5	21-25	3 ክፍለ ጊዜ ለንግግር
6	ንግግርና ንባብ	- በተጠየቃዊ አስተሳሰብ ተገልግለው የተረዱትን ይገልጻሉ - ሀሳቦችን በድርጊትና በጊዜ ቅደም ተከተል ያቀርባሉ - ሁኔታዎችን ተመልክተው ነው ... ይሆናሉ:: - ... እያወዳደሩና እናያነፃፀሩ ይገልፃሉ - ... መንስኤና ውጤት ይገልፃሉ	- ተጠየቃዊ አስተሳሰብ - የደርጊትና አስተሳሰብ - ነው ... ይሆናል እያሉ መደምደም - ማወዳደርና ማነፃፀር - መንስኤና ውጤት	12		6 ክፍለ ጊዜ ለንግግር
			ድምር	45		35

በተራ ቁጥር 2፣ 5 እና 6 ላይ ንግግር ከማዳመጥና ንባብ ጋር አብሮ ቀርቧል:: በሌሎቹ ተራ ቁጥሮች ንግግር ለብቻው ተለይቶ ቀርቧል:: ተጣምረው የቀረቡትን ከመማር ማስተማሩ ክንዋኔ በመነሳት በንግግር የሚከናወኑት ተግባራት ሲለዩ ክፍለ ጊዜያቱ 35 ይሆናሉ:: በአጠቃላይ ከተመደቡት 165 ክፍለ ጊዜያት ውስጥ ለንግግር ክሂል የተመደበው 35 ክፍለ ጊዜያ ከመቶ 21.2 እጁን (21.2%) ይይዛል:: ለስድስቱ ትምህርት ክሂሎች ከተመደበው አማካዩ ድርሻ 16.67% ለንግግር ክሂል የተመደበው ክፍለ ጊዜ በ4.53% ያህል የበለጠ ሆኖ ተገኝቷል::

በዚህ መልክ በሠንጠረዡ ውስጥ ተለይተው የቀረቡትን በመርሐ ትምህርቱ የተጠቀሱ የንግግር ክሂል ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር በሚያስችል መልኩ መቅረባቸውን ተፈትሿል::

ሀ. በመርሐ ትምህርቱ ዓላማ መሠረት "ንግግር" የሚለውና ከገጽ 1-2 የቀረበው የትምህርት ክፍል ተማሪዎች የሚያውቁትን ተረት፣ የሚያስደስታቸውን ጉዳይ፣ የሚወዱትንና የሚጠሉትን በቤታቸው አገልግሎት የሚሰጡ ዕቃዎችን እንሰሳትንና ጥቅማቸውን እንዲናገሩ ማለማመድ ነው::

እነዚህን ተግባራት ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የሚያለማምዱ ጥያቄዎች በመማሪያ መጽሐፉ መኖር አለመኖራቸውን ስንቃኝ በተለያዩ የመጽሐፉ ገጻች ሠፍረው እናገኛቸዋለን:: ለማስረጃ ያህል የሚከተሉትን እንመለከት፣

ምሳሌ 1:- “በአካባቢያችሁ ካሉ አዋቂ ሰዎች /ቤተሰቦች/ ተረቶች እንዲነግሯችሁ በመጠየቅ ካዳመጣችሁት ውስጥ ደስ የሚላችሁን ተረት ለክፍሉ ተማሪዎች ተርቱላቸው::” /ገጽ 6 መልመጃ አንድ ፊደል-ሐ/

ምሳሌ 2:- “ከማርና ከወተት የትኛውን ትወዳላችሁ? ምክንያታችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ::” /ገጽ 7፣ መልመጃ አንድ፣ ፊደል -ለ፣ ተራ ቁጥር 1/

ለ. “ማዳመጣና ንግግር” በሚል በመርሐ ትምህርቱ ክፍል የቀረበው የንግግር ትምህርት ተማሪዎች በጭውውት መልክ የሰላምታ መለዋወጥ ሥርዓትንና ሌሎችንም ጭውውቶች በማድረግ ንግግርን እንደሚለማመድ የሚገልጽ ነው::

በመማሪያ መጽሐፉም ከገጽ 43 ጀምሮ እስከ ገጽ 46 ይዤው ይዘት ቀርቧል:: በእነዚህ ገጻች ውስጥ ተማሪዎች የንግግር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚረዱዋቸው የመለማመጃ ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል::

ለምሳሌ “በቡድን ተከፋፍላችሁ የሚከተሉትን ሰዎች በመምሰል በክፍላችሁ ውስጥ ጭውውት አካሂዱ

1. ሐኪም እና ታካሚ
2. ባለሱቅ እና ዕቃ ገዥ
3. መምህር እና ተማሪ” /ገጽ 45፣ መልመጃ ሁለት/

ሐ. “ንግግር”:- በዚህ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች የውይይት ሥርዓት ጠብቀው በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ውይይት እንዲያካሂዱ የሚያደርግ ነው:: በመማሪያ መጽሐፉም ከገጽ 47 እስከ ገጽ 49 ቀርቧል:: በተጠቀሱት ገጾች ውስጥ ውይይቶችን እንዲያካሂዱ የሚያደርጉ መለማመጃዎች ተዘጋጅተዋል::

ለምሳሌ “በሚከተሉት ርዕሶች በቡድን በቡድን ሆናችሁ ውይይት ካካሄዳችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን የስምምነት ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ::

1. የትምህርት ጥቅም
2. የኤች አይ ቪ ጎጂነት
3. የሕጻናት እንክብካቤ” /ገጽ 49 መልመጃ ሶስት ሀ/

መ. “ንግግር”:- በዚህኛው የንግግር ትምህርት ክፍል ተማሪዎች አንድን ሐሳብ ደጋፊ ወይም ተቃዋሚ ሆነው እንደሚከራከሩ በመርሐ ትምህርቱ በገጽ 16 ላይ ተገልጿል::

በመማሪያ መጽሐፉም ከገጽ 75 እስከ ገጽ 78 የክርክር መመሪያዎችና የመከራከሪያ ሐሳቦች የቀረቡ ሲሆን በቀረቡት ሐሳቦች ላይ ተማሪዎች እንዲከራከሩ ያደርጋል::

ምሳሌ:- "በሚከተሉት ርዕሶች ላይ በቡድንና በግል እየሆናችሁ የክርክር ሥርዓትን ጠብቃችሁ በክፍል ውስጥ ተከራከሩላቸው

1. ከድመትና ከውሻ የትኛው ለባቤቱ ጠቃሚ ነው

2. በኑሮ የምትመርጠው /ጭው/ ከተማ ነው ገጠር? ለምን?" /ገጽ 78 መልመጃ ሁለት/

ሠ. "ማዳመጥና ንግግር":- ተማሪዎች አንድን ታሪክ ወይም ተረት አዳምጠው በራሳቸው አባባል የሚተርኩበት ወይም የሚተርቱበት የትምህርት ክፍል እንደሆነ በመርሐ ትምህርቱ በገጽ 20 ላይ ተገልጿል::

በዚህ መሠረት በመማሪያ መጽሐፉ ከገድ 94 እስከ 99 ባሉት ገጾች "ያዳመጡትን ወይም ያነበቡትን በራስ አባባል ማቅረብ" በሚል ርእስ ተዘጋጅቶ ቀርቧል:: በእነዚህ ገጾች ውስጥ የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ መለማመጃዎች ቀርበዋል:: ለማስረጃ ያህል ሁለት ምሳሌዎችን እንጥቀስ

ምሳሌ 1. "ቀደም ብሎ ያነበባችሁትን ተረት መልዕክት በራሳችሁ አባባል ግለጹ::" /ገጽ 98 መልመጃ/

2. "ያነበባችሁትን የጎሩይ ወልደ ስላሴን ታሪክ በራሳችሁ አባባል ግለጹ:: የታሪክ ቅደም ተከተሉን ተናገሩ::" /ገጽ 98፣ መልመጃ ፊደል ሀ/

ረ. "ንግግርና ንባብ":- የንግግር ክሂልን ለማዳበር በመርሐ ትምህርቱ ከተዘጋጁት የትምህርት ክፍሎች የመጨረሻ ክፍል ሆኖ የቀረበው ንግግርና ንባብ የሚለው ከገጽ 21-22 የተጠቀሰው ነው:: በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች የድርጊትንና የጊዜን ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ሐሳባቸውን ይገልጻሉ::

በመማሪያ መጽሐፉም ይሄው የትምህርት ክፍል ከገጽ 100 እስከ 102 "ተጠየቃዊ አስተሳሰብ" በሚል ርዕስ ትምህርት ሃያ አራት ላይ ቀርቧል:: አብዛኛዎቹ መለማመጃዎች ተማሪዎች ሐሳባቸውን በጽሑፍ እንዲገልጹ የሚጋብዙ ቢሆኑም ሁለት መልመጃዎች በንግግር እንዲመለሱ ሆነዋል::

ለምሳሌ 1. "የተዘባውን የሳር ቤት አሰራር በቅደም ተከተል አስቀምጡ::..."

/ገጽ 100-101 መልመጃ አንድ ተራ ቁጥር 2 ፊደል-ለ/

2. "የሚከተሉትን ሥዕሎች በቅደም ተከተል አስቀምጡ:: ..."

/101-102 መልመጃ አንድ ተራ ቁጥር 3 ፊደል ረ/

እዚህ ላይ ... "አስቀምጡ" የሚለው ትዕዛዝ በጽሑፍ እንዲመልሱ የሚያደርጋቸው አይሆንም ወይ የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል:: ለንግግር መለማመጃ የታቀዱ ናቸው በሚል

በምሳሌነት እንዲጠቀሱ የሆነው በጽሑፍ የሚመለሱትን ጻፉ በማለት ትዕዛዝ ስለተሰጣቸው ነው::

ከዚህ በላይ ከሀ-ረ የተዘረዘሩትና ከመርሐ ትምህርት ላይ የንግግር ክሂልን ለማስተማር /ለማዳበር/ የቀረቡት የትምህርት ክፍሎች በምሳሌዎቹ ለማረጋገጥ እንደተሞከረው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ሙሉ በሙሉ የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ በሚያዳብር መልኩ የቀረቡ ይመስላሉ:: ስለዚህ የደረጃ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በመርሐ ትምህርት መሠረት የተዘጋጀ ነው ማለት ይቻላል::

4.2.2. **በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በቂ የንግግር መለማመጃዎች ስለመዘጋጀታቸው**

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተዘጋጁት የንግግር ክሂልን ለማዳበር ተመርጠው የቀረቡት መለማመጃዎች በቂ ናቸው ወይስ አይደሉም? ለማለት ከሌሎች ትምህርት ይዘቶች /ክሂሎች/ አንጻር ያላቸውን መጠን ማወዳደር ነው:: በዚህም ውድድር መሠረት የንግግር ክሂል ትምህርት ትኩረት የተሰጠውና ያልተሰጠው መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል:: እነዚህን ለማከናወንና በቂ የንግግር ክሂል መለማመጃዎች ተዘጋጅተዋል ወይስ አልተዘጋጁም? ለማለት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የንግግር ክሂልን መለማመጃዎች ከሌሎቹ የትምህርት ይዘቶች ጋር በማነጻጸር ማሳየት ያስፈልጋል:: ንጽጽሩ በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ቀርቧል::

ሠንጠረዥ አራት:- በደረጃ 2 አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ክፍሎች /ክሂሎች/ መለማመጃ ጥያቄዎች

	የመለማመጃ ትምህርት ክፍል /ክሂል/	የጥያቄ ብዛት	ከመቶኛ የሚኖራቸው ድርሻ	የትኩረት ደረጃው	ምርመራ
1	ማዳመጥ	72	7.31%	5ኛ	
2	ንግግር	159	16.14%	3ኛ	
3	ንባብ	352	32.99%	1ኛ	
4	ጽሕፈት	118	11.98%	4ኛ	
5	ሰዋስው	298	30.26%	2ኛ	
6	ሥነ ጽሑፍ	13	1.32%	6ኛ	
7	ጠቅላላ	985	100%		

በተዘረዘረው መረጃ መሠረት በአጠቃላይ 985 ጥያቄዎች ሁሉንም የትምህርት ክፍሎች ተማሪዎች እንዲለማመዱባቸው በመማሪያ በጽሑፍ ውስጥ ተዘጋጅተውላቸዋል:: ሊኖር የሚገባው አማካይ የጥያቄዎች ብዛት 164.17 ያህል ነው:: ይህም ከመቶው 16.67 እጁን /16.67%/ ይይዛል:: የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ጥያቄዎች159 ሲሆኑ ከመቶው ስሌት 16.14 እጁን /16.14%/ ያህል ይይዛሉ::

የንግግር ክሂል ትምህርት መለማመጃ ጥያቄዎች ብዛት ከአማካይ የጥያቄዎች ብዛትና ከመቶኛ አማካይ ድርሻው ያልራቀ ነው:: ሆኖም ለንባብና ለሰዋስው ከቀረቡት መለማመጃ

ጥያቄዎች ያነሰ መለማመጃ ስላለው ትኩረት የተሰጠው በ3ኛ ደረጃ ነው:: ከአማካዩ የጥያቄዎች ብዛት አንጻር ከሌሎቹ የትምህርት ክፍሎች ግን የተሻለ ትኩረት ተሰጥቶታል:: ስለዚህ በደረጃ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተዘጋጁት የንግግር ክሂል መለማመጃ ጥያቄዎች በበቂ መጠን የቀረቡ ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ ሁለት "ለ"ን ይመልከቱ/::

4.2.3. የንግግር ትምህርት ይዘቶች ሳቢና ማራኪ ስለመሆናቸው

የንግግር ክሂል ትምህርት ሳቢና ማራኪ የሚሆነው ተማሪዎችን ለመማር፣ መምህራኑን ለማስተማር የሚያመቹ፣ ፍላጎታቸውን የሚያነሳሱ፣ እንዲሁም ተማሪዎች ከሚኖራቸው የክፍል ደረጃና ዕድሜ አንጻር የሚመጥኑ፣ መምህራኑ ካላቸው የሥልጠናና የትምህርት ደረጃ አኳያ ትምህርቱን ለመስጠት የማይቸገሩ ሆነው ሲገኙ አንደሆነ በዚህ ጥናት ክለሳ ድርሳን ላይ የተገለጸ ነው:: ከእነዚህ ሁኔታዎች አንጻር የደረጃ 2 የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አቀራረቡ ምን እንደሚመስል ቀጥሎ ታይቷል::

ተማሪዎች በጨዋታ፣ በውይይት፣ በተረት፣ በእንቆቅልሽ፣ በእንካስላንቲያ፣ በቡድን ውይይት፣ በክርክር፣ ወዘተ. እየተሳተፉ በሚያዝናና እና በሚስብ መልክ እንዲማሩ ሆነው መለማመጃዎች የተመረጡ፣ የተደራጁና የቀረቡ ናቸው:: በእነዚህ መለማመጃዎች አማካኝነት ተማሪዎች ሲሳተፉ የፍርሐት፣ የሐፍረትና የመደነጋገር ባህሪዎችን እያስወገዱና ደፋርና አንደበተ ርቱዕ እየሆኑ ይሄዳሉ::

ምሳሌ 1. "ሁለት ሁለት በመሆን ሁለት ሁለት እንቆቅልሾችን ተጠያየቁ:: የእንቆቅልሽ ጨዋታውን ስንጫወቱም የአጨዋወት ሥርዓቱን ጠብቃችሁ ተጫወቱ::" /ገጽ 125 መልመጃ ፊደል -ሰ/

3. "... ከጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን ሁለት እንካስላንቲያዎችን በጓደኞቻችሁ ፊት በመቀባበል ተመላለሱ::" /ገጽ 126/
4. "መምህራችሁ የሚሰጧችሁን መልመጃዎች /ስነ ቃላዊ ዜማዎች/ በመጠበቅ አጨዋወት ሥርዓቱን ጠብቃችሁ ተጫወቱ::
    1. እምቡሼ ገላ
    2. ጉልበቱ በርታ በርታ
    3. ድምቢሽ ለድምቢሽ
    4. ጨረቃ ድምቡልቦቃ እና ሌሎች የአካባያችሁን ዜማ ያላቸው ጨዋታዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡላቸው::" /ገጽ 128፣ መልመጃ ፊደል ሀ/

የትምህርት ቤቱም ሁኔታ እነዚህና ሌሎች የንግግር መለማመጃ ትምህርቶች ሲቀርቡ የተለየ እገዛንና በጀትን የማይጠይቁ በመሆናቸው ተግባራዊ ለማድረግ ችግር አያጋጥማቸውም::

4.2.4. ይዘቶቹ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያላቸው ስለመሆናቸው

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተመርጠው የተዘጋጁትና የንግግር ክሂልን ለማዳበር ያስችላሉ በሚል የቀረቡት መለማመጃዎች

1ኛ. መለማመጃዎቹ ካለፈው ደረጃ 1 መማሪያ መጽሐፍ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው:: ጨዋታዎች /ደረጃ 1 ገጽ 198/፣ ተረቶች /ደረጃ 1 ገጽ 163/፣ ወዘተ. ይገኛሉ:: በዚህም መማሪያ መጽሐፍ /በአባሪ ሁለት እንደተመለከተው/ ይዘቶቹ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት እንዳላቸው ማረጋገጥ ተችሏል::

2ኛ. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የንግግር መለማመጃዎች ተደጋጋፊ ሆነውና ጥልቀት እያገኙ መቅረባቸውን ያሣያል::

4.2.5. የአዘጋጆችና የተተኳሪ አመቻቾች የጽሑፍ መጠይቅ መልሶች

ለአዘጋጆችና ለተተኳሪ አመቻቾች የመጽሐፉን የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ በተመለከተ ለቀረቡላቸው የጽሑፍ መጠይቆች የሚከተሉትን መልሶች ሰጥተዋል::

ሀ. የአዘጋጆች መልስ

ስለዝግጅቱ አስተያየታቸውን በጽሑፍ የሰጡት አራት አዘጋጆች የደሴ መምህራን ኮሌጅ መምህራን ናቸው:: ከላይ በግምገማው የተገኘውን ውጤት የሚያጠናክር ሆኗል:: ይሄውም:-

1. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለንግግር ክሂል ትምህርት የተሰጠው ትኩረት በቂ መሆኑን፣
2. የቀረቡት መለማመጃዎች የተማሪዎችን ንዑሳን የንግግር ክሂሎች ከፍ የሚያደርጉና ሳቢና ማራኪ መሆናቸውን፣
3. በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት የንግግር ክሂል መለማመጃዎች የተማሪዎችን የአመቻቾች የትምህርት መስጫ ተቋማትን ሁኔታ ያገናዘቡ መሆናቸውን ለመገንዘብ ይቻላል::
4. መርሐ- ትምህርቱን መሠረት አድርጎ መማሪያ መጽሐፉ የተዘጋጀ መሆኑን፣ ወዘተ. ገልጸዋል::

ለ. የአመቻቾች መልስ

መረጃውን የሰጡት ተተኳሪ አመቻቾች ስምንት ሲሆኑ ከሶስት ወረዳዎች፣ ከአምስት አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢዎች የተገኙ ናቸው:: የሰጡት መረጃም በመጽሐፉ ግምገማ ላይና ከአዘጋጆች የተገኘውን መልስ የሚያጠናክር ነው::

1. ለንግግር ትምህርት የተመረጡት መለማመጃዎች በቂ መሆናቸውንና የተማሪዎችን፣ የአመቻቾችንና የትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን ሁኔታ ከግምት ወስጥ ያስገቡ መሆናቸውን፣
2. የንግግር ክሂል ትምህርት የይዘቶች አደረጃጀት ተከታታጥነትና ተለጣጣቂነት ያላቸው መሆናቸውን፣
3. የይዘቶች አቀራረብ ሳቢነትና ማራኪነት እንዳለውና የተማሪዎችን የንግግር ትምህርት የመማር ፍላጎት ማነሳሳት የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ ሶስት "ሐ" እና "መ" ይመልከቱ/

4.3. የደረጃ ሦስት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ ሥር በሚገኙ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የተዘጋጀው የደረጃ ሦስት መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂልን ለማስተማር የይዘት አመራረጡን፣ አደረጃጀቱንና አቀራረቡን ከማየታችን በፊት የመማሪያ መጽሐፉንና የመርሐ ትምህርቱን አጠቃላይ ገጽታዎች መመልከቱ ይሻላል::

"የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አማርኛ ትምህርት ደረጃ 3 የመማሪያ መጽሐፍ" በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ እና በኖርዌና ዴንማርክ ሕጻናት አድን ድርጅት ትብብር በደሴ መምህራን ኮሌጅ መምህራን በ1998 ዓ.ም የተዘጋጀ ነው:: መጽሐፉ 96 ገጾችና በእነዚህ ገጾች ውስጥ የተካተቱ 28 ይዘቶችን የያዘ ነው::

"የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የአማርኛ መርሐ ትምህርት ደረጃ ሦስት የአማራ ብ/ክ/መ/ት/ቢሮ" በሚል ስያሜ የቀረበው ደግሞ መርሐ ትምህርቱ ነው:: ቀደም ሲል በደረጃ አንድና ሁለት ግምገማ ውስጥ እንደተጠቀሰው መርሐ ትምህርቱ የታተመበት ዘመን አልተገለጸም ከ1996 ዓ.ም ወዲህ መታተሙን የማያመለክት ግን በመግቢያው ላይ ተጠቅሷል:: የተዘጋጀው በአ/ብ/ክ/መ/ት/ ቢሮ ነው::

መርሐ ትምህርቱ 47 ገፆች ያሉት ሲሆነ በውስጡ 28 ይዘቶችና እነዚህን ይዘቶች ለማስተማር የተመደቡ 132 ክፍለ ጊዜያት ይገኛሉ:: በእነዚህ ክፍለ ጊዜያት 28ቱን ይዘቶች በመሸንሸን ማዳመጥን፣ ንግግርን፣ ንባብን፣ ጽህፈትን፣ ሰዋስውንና ሥነ ጽሑፍን ለማስተማር እንደታቀደ ከዝርዝሩ መረዳት ይቻላል::

ስለሁለቱ መጻሕፍት ይህን ያህል ከተባለ ቀጥሎ መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ተመሥርቶ ስለመዘጋጀቱ፣ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተመርጠውና ተደራጅተው የቀረቡት የንግግር ክሂል መማሪያና መለማመጃ ጥያቄዎች በበቂ መጠን ስለመዘጋጀት አለመዘጋጀታቸው፣ ተመርጠውና ተደራጅተው የቀረቡት የንግግር መለማመጃዎች ሳቢነትና ማራኪነት ያላቸው ስለመሆናቸውና የተማሪዎችን የመምህራንና የትምህርት መስጫ ተቋማትን ሁኔታ ያገናዘቡ ስለመሆናቸው፣ ሲደራጅ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያላቸው መሆናቸውን እናያለን::

4.3.1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ተመሥርቶ ስለመቅረቡ

መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ የቀረበ መሆኑንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ ለንግግር ክሂል ትምህርት የተመረጡትን ይዘቶች /ክሂሎች/ ከዓላማቸው፣ ከይዘታቸውና ከተመደበላቸው ክፍለ ጊዜ አንጻር ለይተን እንመልከት::

ሠንጠረዥ አምስት፣ በደረጃ 3 መርሐ ትምህርት ውስጥ ንግግርን ለማስተማር የተመረጡና ደራጅተው የቀረቡ ይዘቶች

ተ.ቁ	የቋንቋ ት/ት ክፍል	ዝርዝር ዓላማ	ይዘት	ክፍለ ጊዜ	ገጽ	ምርመራ
1	ማዳመጥ፣ ንግግር ንባብ	የቃል፣ የጽሑፍና የንግግር መመሪያዎችን ይከተላሉ	ልዩ ልዩ መመሪያዎች	4	1-2	1 ክፍለ ጊዜ ለንግግር
2	ንባብ ጽሕፈትና ንግግር	አንድን ሐሳብ በልዩ ልዩ አባባል ይገልጻሉ	አንድን ሐሳብ በልዩ ልዩ አባባል መግለጽ	4	13-14	2 ለንግግር
3	ንባብ ጽሕፈትና ንግግር	ሃሳባቸውን ቅደም ተከተል በመጠበቅ ይገልጻሉ:: ልዩ ልዩ ነገሮችን ሁኔታዎችን ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ አወዳድረው አነጻጽረው ይገልጻሉ::	ተጠየቃዊ አስተሳሰብ ቅደም ተከተልን ጠብቆ ሐሳብን መግለጽ ማወዳደር ማነጻጸር	4	14-15	2 ለንግግር
4	ማዳመጥና ንግግር	ሥርዓትን ጠብቀው በመወያየት የመፍትሄ ሐሳብ ያቀርባሉ	- ውይይት	5	19	3 ለንግግር
5	ንግግርና ንባበ	በተጠየቃዊ አስተሳሰብ በመጠቀም ሐሳባቸውን ይገልጻሉ:: የሐሳቦችን የነገሮችን መንስኤና ውጤት ይገልጻሉ	- ተጠየቂያዊ አስተሳሰብ - የሀሳቦችን የነገሮችን መንስኤና ውጤት መግለጽ - ሁኔታዎችን ተመልክተው ነው እያሉ መደምደም - ሁኔታዊችን ተመለክተው አይደለም እያሉ መደምደም - ዕውነታን የግል አስተያየት መለየት	8	22-27	4 ክፍለ ጊዜ ለንግግር
6	ጽሕፈት ንግግር	የአንድን ንግግር ጽሑፍ ይዘት በራሳቸው አባባል ያቀርባሉ	የአንድን ንግግር ዕሑፍ ይዘት በራስ አባባል ማቅረብ	4	36-37	2 ለንግግር
7	ንግግር	ሥርዓትን ጠብቀው በዘገባ መልክ ያቀርባሉ	ክርክር	6	42	6 ለንግግር
8	ንግግር/ ጽሕፈት	የተመለከቱትን በዘገባ መልክ ያቀርባሉ	ዘገባ ማቅረብ	5	46	2 ለንግግር

ADDIS ABABA UNIVERSITY

በተራ ቁጥር 7 ላይ ከተጠቀሰው ውጪ ያሉት የንግግር ትምህርቶች ከማዳመጥ ከንባብና ከጽሕፈት ጋር በአንድነት የቀረቡ ናቸው:: በአንድነት የቀረቡትን ክሂሎች ለመለየት በመማር ማስተማር ክንውኑ ላይ የተገለጹት ክንዋኔዎች ወደማንኛው ክሂል እንደሚያደሉ በመመርመር ለንግግር የተመደበውን ክፍለ ጊዜ ለመለየት ተችሏል:: በዚህ አካሄድ ለንግግር የተመደበው ክፍለ ጊዜ 22 ይሆናል:: አጠቃላይ ከተመደበው 132 ክፍለ ጊዜ ከመቶው 16.17 እጁን /16.17%/ ይይዛል:: ለደረጃው ይቀርባል ተብለው ከተዘጋጁት 6 የቋንቋው ትምህርት ክፍሎች ማለትም ማዳመጥ፣ ንግግር፣ ንባብ፣ ጽህፈት ሰዋስውና ሥነ ጽሑፍ ከአማካይ 22 ጥያቄዎች ወይም 16.17% አንጻር ሲሰላ የንግግር ክሂል እኩል ከአማካይ የክሂሎች ድርሻ ትኩረት የተሰጠው መሆኑን ያሳያል::

እነዚህ በሠንጠረዡ ውስጥ ተመርጠው ተደራጅተው የቀረቡት የንግግር ክሂልን ለማዳበር ይረዳሉ የተባሉ ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተዘጋጅተው መቅረባቸውን መፈተሻ ሌላው ተግባራችን ይሆናል::

ሀ. "ማዳመጥ፣ ንግግርና ንባብ" በሚለው ክፍለ ትምህርት ንግግርን ለማስተማር በመርሐ ትምህርቱ የቀረበውን በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ስንመለከት ተማሪዎች የንግግር ክሂላቸውን ሳይሆን የጽሕፈት ክሂላቸውን ሊያዳብርላቸው በሚችል መልኩ ነው::

ለምሳሌ

1. "ሥዕሉ የሚያስተላልፈውን መልዕክት በክፍት ቦታው ላይ አስቀምጡ::" /ገጽ 1 መልመጃ አንድ/ ሥዕሎቹ ማስጠንቀቂያን ለማስተላለፍ የሚረዱ ወይም መመሪያ ሰጪዎች ናቸው:: ሲጋራ ማጨስ ክልክል ነው:: አደገኛ ነው የሚሉ ምልክቶችን የያዙ ናቸው:: ከሥዕሎቹ ፊት ለፊት ሠረገዝ /ዳሽ/ አለ:: በክፍት ቦታው /በሠረዙ/ ውስጥ መልሱን እንዲጽፉ የሚጠይቅ ነው::
2. "በአካባቢ ያሉ አዋቂ ሰዎችን በመጠየቅ ጎብረተሰቡ በመመሪያነትና በማስገንዘቢያነት በማስጠንቀቂያነት የሚጠቀምባቸውን አባባሎች ወይም ምሳሌያዊ አነጋገሮች ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ::" /ገጽ 2 መልመጃ ሁለት/::

ስለዚህ በሠንጠረዡ በተራ ቁጥር አንድ ላይ የተጠቀሰውን የንግግር ክሂል ለማስተማር በመርሐ ትምህርቱ ላይ የተነደፈው ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር አላገለገለም::

ለ. በሁለተኛ ደረጃ የንግግር ክሂልን ለማስተማር በመርሐ ትምህርቱ ላይ /ከገጽ 13-14/ "ንባብ፣ ጽሕፈትና ንግግር" ተብሎ የቀረበው ነው:: ሥዕሎችን በመመልከት ሐሳባቸውን እንዲገልጹ አንድን ሐሳብ በልዩ ልዩ አባባል መግለጽ እንዲችሉ ለማድረግ የቀረበ ትምህርት ነው:: ይህኛው ክፍል በመማሪያ መፅሀፉ /ገጽ 27 ትምህርት ዘጠኝ/ ላይ አንድን ሐሳብ በልዩ ልዩ አባባሎች በመገለጽ በጽሁፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ:: የሚል ነው::

ቀደም ሲል በፊደል "ሀ" ስር ላይ እንደተገለጸው ሁሉም መለማመጃዎች የቀረቡት የንግግር ክሂልን ለማዳበር በሚያስችል መልክ ሳይሆን የጽሕፈት ክሂልን ለማዳበር ነው:: መርሐ ትምህርቱና መማሪያ መጽሐፉ አሁንም /ዳግም/ አለመጣጣማቸውን የሚያመለክት ነው::

ሐ. "ንባብ፣ ጽሕፈትና ንግግር" የሚለው በሦስተኛ ደረጃ የንግግር ክሂልን ለማዳበር በመርሐ ትምህርቱ ገጽ 14-15 የቀረበ ነው:: በዚህ ክፍል ተማሪዎች በቤት ውስጥ በባህላቸው የሚደረጉ ልዩ ልዩ ድርጊቶችን በቃል እንዲናገሩ ያደፋፍራል፤ የጊዜንና የድርጊትን ቅደም ተከተል ይገልጻሉ፣ ነገሮችን እያወዳደሩና እያነጻጸሩ ይገልጻሉ ይላል:: እነዚህን ክንዋኔዎች ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችሉ መለማመጃዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ መዘጋጀቱን ስንመለከት የሚከተለውን እናገኛለን::

በመርሀ ትምህርቱ ላይ የተጠቀሰውን መሠረት አድርጎ በመማሪያ መጽሀፉ ገጽ 46 ጀምሮ ተጠየቃዊ አስተሳሰብ በሚል ትምህርት አስራ ስድስት ላይ ቀርቧል:: ከምንባቡም በኋላ የተወሰኑ መለማመጃዎች ተሰጥተዋል::

ምሳሌ 1. ከሚከተሉት ጥንድ ጥንድ ሐሳቦች መካከል ሁለቱን መርጣችሁ በምሳሌ መሠረት እያወዳደራችሁ /እያነጻጸራችሁ ዐረፍተ ነገር መሥርቱ::

ሀ. "ንብና ጉንዳን በልሀተኛ ታታሪ ነፍሳት ናቸው::..."

መ. "ጊዜን ባግባቡ በስራ ላይ ማዋልና በቁጠባ መኖር ለዕድገት ጠቃሚ ናቸው::"

/ገጽ 54፣ መልመጃ አራት ከሀ-መ/

ምሳሌ 2. የሚከተሉት የራስን የሕይወት ታሪክ ለመጻፍ የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው:: አቀማመጣቸው ግን የተፋለሰ ስለሆነ በትክክለኛ የድርጊት ቅደም ተከተል አስቀምጧቸው:: /ገጽ 90፣ መልመጃ ሁለት/

በዚህ መሠረት ይህ የትምህርት ክፍል መርሐ ትምህርቱን መሠረት አድርጎ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የሠፈረ ይመስላል::

መ. ማዳመጥና ንግግር በመርሐ ትምህርቱ በገጽ 19 ላይ የተጠቀሰና ትምህርቱ በውይይት የሚቀርብ መሆኑን የሚገልጽ ነው:: ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ውይይት እንዲያደርጉ የሚገፋፋ ክንዋኔዎች የተካተቱበት ነው:: እነዚህን ክንዋኔዎች ተግባሪዊ ለማድረግ የሚያስችሉ መለማመጃዎችም በመማሪያ መጽሐፉ ተጠቅሰው ይገኛሉ::

ለምሳሌ ከሚከተሉት ርዕሶች መካከል በአንዱ ላይ በቡድን ሆናችሁ ከዚህ በፊት ስለውይይት በተማራችሁት መሠረት ተወያዩ::

ሀ. "የትምህርት ቤታችሁን ንብረት እንዴት በጥንቃቄ መያዝ ይቻላል::..."

መ. "በአካባቢያችን የሚገኙ አሳሳቢ በሽታዎችና እንዴት መከላከል ይቻላል?" /ገጽ 40፣ መልመጃ ሀ-ሠ/

በመጽሐፉ የተጠቀሱት ውይይት እንዲያደርጉ የሚጋብዙ ጥያቄዎች ብቻ ሳይሆኑ ወይይቱን እንዴት ማካሄድ እንደሚቻል ማብራሪያ የሚሰጡ መመሪያዎችም ጭምር ናቸው::

እነዚህን ምሳሌዎችና ሌሎችም በመጽሐፉ የተካተቱ ነገር ግን በዚህ ያልተገለጹ መለማመጃዎች መሠረት በማድረግ ትምህርቱ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረበው መርሐ ትምህርቱን መሠረት አድርጎ እንደሆን ማረጋገጥ ይቻላል::

ሠ. ንግግርና ንባብ በአምስተኛ ደረጃ በመርሐ ትምህርት /ከገጽ 22-27/ ላይ የተጠቀሰ የትምህርት ክፍል ነው:: በዚህ የትምህርት ክፍል የይዘቱ ክፊሉ አካል "ሐ" "ተጠየቃዊ አስተሳሰብ" በሚል በመርሐ ትምህርቱ ከገጽ 14-15 ላይ ቀደም" ሲል የተጠቀሰ ነው:: ቀሪዎቹ የሐሳቦችን /የነገሮችን/ መንስኤና ውጤት መግለጽ ሁኔታዎችን ተመልከተው "ነው" እያሉ መደምደም ሁኔታዎችን ተመልክቶ "ይሆናል" እያሉ መደምደም እውነታንና የግል አስተያየትን መለየት የሚሉት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ መርሐ ትምህርቱን መሠረት አድርገው የተዘጋጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሲሞከር የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል::

1. መንስኤና ውጤት መግለጽ በተመለከተ በመማሪያ መጽሐፉ ቀርቧል::

   የቀረበው ግን ንግግርን ለማስተማር ሳይሆን ጽሕፈትን ለማስተማር ነው::

ለምሳሌ "ዐረፍተ ነገሮቹን የድርጊት መነሻ በማድረግ ውጤታቸውን ጽፋቸሁ ለክፍለ ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው::

ሀ. ልጅቷ ፈተና ከመድረሱ በፊት በርትታ አጥንታለች:: ...

ሠ.ልጂቱ በወባ ትንኝ ተነከሰች::" /ገጽ 51፣ መልመጃ ሁለት ተራ ቁጥር 3ሀ-ሠ/

2. "ሁኔታዎችን ተመልክተው ነው ... ይሆናል እያሉ መደምደም" የሚለውን

ስንመለከት እንደዚሁ በመማሪያ መጽሐፉ ቀርቦ እናገኘዋለን:: ነገር ግን ልምምዱ የሚካሄደው በንግግር ይሁን በጽሑፍ ተለይቶ አልተቀመጠም::

ለምሳሌ "የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች የያዙትን ሐሳብ በመገንዘብ ነው ወይም ይሆናል ወይም አይሆንም በማለት ደምድሙ::

ሀ. ለእንስሶች መጠለያ አስፈላጊ ----------::...

በ. አላግባብ የሰው ሀብት የሚፈለግ ሰው አንድ ቀን ይጋለጣል ---::" /ገጽ 52-53 መልመጃ ሶስት ሀ-በ/

በጽሕፈትም ሆነ በንግግር ማቅረቡ ትምህርቱን የሚሰጠው መምህር/ት ፍላጎት ስለሆነና በንግግር የመቅረብ እድሉም ከጽሑፍ ጋር እኩል ስለሆነ እነዚህን መለማመጃዎች ከመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርተው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ እንደተካተቱ አድርጎ መውሰድ የሚቻል ይመስላል::

3. "እውነታና የግል አስተያየትን መለየት" የሚለውና በመርሐ ትምህርቱ የተጠቀሰው ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የንግግር ክሂልንም ሆነ ሌሎች ክሂሎችን ለማዳበር አልቀረበም::

በዚህ መሠረት ንግግርና ንባብ የሚለው የትምህርት ክፍል ከመቶው 75 እጅ ያህል (75%) መርሐ ትምህርቱን መሠረት በማድረግ ንግግርን ለማስተማር በመማሪያ መጽሐፉ የቀረበ አይደለም:: ቀሪው 25% ግን የመርሐ ትምህርቱንና የመማሪያ መጽሐፉን መጣጣም ያሳያል::

ረ. "ጽሕፈትና ንግግር" የሚለው የትምህርት ክፍል በመርሐ ትምህርት በገጽ 36 እና 37 ላይ የቀረበና ተማሪዎች የአንድን ንግግር/ ጽሑፍ ሐሳብ በራሳቸው አባባል እንደገልጹ የሚያደርግ ነው:: በመማሪያ መጽሐፉም ከገጽ 69 ጀምሮ ይገኛል:: በጽሑፍና በንግግር አማካኝነት ያነበቡትን ታሪክ እንዲገልጹ አድርጓል:: በንግግር እንዲገልጹ ከሚያደርጉት ውስጥ የሚከተለውን ጽሑፍ በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ በራሳችሁ አገላለጽ ታሪኩን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው:: /ገጽ 70 መልመጃ ሁለት/:: በዚህ መሠረት መማሪያ መጽሐፉ /ይህ ክፍል/ ከመርሐ ትምህርቱ ተነስቶ የተዘጋጀ መሆኑን ያስገነዝበናል::

ሰ. "ንግግር" የሚለው ክፍል ከመርሐ ትምህርቱ ወስጥ ከሌሎች ክሂሎች ወይም የትምህርት ክፍሎች የንግግር ትምህርት ይዘት ሳይጣመር በተናጠል የቀረበበት ነው:: ይህ የክሂል ዘርፍ በመርሐ ትምህርቱ ገጽ 42 እና 43 የቀረበ ሲሆን ተማሪዎች ሐሳቦችን በመደገፍና በመቃወም ክርክር እንዲያካሂዱ የሚያደርግ ነው:: ይሄው ይዘት በመማሪያ መጽሐፉም

ከገጽ 82-83 ተዘጋጀቶ ቀርቧል:: ተማሪዎች የክርክር አካሄድን የሚያስገነዝባቸው መመሪያ ከቀረበላቸው በኋላ በዚያው መሠረት ክርክር እንዲያካሂዱ መለማመጃዎች ተሰጥተዋል::

ለምሳሌ:- "ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ ወይም ራሳችሁ በመረጣቸሁት ርዕስ ቀደም ሲል ስለክርክር በማስታወሻ የያዛችሁትን በመጠቀም ከተዘጋጃችሁ በኋላ በክፍል ውስጥ ክርክር አካሂዱ::

ሀ. ከእውቀትና ከሀብት የቱን ተመርጣላችሁ?

ለ. ለአገር ልማት የሚጠቅመው መንገድ ነው ሰው ነው?" የሚሉ መለማመጃዎች ተዘጋጅተው ቀርበዋል::

በእነዚህና በሌሎችም መረጃዎች መሠረት የዚህ መጽሐፍ ክፍል መርሐ ትምህርቱን መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ መሆኑን እንገነዘባለን::

ሸ. "ንግግር/ጽሕፈት" የሚለው ንግግርን በተመለከተ በመርሐ ትምህርቱ የቀረበ የመጨረሻው ክፍል ነው:: ይህ ክፍል የቀረበው በመርሐ ትምህርቱ በገጽ 46 እና 47 ላይ ነው:: ተማሪዎች ያዩትን ድርጊት ወይም ሁኔታ በቦታው ላልነበረና ላላየ ሰው በዘገባ መልክ እንዴት ማቅረብ እንደሚችሉ ለማለማመድ የሚያስችል ነው:: በመማሪያ መጽሐፉም /ከገጽ 92-96/ ቀርቧል:: በእነዚህ ገጾች ውስጥ ገጽ 96 መልመጃ ሁለት የሚከተለው ይገኛል

"በአካባቢያችሁ ባለው ገበያ ቀን የሚታየውን የሕዝብ ግንኙነት፣ የሸቀጥ ልውውጥና የገበያ አቀማመጥ በሚመለከት ዋና ዋና ነጥቦችን ይዛችሁ የቃል ዘገባ አቅርቡ::"

ስለዚህ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረበው ይህ የንግግር መለማመጃ መማሪያ መጽሐፉ መርሐ ትምህርቱን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ መሆኑን ያስረዳናል::

በአጠቃላይ በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ የንግግር ክሂልን ለማዳበር ከተዘጋጁት ይዘቶች መካከል ለመማሪያ መጽሐፉ ዝግጅት መነሻነት ማገልገላቸውን በተመለከተ አብዛኛዎቹ ለመማሪያ መጽሐፉ ዝግጅት እንደዋሉ ትንተናው አሳይቷል:: ሁለት ያህሉ ይዘቶች ግን ለጽሕፈት መለማመጃ እንጅ ለንግግር ክሂል አልዋሉም:: ከዚህ በመነሳት መማሪያ መጽሐፉ ሙሉ በሙሉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ አልተዘጋጀም ብሎ መደምደም ይቻላል::

4.3.2. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች በበቂ መጠን ስለመዘጋጀታቸው

ቀደም ሲል መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ መዘጋጀትና አለመዘጋጀቱ ተፈትሿል:: በተገኘውም ውጤት መሠረት መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ

ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀ መሆኑን የሚያመላክቱ በቂ መረጃዎች አልተገኙበትም:: በመጽሐፉ ውስጥ ንግግርን ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶች በመርሐ ትምህርቱ ሙሉ በሙሉ የተመሠረቱ አልመሆናቸው ታይቷል:: ከተወሰኑት በስተቀር በመርሐ ትምህርቱ የተነደፉት ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ሙሉ በሙሉ የሉም::

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ መማሪያ መጽሐፉ መርሐ ትምህርቱን ሙሉ በሙሉ መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ አለመሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም በራሱ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የንግግር ክሂልን እንዲያዳብሩ የቀረቡት መለማመጃዎችስ ምን ያህል በበቂ መጠን የተማሪዎችንን የንግግር ችሎታ ለማዳበር በሚያስችል መልኩ ቀርበዋል? የሚለውን እንመለከታለን:: በበቂ ሁኔታ መቅረብ አለመቀረባቸውን ለመበየን የንግግር ክሂል ከሌሎች ትምህርት ይዘቶች /ክፍሎች/ አንጻር ያለውን የሽፋን መጠን በማወዳደር ማየት ነው:: በዚህ መሠረት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን የሁሉንም ትምህርት ክፍሎች መለማመጃዎች የድግግሞሽ መጠን እናወዳድራለን::

ሠንጠረዥ ስድስት:- በደረጃ 3 አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ክፍሎች /ክሂሎች/ መለማመጃ ጥያቄዎች

	የመለማመጃ ትምህርት ክፍል /ክሂል/	የጥያቄ ብዛት	ከመቶኛ የሚኖራቸው ድርሻ	የትኩረት ደረጃ	ምርመራ
1	ማዳመጥ	1	0.19%	5ኛ	
2	ንግግር	60	11.65%	4ኛ	
3	ንባብ	120	23.30%	2ኛ	
4	ጽሕፈት	115	22.33%	3ኛ	
5	ሰዋስው	219	42.53%	1ኛ	
6	ሥነ ጽሑፍ	0	0		
7	ጠቅላላ	515	100%		

በደረጃ ሦስት መማሪያ መጽሐፍ ተዘጋጅተው የቀረቡት የሁሉም ትምህርት ይዘቶች መለማመጃ ጥያቄዎች 515 ናቸው:: በመርሐ ትምህርቱ ላይ ለተገለጹት ለ6ቱ የትምህርት ዘርፎች /ማዳመጥ፣ ንግግር፣ ንባብ፣ ጽሕፈት፣ ሰዋስውና ሥነ ጽሑፍ/ በአማካይ ሊዘጋጁ የሚገባቸው የመለማመጃ ጥያቄዎች ብዛት 85.83 ጥያቄዎች ናቸው:: በመቶኛ ስሌት ሲተመን ለእያንዳንዳቸው የሚኖራቸውም ድርሻ 16.67% ያህል ነው::

የንግግር ክሂልን ለማለማመድ በመማሪያ መጽሐፉ ወስጥ ተዘጋጅተው የቀረቡት 60 ጥያቄዎች ናቸው ከመቶ እጅ 11.65 /11.65/ ያህሉን ይይዛሉ:: በሁለቱም መመዘኛዎች ከአማካዩ ያነሱ ናቸው:: ከሌሎች ክሂሎች አንጻር ሲታይ ለንግግር ክሂል መለማመጃነት በመማሪያ መጽሐፉ ተዘጋጅተው የቀረቡት ዝቅተኛ ቁጥር ያላቸው ናቸው:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ ሁለት "ሐ"ን ይመለከቱ/::

4.3.3. የትምህርት ይዘቶቹን ሳቢነትና ማራኪነት በተመለከተ

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የንግግር ክሂልን ለማዳበር ተመርጠውና ተዘጋጀተው የቀረቡት መለማመጃዎች ሳቢነትና ማራኪነት እንዲሁም ንዑሳን የንግግር ክሂሎችን ለማዳበር ብቃት ያላቸው ስለመሆናቸውና የተማሪዎችን የመምህራንና የትምህርት መስጫ ተቋማቱን ሁኔታ ያገናዘቡ ስለመሆናቸው ቀጥሎ ታይቷል::

ሀ. ሳቢነትንና ማራኪነትን በተመለከተ

በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚጠቀሱት ይዘቶች ለተማሪዎች ሳቢና ማራኪ ሊሆኑ የሚችሉት ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባራት በማሳተፍ ማለትም በጭውውቶች፣ በክርክር፣ በቡድን ውይይት፣ በጋራ ውይይት፣ በሥዕሎችና በካርታዎች ምልከታ፣ ወዘተ. እንዲማሩ ሊያደርግ እንደሆነ በዚህ ጽሑፍ ክለሳ ድርሳን ላይ ተገልጿል::

ከዚህ አንጻር የደረጃ 3 የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ስንመለከት ንግግር ለማስተማር የቀረቡት መለማመጃዎች ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ተማሪዎች ንግግርን እንዲለማመዱ የሚያደርጉ ሆነው የቀረቡ ይመስላሉ:: ለዚህም ማስረጃ ይሆን ዘንድ የተወሰኑትን እንጥቀስ::

ለምሳሌ 1. ቤተ መጻሕፍት መግባትና ማንበብ በሚሰጠው ጥቅም ላይ በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ:: /ገጽ 43 መልመጃ 1 ተራ ቁጥር 3/

2. የሚከተለውን ሥዕል በመመልከት የተገነዘባችሁትን በቃል ለጓደኞቻችሁ ግለጹ:: /ገጽ 73 መልመጃ አራት/

ለ. ንዑሳን የንግግር ክሂሎችን ከማዳበር አንጻር ተማሪዎችን በቡድን በማወያየት በማከራከር ፍርሐታቸውንና ሐፍረታቸውን እንዲያስወግዱ ለማድረግ የሚችል ሆኖ ተገኝቷል:: ይሁን እንጅ እንደተረት፣ እንከስላንቲያ ያሉት ንዑሳን ንግግር ክሂሎችን ለማዳበር የሚረዱ መለማመጃዎች አልተከተቱም::

ሐ. የተማሪዎችን የአመቻቾችንና የትምህርት ቤቶችን ሁኔታ ያገናዘበ ስለመሆኑ ቀደም ባሉት ደረጃዎች ለመግለጽ እንደተሞከረው ትምህርቱን የሚጡት አመቻቾች የ10ኛን ወይም የ12 ክፍልን ያጠናቀቁና የአንድ ዓመት የማስተማር ሥልጠና የወሰዱ ናቸው:: እነዚህ አመቻቾች በዚህ ደረጃ የቀረበውን የንግግር ክሂል ትምህርት ለመስጠት የሚቸገሩ አይመስሉም:: ለተማሪዎቹም የቀረቡት መለማመጃዎች ከአካበቢያቸው ያልራቁና አደናጋሪ ባለመሆናቸው ለመገንዘብ አይቸገሩም::

በመጨረሻም ትምህርት ቤቶቹ እነዚህ የንግግር ክሂል ማዳበሪያ ትምህርቶች ሲሰጡ የተለየ ወጪን የሚጠይቁ ባለመሆናቸው ተግባራዊ ሲሆኑ የሚያስቸግር ነገር አይገጥማቸውም::

4.3.4. የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶቹ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያላቸው ስለመሆናቸው

ባለፉት ደረጃዎች በነበሩት መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በንግግር ክሂል ትምህርት የተጠቀሱና በዚህ መጽሐፍ የንግግር ክሂልን ለማዳበር ተመርጠው በተዘዘጋጁት መልመጃዎች ያልታዩ ጭውውት፣ ተረት፣ እንቆቅልሽና እንካስላንቲያ ናቸው:: ሌሎቹ ቀደም ብሎ አነደተገለጸው ክርክር፣ ውይይት፣ ሥዕሎች፣ ወዘተ. ቀርበዋል:: ቀሩ የተባሉት የንግግር ማቅረቢያዎች ከቀደሙት ክፍሎች ሰፊና ጠለቀ ባለ መልኩ መቅረብ እንደነበረባቸው አጥኚው ያምናል:: ስለዚህ ከተከታታይነትና ተለጣጣቂነት አንጻር የመማሪያ መጽሐፉ ጉድለት ያለበት እንደሆነ መረዳት ይቻላል::

4.3.5. የጽሑፍ መጠይቅ መልሶች

የጽሑፍ መጠይቆቹ የቀረቡት ለ4 አዘጋጆችና ለ8 አመቻቾች ነው:: አዘጋጆቹ የደሴ መምህራን ኮሌጅ መምህራን ሲሆኑ በአሁኑ ጊዜ በዚሁ ኮሌጅና በወሎ ዩኒቨርሲቲ በማስተማር ላይ ይገኛል:: 8ቱ አመቻቾች ቀደም ብሎ በተጠቀሰው ዞንና ወረዳዎች በ5 አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢዎች በማስተማር ላይ ያሉ ናቸው:: (ለበለጠ መረጃ አባሪ አራት "ሀ" እና አባሪ አምስት "ሀ"ን ይመልከቱ)::

ሀ. የአዘጋጆች መልስ

ስለዝግጅቱ አስተያየታቸውን በጽሑፍ የሰጡት አራት አዘጋጆች ናቸው:: የሰጡት መልስም በግምገማው የተገኘውን ውጤት የሚጠናክር ሆኗል::

1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ አለመዘጋጀቱን፣
2. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት ንግግርን ለማለማመድ የቀረቡት ይዘቶች ከሌሎች ክሂሎች አንጻር ሲታዩ ዝቅተኛ መሆናቸውን፣
3. ንዑሳን የንግግር ክሂሎችን ለማዳበር የሚያስችሉ መለማመጃዎች በበቂ መጠን የቀረቡ ባይሆንም እነዚያው ግን ንዑሳን የንግግር ክሂሎችን ለማዳበር ጠቃሚዎች እንደሆኑ፣
4. የንግግር ክሂልን ለማዳበር የተመረጡት መለማመጃዎች ከቀደሙት የክፍል ደረጃዎች አንጻር ሲታዩ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነታቸው የላላ መሆኑን፣

5. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የንግግር ክሂልን ለማዳበር የቀረቡት መለማመጃዎች የተማሪዎችን፣ መምህራንንና የትምህርት መስጫ ተቋማትን ሁኔታ ያገናዘቡ መሆናቸውን በመግለጽ ለቀረቡላቸው የጽሑፍ መጠይቆች መልስ ሰጥተዋል::

ለ. የአመቻቾች መልስ

አመቻቾች ለቀረቡላቸው የጽሐፍ መጠይቆች ከሰጡት መልስ መረዳት እንደሚቻለው በአዘጋጆች ከተሰጡት መልሶች የተለዩ አይደሉም:: መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ አለመዘጋጀቱን፣ የይዘቶች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት አለመኖሩን ከገለጹ በኋላ በአነስተኛ መጠንም ቢሆን የቀረቡት የንግግር መለማመጃ ይዘቶችን የተማሪዎችን ንዑሳን የንግግር ክሂሎች ለማዳበር የሚረዱ፣ ሳቢና ማራኪነት ያላቸው የተማሪዎችን የአመቻቾችንና የትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን ሁኔታ ከግምት ያስገቡ ናቸው ብለዋል::

4.4. የአንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ

የአንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በደሴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህራን እንደገና ተሻሽሎ በ1997 ዓ.ም. የተዘጋጀ ነው:: መማሪያ መጽሐፉ ክፍል አንድ፣ ክፍል ሁለትና ሦስት ተብሎ በሦስት ተከፍሏል:: በክፍል አንድ 2፣ በክፍል ሁለት 11ና በክፍል ሦስት 6 ትምህርት እየተባለ ስያሜ የተሰጣቸው 19 ክፍልፋዮችን የያዘ ነው::

4.4.1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ ስለመቅረቡ

የአንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት በ1996 ዓ.ም በሥ/ት/ዝ/ጥ/ም እንስቲትዮት የቋንቋዎች ት/ሥ/ት/ዝግጅት ቡድን ተሻሽሎ የተዘጋጀ ነው:: በሁለት የትምህርት ክፍለ አመት የተከፈለ ሆኖ በመጀመሪያው የትምህርት ክፍለ አመት 11 ይዘቶች፣ በሁለተኛው ደግሞ 8 በአጠቃላይ 19 ይዘቶች ተካተውበታል:: በመጀመሪያው የትምህርት ክፍለ አመት 80፣ በሁለተኛው 61 በሙሉ አመቱ 141 ክፍለ ጊዜያት ተመድበውለታል:: ከተጠቀሱት አጠቃላይ 19 ይዘቶች ውስጥ ለንግግር ትምህርት ተብለው በመርሐ ትምህርቱ ሠንጠረዥ ውስጥ የተገለጹት ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ የተመለከቱት ናቸው::

ሠንጠረዥ ሰባት:- በአንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ የቀረቡ የንግግር ትምህርት ይዘቶች

ተ.ቁ	የቋንቋ ት/ት ክፍል	ዓላማው	ይዘት	የተመደበበት ክ/ጊዜ	የሚገኝበት ገጽ	ምርመራ
1	ማዳመጥና ንግግር	የተለያዩ ድምጾችን አዳምጠው የምን ድምጽ እንደሆኑ ለይተው ይናገራሉ::	ልዩ ልዩ ድምፆችን መለየት የአንሰሳትና የአእዋፍ	4	1	2ክ/ጊዜ ለንግግር
2	ማዳመጥና ንግግር	ሰላምታ ይለዋወጣሉ በተለያዩ ጊዜዎች የሚጠቀሙባቸውን የሰላምታ ልውውጥ ቃላትን ተረድተው ይገለገላሉ	የሀሳብ ልውውጥ ሰላምታ መለዋወጥ	6	5-6	4 ለንግግር
3	ማዳመጥና ንግግር	የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቀው የሚፈልጉትን ይገልጻሉ ተጠየቀዊ በሆነ መንገድ ነገሮችን ይመዝናሉ	ተጠየቃዊ አስተሳሰብ የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተል ጠብቆ ተረቶችንና ታሪክችን መተረክ የማወዳደር ችሎታ	12	18-20	6 ለንግግር ብቻ የቀረበ

ከሠንጠረዡ መመልከት እንደሚቻለው የመጀመሪያው የቋንቋ ትምህርት ይዘት (ክፍል) ሆኖ የቀረበውና ልዩ ልዩ ድምፆችን ለመለየት የሚያስችለው ይዘት ነው:: ይህ ይዘት በመርሐ ትምህርቱ የተጠቀሰውን ዓላማ ሊያሳካ በሚችል መልኩ በመማሪያ መጽሐፉም ላይ በመጀመሪያው ክፍል ተጠቅሷል:: ሁለተኛው የቋንቋ ትምህርት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ አልቀረበም:: የሐሳብ ልውውጥ፣ ሥዕልንም ሆነ የሰላምታ ልውውጥን በተመለከተ የቀረበ የትምህርት ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የለም:: በሦስተኛ ደረጃ ተጠየቃዊ አስተሳሰብ በሚል ይዘት የቀረበው ሁለት ንዑሳን ይዘቶች አሉት::

1. "የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቀው የሚፈልጉትን ይገልጻሉ::"
2. "የማወዳደር ችሎታ የሚሉ" ናቸው (በመርሐ ትምህርቱ ከገጽ 18-20)::

እነዚህ ይዘቶች የሚቀርቡት:-

- "የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቀው የሚፈልጉትን ይገልጻሉ::"
- "ተጠየቃሚ በሆነ መንገድ ነገሮችን ያወዳድራሉ" የሚሉትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ነው::

ይዘቶቹ ዓላማዎቻቸውን መሠረት አድርገው በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ የመማር ማስተማሩ ክንውን ሲፈጸምባቸው ስንመለከት አንዳንድ ክንዋኔዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱ ቢመስሉም ከመርሐ ትምህርቱ ተቀድተው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ አለመስፈራቸውን አጠቃላዩን ዝግጅት ከተመለከትን በኋላ መደምደም እንችላለን:: ከክንዋኔዎቹ ውስጥ የተወሰኑትን እንጥቀስ፤

1. “ማንኛውም ነገር መነሻና መድረሻ እንዳለው በተለያዩ ምሳሌዎች ማለማመድ::” /ገጽ 20/
2. “ነገሮችን ለማወዳደር ልዩነትና ግንኙነታቸውን በሚገባ ማወቅ እንመዲያስፈልግ በምሳሌዎች ማስገንዘብ::” /ገጽ 20/
3. “ተማሪዎች ፊደል ሲለዩ የሆሄያትን ቅርጻዊና ድምፃዊ ልዩነት በማወዳደር እንዲማሩ በማድረግ ማለማመድ::” /ገጽ 20/ የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል::

በተራ ቁጥረ 1 እና 2 ላይ የተጠቀሱትን ክንዋኔዎች የመሰለ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የለም:: በተራ ቁጥር 3 የተጠቀሰውን ክንዋኔ የመሰለ ግን በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በስፋት ይገኛል:: ይሁን እንጂ ይህ ይዘት የንባብና የጽሕፈት ክሂል ትምህርቶች በሚቀርቡበት ጊዜ በስፋት የቀረበ ስለሆነ በዚህ ቦታ ላይ እንደገና መጠቀስ አይገባውም ነበር:: በሌላው የመርሐ ትምህርቱ ክፍል በስፋት ቀረቦ የሚገኘው ይዜው ክንዋኔ ነው:: ለማስረጃ ይረዳ ዘንድ የሚከተሉትን ከመርሐ ትምህርቱ እንጠቀስ:: ምሳሌ:-

- “በተለያዩ ድምፆች መካከል ያለውን ልዩነታቸውን በማዳመጥ ቅርፃቸውን ለይተው መናገር እንዲችሉ ማለማመድ::” /ገጽ 2/
- “እያንዳንዱ መሪ ሆሄ ከዘሮቹ ጋር ያለውን ግንኙነትና ልዩነት ማስገንዘብ::” /ገጽ 3/
- “የተዘበራረቁ ሆሄያትን ቅርጻቸውን ተመልክተው ድምፃቸውን እንዲለዩ ማለማመድ::” /ገጽ 4/

እነዚህን መሠረት በማድረግ በአንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበው የንግግር ክሂል ትምህርት የአንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርትን ሙሉ በሙሉ ተመሥርቶ ያልተዘጋጀ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል::

4.4.2. የንግግር ክሂል ትምህርት መለማመጃ ይዘቶች በበቂ መጠን ስለመጋጀታቸው

በዚህ ክፍል ለማየት የሚሞከረው በ1ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማረያ መጽሐፍ ውስጥ የንግግር ክሂልን ለማዳበር ተመርጠውና ተደራጅተው የቀረቡት መለማመጃዎች የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ለማዳበር ከመርሐ ትምህርቱ ውጭም ቢሆን በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በበቂ መጠን ተዘጋጅተው መቅረብ አለመቅረባቸውን ነው:: ይህንን ለማረጋገጥ የሚቻለው የንግግር ክሂል ከሌሎች የቋንቋው ክፍለ ትምህርቶች አንጻር ምን ያህል ትኩረት እንደተሰጠው በማነጻጸር ነው:: ይህንን ንጽጽር ለማካሄደ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን መለማመጃዎች በሙሉ በመዘርዘር ከዚያ ውስጥ ምን ያህሉ ለንግግር መለማመጃ እንደዋሉ ለይቶ በማውጣት ነው:: ለዚህ ይረዳን ዘንድ ዝርዝሩ በሠንጠረዥ ቀጥሎ ይቀርባል::

ሠንጠረዥ ስምንት:- በአንደኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ክፍሎች መለማመጃ ጥያቄዎች

	የመለማመጃ ትምህርት ክፍል /ክሂል/	የጥያቄ ብዛት	ከመቶኛ የሚኖራቸው ድርሻ	የትኩረት ደረጃው	ምርመራ
1	ማዳመጥ	45	8.23%	3ኛ	
2	ንግግር	7	1.28%	5ኛ	
3	ንባብ	236	43.14%	1ኛ	
4	ጽሕፈት	231	42.23%	2ኛ	
5	ሰዋስው	28	5.12%	4ኛ	
6	ሥነ ጽሑፍ	0	-	-	የለውም
7	ጠቅላላ	547	100%		

መረጃውን መሠረት በማድረግ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ትኩረት ተደርጎባቸው የቀረቡት ንባብና ጽሕፈት ናቸው:: የንግግር ክሂል ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝና የተሰጠው ትኩረት በጣም አናሳ መሆኑን የሚያመለክት ነው:: ሥነጽሑፍን በተመለከተ አንድም መለማመጃ አልቀረበም:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ ሁለት "መ"ን ይመልከቱ/::

በዚህ የክፍል ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎች የበለጠ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲማሩ የሚፈልገው ንባብና ጽሕፈትን እንደሆነ ተደርጎ ሊገመት ይችላል:: ይሁን እንጂ ይህ አስተያየት ከግምት ያለፈ ሊሆን አይችልም:: ምክንያቱም ተማሪዎች ሁሉንም የቋንቋ ክፍለ ትምህርቶች በእኩል ደረጃ ካልተማሩ መጨረሻ ላይ የሚገኘው ውጤት የተሳካ ሊሆን አይችልም:: ለዚህም ነው በዚህ ጥናት ክለሳ ድርሳን ላይ 12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ ተማሪዎች ራሳቸውንና አካባቢያቸውን በንግግር አማካኝነት ለመግለጽ ሲቸገሩ ይስተዋላሉ የሚል ሐሳብ ተጠቅሶ የቀረበው::

በዚሁ መማሪያ መጽሐፍ መግቢያ ላይም "... ይህ የአንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የቋንቋነ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማ መሰረት በማድረግ ... ተሻሽሎ የተዘጋጀ ነው" ይላል:: ይህ ማለት ለንባብና ለጽሕህፈት ብቻ ትኩረት ተደርጎ ሌሎቹ የቋንቋው ክፍለ ትምህርቶች /ክሂሎች/ ችላ ይባላሉ ማለት አይደለም:: ስለዚህ የመማሪያ መጽሐፉ ዝግጅት የቋንቋ ክፍለ ትምህርቶችን እኩል በሆነ መንገድ ያለማስተናገድ ችግር የታየበት በተለይም የንግግር ክሂልን የዘነጋ መሆኑን መገንዘብ የሚቻል ይመስላል::

4.4.3. የትምህርቱ ይዘቶች ሳቢነትና ማራኪነት ያላቸው ስለመሆናቸው

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የንግግር ክሂልን ለማዳበር የተመረጡት፣ የተደራጁትና የቀረቡት መለማመጃዎች ሳቢና ማራኪ ሆነው ስለመቅረባቸው፣ የንግግርን ንዑሳን ክሂሎች ለማዳር መቻልና አለመቻላው፣ እንዲሁም የተማሪዎችንና የመምህራንን ዳራ፣ የትምህርት ተቋማትን /የትምህርት ቤቶች/ አቅም ያገናዘቡ መሆን አለመሆናቸውን መገለጽ የሚቻል

አይመስልም:: ምክንያቱም 108 ገጾች ባሉት 547 የመለማመጃ ጥያቄዎች በወጡበት መጽሐፍ ውስጥ ለንግግር ክሂል ትምህርት የቀረቡት መለማመጃ ጥያቄዎች በሁለት መልመጃዎች ውስጥ ሰባት ጥያቄዎች ብቻ ናቸው:: በእነዚህ ጥያቄዎች አማካኝነት ተማሪዎች ሥዕሎችን ተመልክተው እንዲናገሩ፣ ተረት እንዲተርቱ፣ የሚጋብዙ ናቸው:: እንደክፍል ደረጃው የሚመጥኑ በርከት ያሉ ክርክሮች፣ ውይይቶች፣ የቡድን ጭቅጭቆች /ሚና ጨዋታ/፣ ጥያቄና መልስ፣ እንቆቅልሽ፣ እንካስላንቲያ፣ የመሳሰሉትን አካቶ በማቅረብ የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ከፍ ማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ መፍጠር ይቻል ነበር::

ስለዚህ ትምህረቱ የቀረበው ሳቢና ማራኪ በሆነ መልኩ አይደለም:: የቀረቡትን መልመጃዎች ብቻ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር የተማሪዎች፣ የመምህራንና የትምህርት ቤቶች ሁኔታ የሚፈቅድ ይመስላል::

4.4.4. የይዘቶቹን ተከታታያነትና ተለጣጣቂነት በተመለከተ

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የንግግር ክሂል ተደጋግሞ ለልምምድ ባለመቅረቡ ያለው ተከታታይነትም ሆነ ተለጣጣቂነት በጣም ዝቅተኛ ነው ብሎ መናገር ይቻላል:: ነገር ግን በመልመጃዎቹ ውስጥ የቀረቡት ሥዕልን አይቶ መናገርና ተረት መተረተ በቀጣዮቹ የክፍል ደረጃዎችም ቀርበዋል::

ለምሳሌ 1. "በሚከተሉት ሥዕሎች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በማወዳደር አስረዱ::"
/2ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ ገጽ 13፣ ተራ ቁጥር 4/

2. "የታሪኩን ቅደም ተከተል ጠብቃቸሁ አንድ ተረት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አውሩላቸው::" /2ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ ገጽ 65 ተራ ፊደል ሸ/

4.4.5. ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መልሶች

መማሪያ መጽሐፉን ያዘጋጁና አማርኛ ቋንቋን አንደኛ ክፍል በማስተማር ላይ የሚገኙ ተተኳሪ መምህራን መጽሐፉ ንግግርን ለማስተማር ያለውን የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ በተመለከተ የተለያዩ የጽሑፍ መጠይቆች ቀርበውላቸው የሚከተሉትን መልሶች ሰጥተዋል::

ሀ. የአዘጋጆች መልስ

ስለዝግጅቱ አስተያየታቸውን በጽሑፍ የሰጡት አንድ አዘጋጅ ናቸው:: ከዚህ አዘጋጅ መልስ እንደምንረዳው በተሰጡት አማራጮች እንደማይስማሙና በእሳቸው እምነት ለአንደኛ ክፍል ተማሪዎች ንግግርን ማስተማር አስፈላጊ እንዳለሆነ ነው:: ከዚህ አኳያ በመማሪያ መጽሐፉ ግምገማ በተገኘው ውጤት አይስማማም::

ለ. የመምህራን መልስ

መረጃውን የሰጡት ተተኳሪ መምህራን 11 ሲሆኑ ከሶስት ወረዳዎች ስድስት መደበኛ ትምህርት ቤቶች የተገኙ ናቸው:: የአበዛኛዎቹ መልሶች በመጽሐፉ ግምገማ ላይ የተገኘውን ውጤት የሚያጠናክር ነው:: ማለትም የአንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ:-

1. በመርሐ ትምህርቱ ላይ ሙሉ በሙሉ ተመስርቶ እንዳልተዘጋጀ
2. የንግግር ክሂ መለማመጃ ይዘቶችን በበቂ መጠን እንዳላካተተ
3. ሳቢና ማራኪ የሆኑ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብ እንደማይታየበት
4. ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያላቸውን ይዘቶች እንዳልያዘ ወዘተ. በመልሶቻቸው ገልፀዋል:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ ሦስት "ሀ" ን ይመልከቱ/::

4.5. የሁለተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ

የ2ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የተዘጋጀው በ1996 ዓ.ም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ በደብረ ብርሃን መምህራን ኮሌጅ መምህራን አማካኝነት ነው:: መጽሐፉ 88 ገፆችን፣ 22 የተለያዩ ርዕሶች አሉት:: ርዕሶቹ የተለያዩ ምንባቦችንና መልመጃዎን ይዘዋል:: በዚህ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የንግግር ክሂልን ለማዳበር ተዘጋጅተው የቀረቡት መለማመጃ ጥያቄዎችን ከመርሐ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን መጣጣም ከሌሎቹ የቋንቋው ክፍለ ትምህርቶች አንጻር ሲታይ በቂ የንግግር ክሂልን ማዳበር የሚያስችሉ መለመጃመጃዎች መቅረባቸው፣ የቀረቡት መለማመጃዎች የተማሪዎችን፣ የመምህራንና የትምህርት ቤቶችን ሁኔታ ያገናዘቡ ስለመሆናቸውና አቀራረባቸው ሳቢነትና ማራኪነት ያለው ስለመሆኑ፣ ንዑሳን የንግግር ክሂሎችን ለማዳበር ያላቸው ብቃት ይዘቶቹ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያላቸው ስለመሆናቸው የሚሉት በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ ይቀርባሉ::

4.5.1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀ ስለመሆኑ

መማሪያ መጽሐፉ ከመርሐ ትምህርቱ ጋር ያለው ተያያዥነት ከመነሳቱ በፊት ስለመርሐ ትምህርቱ አንዳንድ ነጥቦችን እናንሳ

በአማራ ብሄራዊ ክልል ትምህርት ቢሮ ሥር ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች የሚያገለግለው የ2ኛ ክፍል መርሐ ትምህርት የተዘጋጀው በሥ/ት/ዝ/ጥ/ም ኢንስቲትዩት የቋንቋዎች ት/ሥ/ት/ዝ/ ቡድን በ1996 ዓ.ም ነው:: መርሐ ትምህርቱ 25 ገጾች ያሉት ሲሆን በእነዚህ ገጾች 25 የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች ይገኛሉ:: እነዚህን ይዘቶች ለማስተማር 159 ክፍለ ጊዜያት ተመድበዋል:: መማሪያ መጽሐፉ ከመርሐ ትምህርቱ ጋር ያለውን ትስስር ለማየት

እንችል ዘንድ በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ የሚገኙትን የንግግር ክሂል ለማስተማር የዋሉ ይዘቶችንም ሆነ ክፍለ ጊዜያትን ለይተን በሠንጠረዥ እንመለከታለን::

ሠንጠረዥ ዘጠኝ የንግግር ክሂል ይዘቶች መጠን በ2ኛ በክል መርህ ትምህርት ውስጥ

ተ.ቁ	የቋንቋ ትምህርት ክፍል	ዝርዝር ዓላማዎች	ይዘት	ክፍለ ጊዜ	የሚሰበት ገጽ	ምርምራ
1	ማዳመጥ ማናገር	ያዳመጧቸውን ተረቶች ወይም ታሪኮች መልሰው ይናገራሉ	አጾምጦ መልሶ መናገር	2	1	1 ክፍለ ጊዜ ለንግግር
2	ንባብ/ ማዳመጥና ንግግር	መመሪያዎችን ተከትለው የታዘዙትን ይሰራሉ	ልዩ ልዩ መመሪያዎች	6	18	3 ክፍለ ጊዜ ለንግግር
3	ማዳመጥና ንግግር	ለውይይት ወቅት ሊከተሏቸው የሚገቡ ሥርዓቶችን አውቀው ይወያያሉ:: ሥርዓቱን ጠብቀው ይጫወታሉ	ጭውውትና ውይይት	5	21	4 ክፍለ ጊዜ ለንግግር
4	ንግግር እና ጽሕፈት	የድርጊትንና የጊዜን ቅደም ተከተል ጠብቀው እለታዊ ክንዋኔዎቻቸውን ይዘረዝራሉ	ተጠያቃው አስተሳሰብ የድርጊትና ጊዜ ቅደም ተከተል	6	22	3 ክፍለ ጊዜ ለንግግር
5	ንግግር ማዳመጥ	የአንድን ጽሑፍ ወይም ንግግር ይዘት በራሳቸው አባባል በንግግር ያቀርባሉ	የንግግር ይዘትን በራስ አባባል ማቅረብ/ ፓራፍሬዝ/	6	24	3 ክፈለ ጊዜ ለንግግር

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የንግግር ክሂል ለብቻው ተለይቶ አልቀረበም:: ለንግግር የዋለው ክፍለ ጊዜ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ የመማር ማስተማሩን ክንውን ማየት አስፈልጋል:: በክንውኑ ላይ የተጠቀሱትን ተግባራት በማየት የትኛው ክሂል በምን ያህል ክፍለ ጊዜ እንደሚጠናቀቅ መገመት ይቻላል:: ስለዚህ ለንግግር ክሂል የዋሉት ክፍለ ጊዜያት 13 ናቸው:: እነዚህም በአጠቃላዩ ከተመደበው 159 ክፍለ ጊዜያት ውስጥ ከመቶው እጅ 8.18 (8.18%) ያህሉን ይይዛል:: ለስድስቱ ትምህርት ክፍሎች ከሚደርሰው አማካይ 26.5 ክፈለ ጊዜ (16.67%) በጣም አናሳ ነው::

መማሪያ መጽሀፉ በመርህ ትምህርቱ ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ መሆኑን ለማረጋገጥ እነዚህ ይዘቶች በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ መቅረባቸውን ማረጋገጥ ይኖርብናል::

ለዚህም፣

1. በሠንጠረዡ ተራ ቁጥር አንድ ላይ "ማዳመጥና ንግግር" የሚለውና በመርሐ ትምህርቱ ገጽ 1 ላይ የሚገኘው በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ተማሪዎች እንዲለማመዱበት የቀረበ መልመጃ አለ::

ለምሳሌ ሀ. "ብልጧ ጦጢት በሚል ርዕስ የቀረቡትን ሥዕላዊ መግለጫዎች በሙሉ በመመልከት የተረዳችሁትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አብራሩ::" /ገጽ 4፣ መልመጃ አንድ፣ ተራ ቁጥር 2/

ለ. “በአካባቢያችሁ ያሉትን አዋቂ ሰዎች የተለያዩ ተረቶች እንዲነግሯችሁ በመጠየቅ ካዳመጣቸሁት ውስጥ ደስ የሚላችሁን ተረት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በክፍል ውስጥ አውሩላቸው::” /ገጽ 4፣ መልመጃ አንድ፣ ተራ ቁጥር 4/

2. በሠንጠረዡ ላይ የጠቀስናቸው “ንባብ/ማዳመጥና ንግግር” የሚሉት የቋንቋ ትምህርት የዘቶች /ክፍሎች/ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ አልተጠቀሱም:: በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ ንግግርንና ንባብን ወይም ማዳመጥን ለማስተማር ከታቀደ በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ግን አልተካተተም::

3. በተራ ቁጥር 3 “ማዳምጥና ንግግር” ለማስተማር በመርሐ ትምህርቱ የቀረበው ይዘት በመማሪያ መጽሐፉም ውስጥ ይገኛል:: ለማስረጃ ያህል የተወሰኑትን እንመልከት::

ለምሳሌ ሀ. “በሰዓቱ ትምህርት ቤት ለመድረስ ምን ማድረግ እንደሚሻል በክፍል ውስጥ ተወያዩበት::” /ገጽ 34፣ መልመጃ 13፣ ተራ ቁጥር 5/

ለ. “ደስ የሚላችሁን ጉዳይ /ርዕሰ/ በመምረጥ በጭውውት መልክ ተማሪዎችን የሚያስደስት ነገር አቅርቡ::” /ገጽ 39፣ መልመጃ 14፣ ተራ ቁጥር 1/

4. በተራ ቁጥ 4 ላይ የተጠቀሰውና “ንግግር እና ጽህፈት” ለማስተማር ተዘጋጅቶ የቀረበው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥም እንዲሁ ተዘጋጅቶ ቀርቧል::

ለምሳሌ:- “የታሪኩን ቅደም ተከተል ጠብቃችሁ አንድ ተረት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አውሩላቸው::” /ገጽ 65፣ መልመጃ 19፣ ተራ ፊደል ሸ/

5. በመጨረሻ ላይ የተጠቀሰውና “ንግግርና ማዳመጥ” ለማስተማር የቀረበው ይዘት ንግግርን ማለማመድ የሚያስችሉ የተለያዩ መልመጃዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተጠቅሰው ይገኛሉ::

ለምሳሌ:- “... ተረቱን ከተረታችሁ በኋላ ከተረቱ ምን እንደምትማሩ ለመምህራችሁ ተናገሩ::” /ገጽ 56፣ መልመጃ 18፣ ፊደል ሐ፣ ተራ ቁጥር 5 እና 6/

የቀረቡትን ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ በመርሐ ትምህርቱ ከቀረቡት 5 የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች ውስጥ አራቱ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱ ሲሆኑ አንዱ ግን አልተጠቀሰም:: ስለዚህ መማሪያ መጽሐፉ ሙሉ በሙሉ መርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ ተዘጋጅቷል ለማለት የሚቻል አይመስልም::

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

4.5.2. የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ የሚያዳብሩ መልመጃዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በበቂ መጠን ስለመዘጋጀታቸው

የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ለማዳበር የሚያስችሉ መለማመጃዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በበቂ ደረጃ መዘጋጀትና አለመዘጋጀታቸውን ለማረጋገጥ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን አጠቃላይ የቋንቋውን ትምህርት ይዘቶች /ክፍሎች/ ለማለማመድ የቀረቡት ጥያቄዎችና መልመጃዎች መፈተሽ ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ በሠንጠረዥ በመለየት የእያንዳንዱን ክሂል ድረሻ ማየት ይገባል።

ሠንጠረዥ አስር፦ በሁለተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ክፍሎች መለማመጃ ጥያቄዎች

	የመለማመጃ ትምህርት ክፍል /ክሂል/	የጥያቄ ብዛት	ከመቶኛ የሚኖራቸው ድርሻ	የትኩረት ደረጃው	ምርመራ
1	ማዳመጥ	4	0.73%	6ኛ	
2	ንግግር	99	18.07%	3ኛ	
3	ንባብ	202	36.86%	1ኛ	
4	ጽሕፈት	71	12.6%	4ኛ	
5	ሰዋስው	147	21.82%	2ኛ	
6	ሥነ ጽሑፍ	25	4.56%	5ኛ	
7	ጠቅላላ	548	100%		

የዚህን ሠንጠረዥ አማካይ የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ትኩረተ ስንመለከተ የ548 ጥያቄዎች 91.33፣ ከመቶኛ ስሌት ከሚሰላው አንጻር ደግሞ 16.67% ይሆናል። ማለትም እያንዳንዱ የቋንቋ ትምህርት ክፍል እኩል ትኩረተ ቢሰጣቸው ኖሮ የጥያቄዎቹ ቁጥር 91.33 በመቶኛ ስሌት የሚሰላው ደግሞ 16.67% ይሆን ነበር ማለት ነው። ስለዚህ ምንም እንኳ ከንባብና ከሰዋስው አንጻር ሲታይ ዝቅ ያለ ቢሆንም ከአማካይ ድርሻው አኳያ ሲታይ የንግግር ትኩረት የመሰጠቱ ደረጃ ከፍ ያለ ስለሆነ የንግግር ክሂል ትኩረት ተሰጥቶት የተዘጋጀ ነው ማለት ይቻላል። የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ሊያዳብሩ የሚችሉ ማለማመጃዎች በበቂ መጠን ቀርበዋል ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ይመስላል። /ለበለጠ መረጃ አባሪ ሁለት "ሠ"ን ይመልከቱ/።

4.5.3. የትምህርቱ ይዘቶች ሳቢነትና ማራኪነት ያላቸው ስለመሆናቸው

ንዑሳን የንግግር ችሎታዎች ከማዳበር አንጻር ማራኪና ሳቢ፣ የተማሪዎችን የመምህራንና የትምህት ቤቶችን ሁኔታ ያገናዘበ ሆኖ ስለመቅረቡ የሚለውን ስናነሳ ንዑሳን የንግግር ችሎታዎች የምንላቸው ሳይፈሩና ሳይደነጋገሩ ሐሳብን በሰዎች ፊት መግለጽ መቻል፣ በውይይት፣ በክርክርና በቃለ ምልልስ፣ ተረቶችን በመተረት፣ ወዘተ. መሳተፍ መቻል ናቸው። እነዚህን ችሎታዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተማሪዎች እንዲያዳብሯቸው የሚያስችሉ በቂ

መለማመጃዎች ተዘጋጅተው ቀርበዋል:: ከመድጸፉ ይዘቶች መመልከት እንደሚቻለው ተረቶች፣ ውይይቶች፣ ጭውውቶች፣ ክርክሮች፣ ወዘተ. ተዘርዝረዋል:: አቀራረባቸውም ተማሪዎችን በሚያነቃቃና አሳታፊ በሆነ መልኩ ሳቢና ማራኪ ነው::

በተማሪዎች በመምህራንና በትምህርት ቤቶች ዘንድም ይዘቶቹን ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻሉ ናቸው:: የተማሪዎችን የእድሜና የክፍል ደረጃ ባገናዘበ መልኩ፣ ቀላል አቀራረብን የተከተሉ ክርክሮች፣ ውይይቶች እንዲያካሄዱ ተደርገዋል::

ለምሳሌ:- "ከማርና ከወተት የትኛውን ትወዳላችሁ? ምክንያታችሁን ተናገሩ::" /ገጽ 35 መልመጃ 13፣ ፊደል "ሐ"፣ ተራ ቁጥር 1/ የሚለው ተማሪዎች ሐሳባቸውን እየሰነዘሩ እንዲከራከሩ የሚለማመዱበትን ደጋፊዎች በተለያዩ ቡድኖች ሆነው የሚያካሂዱትን ክርክር ቀለል ባለ አቀራረብ እንዲለማመዱት አድርጓል::

ከመምህራኑም የሥልጠና ሁኔታ እነዚህ ክሂሎች የሚዳብሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚቸገሩ አይደሉም:: 10ኛን ወይም 12ኛ ክፍልን ካጠናቀቁ በኋላ የአንድ አመት የማስተማር ሥልጠና ያገኙ በመሆናቸው የቀረበውን ትምህርት ለማስተማር እንደማይቸገሩ ይታሰባል::

ከትምህርት ተቋማትም አንጻር የሚቀርበው ትምህርት ብዙ ወጭንና የተለየ ሁኔታ እንዲመቻችለት የማይጠይቅ በመሆኑ ትምህርቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግድ ሁኔታ አይታይም::

4.5.4. የትምህርቱ ይዘቶች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያላቸው ስለመሆናቸው

በ2ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት በአብዛኛው ለብቻው ተለይቶ የቀረበ ነው:: አንዳንድ ቦታዎች ላይ ደግሞ ከሌሎች ክሂሎች ጋር የሚቀርብበት ሁኔታ ይታያል::

ምሳሌ 1. "ዕፅዋት ለሰው ልጅ ጠቃሚ ናቸው የተባለበትን ምክንያት ለክፍል ጓደኞቻቸው አስረዱ::" /ገጽ 16፣ መልመጃ 8፣ ተራ ቁጥር 3/

በዚህ ምሳሌ መሠረት ተማሪዎች ዕፅዋት ለሰው ልጅ ጠቃሚ ናቸው የሚለውን ሀሳብ ከምንባቡ ውስጥ ደጋግመው በማንበብ ይገነዛበሉ:: ቀጥለው በራሳቸው አባባል ምክንያታዊ የሆነ ገለጻ ይሰጣሉ:: ንግግር ከንባብ ጋር የቀረበበት መለማመጃ መሆኑንም ያስገነዝበናል::

ምሳሌ 2. "በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ያለው አትክልት በጥሩ ሁኔታ እንዲያድግ ምን ማድረግ ይሻላል በክፍል ውስጥ ተወያዩበት::" /ገጽ 34፣ መልመጃ 13፣ ፊደል ሀ፣ ተራ ቁጥር 4/ በዚህኛው ምሳሌ መሠረት ደግሞ የንግግር ክሂል ብቻውን እንዲዳብር የተደረገበት ነው:: በእርግጥ አንዱ ሲናገር ሌላው ማድመጡ የማይቀር ቢሆንም::

ከሁለቱም ምሳሌዎች መረዳት የሚቻለው የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚያስችሉ መለማመጃዎች በውል ታስቦባቸው ተዘጋጅተው የቀረቡ መሆናቸውን ነው::

ተከታታይነትና ተለጣጣቂነታቸውን በተመለከተም:-

1ኛ. ቀደም ባለው የክፍል ደረጃም ሆነ በቀጣዩ የክፍል ደረጃ የተወሰኑት የንግግር ክሂል ማዳሪያዎች ቀርበው በዚህ ክፍል በተሻለ ሁኔታ መቅረባቸውን አንመለከታለን::

ምሳሌ 1. "ከምንባቡ ያገኛችሁትን ተረት የሚመስል ሌላ ተረት ከወላጆቻችሁ ጠይቃችሁ በማምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተርኩላቸው::" /አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ አንደኛ ክፍል፣ ገጽ 107፣ መልመጃ አራት፣ ተራ ቁጥር 1/ ከቀደመው የቀጠለ መሆኑን ያሳያል::

ምሳሌ 2. "አንድ ተረት አንብባችሁ ወይም አዳምጣችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተርኩላቸው::" (አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ 3ኛ ክፍል፣ ገጽ 72፣ መልመጃ 3፣ ተራ ፊደል ለ) ለተከታዩ ክፍል መሰረት የጣለ መሆኑን ያሳያል::

2ኛ. በዚሁ የክፍል ደረጃመ በመጽሐፉ የተለያዩ ቦታዎች የንግግርን ክሂል ለማዳበር የሚያስችሉ መለማመጃዎች ቀርበዋል::

ከነዚህ መረጃዎች በመነሳት በ2ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የንግግር ክሂል መለማመጃ ጥያቄዎች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያላቸው ናቸው ብሎ መደምደመ የሚቻል ይመስላል::

4.5.5. ከጽሑፍ መጠይቆች የተገኙ መልሶች

ሀ. የአዘጋጆች መልስ

የሁለተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍን ከአዘጋጁት የደብረ ብርሃን መምህራን ኮሌጅ መምህራን ውስጥ ለጽሑፍ መጠይቁቹ መልስ የሰጡት ሁለት ናቸው:: ሁለቱ የሰጧቸውን መልሶች ጠቅለል አድርገን ስንመለከታቸው የሚከተሉትን ነጥቦች የያዙ ሆነው አናገኛቸዋለን::

1. መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት አብዛኛዎቹ የንግግር ክሂል ማስተማሪያ ይዘቶች በመርሐ ትምህርቱ የሚገኙ መሆናቸውን፣
2. የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ሊያዳብሩ የሚችሉ ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በበቂ መጠን የተዘጋጁ መሆናቸውን፣
3. የትምህርት ይዘቶቹ አቀራረብ ሳቢነትና ማራኪነት ያለውን አቀራረበ የተከተሉ እንደሆኑና የተማሪዎችን የመማር ፍላጎትን እንደሚያነሳሱ፣

4. የትምህርት ይዘቶች ሲደራጁ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት እንዲኖራቸው የተደረገ መሆኑንና ሌሎችንም ከእነዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሀሳቦች ሰጥተዋል:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ ሦስት "ሸ"ን ይመልከቱ/::

ለ. የመምህራን መልስ

የመጠይቆቹን መልስ የሞሉት ተተኳሪ መምህራን 12 ሲሆኑ ከሦስቱ ወረዳዎች በሚገኙ ስድስተ ትምህርት ቤቶች በማስተማር ላይ ያሉ ናቸው:: የሰጧቸው የጽሑፍ መጠይቅ መልሶች የሚከተሉትን መረጃዎች የያዙ ናቸው::

1. የንግግር ክሂልን በማስተማር የተመረጡት ይዘቶች በመጽሀፉ ሲካተቱ መርሀ ትምህርቱን መሰረት አድርገው እንደሆነ
2. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ንግግርን ለማስተማር የቀረቡ መለማመጃዎች በበቂ መጠን እንደቀረቡ፣
3. ሳቢነትና ማራኪነት ያላቸው የንግግር ክሂል ትምህርቶች እንደሚገኙና የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት የሚያነሳሱ፣
4. የይዘቶች አደረጃጀት ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት እንደሚታይባቸው ገልጸዋል:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ ሦስት "ቀ"ን ይመለከቱ/::

4.6. የ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ

የ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የተዘጋጀው በ1996 ዓ.ም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በደሴ መምህራን ኮሌጅ መምህራን አማካኝነት ነው:: ይህም 94 ገጾች ያሉት ሲሆን በእነዚህ ገጾች የተካተቱ 20 ርዕሶች ይገኛሉ:: ርዕሶቹም የተለያዩ ምንባቦችንና መልመጃዎች ይዘዋል::

ስለመማርያ መጽሐፉ ይህንን ያህል ካልን በመቀጠል ተመርጠውና ተዘጋጅተው የቀረቡት የንግግር ክሂል ይዘቶች ከመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርተው ሳቢና ማራኪ በሆነ አቀራረብ ንዑሳን የንግግር ክሂሎችን ሊያዳብር በሚችል መልኩ የተማሪዎችን፣ የመምህራንንና የትምህርት ቤቶችን ሁኔታ ከግምት ውስጥ አስገብቶ፣ ተከታታይነቱንና ተለጣጣቂነቱን ጠብቆ፣ በቂ የንግግር ክሂል መለማመጃዎችን መያዙን እንመለከታለን::

4.6.1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመስርቶ ስለመዘጋጀቱ

ለዚሁ የክፍል ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ተዘጋጅቶለታል:: የተዘጋጀውም በሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ኢንስቲትዮት የቋንቋዎች ት/ሥ/ት/ ቡድን በ 1996 ዓ.ም ነው:: መርሐ

ትምህርቱ 27 ገጾች አሉት:: በውስጡ 26 ይዘቶች ይገኛሉ:: እነዚህን ይዘቶች ለማስተማር 117 ክፍለ ጊዜያት ተመድበዋል:: ለንግግር ክሂል ትምህርት የቀረቡት በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ተዘርዝረዋል::

ሠንረጠዥ አስራ አንድ:- በ3ኛ ክፍል መርሐ ትምህርት ውስጥ ለንግግር ክሂል ትምህርት የተመረጡ ይዘቶች

ተ.ቁ	የቋንቋ ትምህርት ክፍል	ዝርዝር ዓላማ	ይዘት	ክ/ጊዜ	ገጽ	ምርመራ
1	ንግግርና ጽሕፈት	ተጠያቂያዊ አስተሳሰብን ተጠቅመው የሁኔታዎችን ነገሮችን፣ የድርጊቶችን የጊዜ ቅደም ተከተል ይለያሉ	ተጠየቃዊ አስተሳሰብ የጊዜና የድርጊት ቅደም ተከተል	5	19-22	2 ለንግግር የቀረበ
2	ንግግርና ማዳመጥ	- ተጠያቂያዊ አካሄድ በመከተል - ሀሳብን በመደገፍና በመቃወም ይከራከራሉ	ልዩ ልዩ ተጠያቂያዊ የንግግር ሥርዓት መግለጫዎች - ውይይት - ክርክር	6	24-25	3 ለንግግር
3	ንግግር	አንድን ሀሳብ በራሳቸው አባባል ይገልጻሉ	አንድን ሀሳብ በራስ አባባል /ፓራፍሬዝ/ ማቅረብ	4	25-26	4 ለንግግር
	ድምር					9

ምንም እንኳ በሁለቱ የቋንቋ ትምህርት ክፍሎች ማለትም በተራ ቁጥር አንድና ሁለት የንግግር ክሂል ከጽሕፈትና ከማዳመጥ ጋር አብሮ የቀረበ ቢሆንም የመማር ማስተማር ክንዋኔዎችን በመመልከት በተራ ቁጥር 1 ሁለት፣ በተራ ቁጥር 2 ደግሞ ሦስት ክፍለ ጊዜያት ለንግግር ክሂል ሊመደብለት እንደሚችል መገንዘብ ተችሏል:: በዚህ መሠረት ለዓመቱ የተመደቡት የንግግር ክሂል ትምህርት ክፍለ ጊዜያት 9 ይሆናሉ:: ለዓመቱ ከተመደበው 117 ጠቅላላ ክፍለ ጊዜያት ውስጥ ከመቶ 7.69 እጁን (7.69%) ያህሉን ይይዛል ማለት ነው:: ይህ እንግዲህ በመርሐ ትምህርቱ ላይ የሚታየው ነው::

በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያለውን ሁኔታ የተመለከትን እንደሆነ በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትና ለንግግር ክሂል ማስተማሪያ የቀረቡት ይዘቶች ሙሉ በሙሉ ለንግግር ክሂል ማስተማሪያነት በመማሪያ መጽሐፉ የዋሉ አይደሉም:: ከንግግር ክሂል በበለጠ የጽሕፈት ክሂልን ለማስተማር የዋሉ ናቸው::

ለምሳሌ 1. "የጋቢዮን አሰራር ቅደም ተከተል ከባለሙያዎች በመጠየቅ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ካነበባችሁ በኋላ ተወያዩበት::" /ገጽ 61፣ መልመጃ ሶስት/

2. "... ዐረፍተ ነገሮቹ በሚገልጹት የድርጊት ቅደም ተከተል መሠረት አስተካክላችሁ ጻፉ::" /ገጽ 60፣ መልመጃ ሦስት/

3. “በተሰጣችሁ ጽሑፍ ውስጥ ያሉትን ፍሬ ሐሳቦች በራሳችሁ አባባል ጻፉ::”/ገጽ 31/

ከዚህ መረዳት የሚቻለው በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ ለንግግር ክሂል ተብለው የተመረጡት ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ሙሉ በሙሉ አለመቅረባቸውን ነው:: በሠንጠረዡ ውስጥ ከተመለከቱት ሦስት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች /ክፍሎች/ ውስጥ በተራ ቁጥር 2 የተመለከተውና ውይይት፣ ጭውውትና ክርክር ከሚሉት 3 ንዑሳን ይዘቶች ውጪ ያሉት በመማሪያ መጽሐፉ ለንግግር ክሂል ማስተማሪያነት አልዋሉም:: ስለዚህ ከተመረጡት ሦስት ይዘቶች ውስጥ አንድ ብቻ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለንግግር ክሂል ትምህርት ማስተማሪያነት ውሏል ማለት ነው:: ይህም 33.33% ብቻ ይይዛል:: ከዚህ መረዳት የሚቻለው መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ የቀረበ አለመሆኑን ነው::

4.6.2. የንግግር ክሂል ትምህርት መለማመጃ ይዘቶች በበቂ መጠነ ስለመዘጋጀታቸው

በመማሪያ መጽሐፉ የተዘጋጁት ይዘቶች የንግግር ክሂልን ለማዳበር የተመረጡ መለማመጃዎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ የሚያዳብሩ ሆነው ስለመዘጋጀታቸው ቀጥለን እንመለከታለን::

ከላይ በተገለጸው መሠረት ለ3ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ የተዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት የንግግር ክሂል ይዘቶች በመርሐ ትምህርቱ ተመሥርተው አለማቅረባቸውን ለመገንዘብ ተችሏል:: ቀጥሎ ደግሞ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርተው የቀረቡትና ከመርሐ ትምህርቱ ውጪ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተዘጋጅተው የቀረቡት የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎችን የንግግር ክሂላቸው እንዲዳብር ምን ያህል ረድተዋል? የሚለውንና ከሌሎቹ የቋንቋ ክፍለ ትምህርቶች አንጻር ምጥጥናቸው ምን ይመስላል? በበቂ ሁኔታ ተመርጠው ተደራጅተው ቀርበዋል? የሚሉትን እንመለከታለን:: የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የቋንቋ ትምህርት ክሂሎችን ለማዳበር የተመረጡትን መለማመጃዎች መጠን መለየት ያስፈልጋል:: ይህንን ለመለየት በሠንጠረዥ መዘርዘሩ አስፈላጊ ስለሆነ ቀጥለን እንዘርዝራቸዋለን::

ሠንጠረዥ አስራ ሁለት:- በሦስተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ክፍሎች መለማመጃ ጥያቄዎች መግለጫ

	የመለማመጃ ትምህርት ክፍል /ክሂል/	የጥያቄ ብዛት	ከመቶኛ የሚኖራቸው ድርሻ	የትኩረት ደረጃው	ምርመራ
1	ማዳመጥ	4	0.63%	5ኛ	
2	ንግግር	21	3.28%	4ኛ	
3	ንባብ	240	37.50%	2ኛ	
4	ጽሕፈት	87	13.59%	3ኛ	
5	ሰዋስው	288	45%	1ኛ	
6	ሥነ ጽሑፍ	0	0%	0	የለውም
7	ጠቅላላ	640	100%		

ከሠንጠረዡ ላይ መረዳት እንደሚቻለው ከተዘጋጁት 640 የመለማመጃ ጥያቄዎች ውስጥ ለንግግር ክሂል መለማመጃ የዋሉት 21 ናቸው ይህም ከጠቅላላው 3.28 እጁን (3.28%) ይይዛሉ:: ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ለንግግር ክሂል ትምህርት የተሰጠው ትኩረተ ወይም የልምምድ ሽፋን አናሳ መሆኑን ነው:: በአማካይ የመለመጃመጃ ጥያቄዎች ብዛት 106.67 ወይም ከመቶኛ ድርሻቸው 16.67% በጣም ያነሰ ነው:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ ሁለት "ረ"ን ይመልከቱ/::

4.6.3. የትምህርቱ ይዘቶች ሳቢና ማራኪ ስለመሆናቸው

በዚህ ክፍል ንዑሳን የንግግር ክሂሎችን ለማዳበር የሚያስችሉ መለማመጃዎች ሳቢና ማራኪ በሆነ መልኩ እንዲሁም የተማሪዎችን የመምህራንና የትምህርት ተቋማትን ሁኔታ አገናዝበው መቅረባቸውን እናያለን::

በመማሪያ መጽሐፉ ተዘጋጅተው ከቀረቡት 21 የመለማመጃ ጥያቄዎች ውስጥ በተረት መልክ የቀረቡ 4፣ በቡደን ውይይት 11፣ በክርክር 1፣ በተናጠል የሚቀርብ ንግግር 5 መሆናቸውን መረዳት ተችሏል:: የቀረቡት መለማመጃዎች ቁጥራቸው አናሳ ቢሆንም አቀራረባቸው የተማሪዎችን የንግግር ክሂሎች ከፍ ለማድረግ የሚያስችል ነው:: በተለይ የቡድን ውይይቶች በርከት ብለው ቀርበዋል:: ተረቶች፣ ክርክሮች፣ ጭውውቶች፣ ቃለ ምልልሶችን፣ ወዘተ. በበቂ ሁኔታ አልቀረቡም:: ጭውውቶችንና ቃለ ምልልሶችን የመሳሰሉት የንግግር ክሂል ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ አቀራረቦች አልተካተቱም:: በአጠቃላይ የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ መለማመጃዎች ቁጥራቸው አናሳ ከመሆኑም በተጨማሪ በአይነታቸውም ቢሆን ሁሉንም አይነት የንግግር ማቅረቢያ መንገዶች ያካተቱ አይደሉም::

የቀረቡት 21 የንግግር መለመጃመጃዎች ከተማሪዎች፣ ከመምህራንና ከትምህርት ተቋማት ዳራ አንጻር ተግባራዊ ለማድረግ ያለውን አመቺነት ስንመለከት ከተማሪዎች እድሜ፣ እውቀት፣ ጾታ፣ ወዘተ. አንጻር ትምህርቱን ለማቅረብ አስቸጋሪ የሚሆንበት ሁኔታ አይታይም::

ከመምህራን የስልጠና ሁኔታም የተመረጡትን የንግግር ትምህርቶች ለማቅረብ የሚችገሩበት ሁኔታ አይታይም:: የትምህርት ተቋማትም ቢሆንም እነዚህን መለማመጃዎች ተግባራዊ ለማድረግ የማያስችል ሁኔታ ያጋጥማቸዋል ተብሎ አይታሰብም:: ትምህርቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠይቅ የተጋነነ ወጪም ሆነ ቁሳቁስ አይጠይቅም::

4.6.4. የትምህርቱ ይዘቶች ተከታታይነት ተለጣጣቂነት ያላቸው ስለመሆኑ

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ አብዛኛዎቹ የንግግር ማለማመጃዎች የቡድን ውይይትን መሠረት አድርገው የቀረቡ ናቸው:: ሌላዎቹ በአነስተኛ ድግግሞሽ ወይም አንዱ ብቻ ተጠቅሰው የቀረቡበት ሁኔታ ይታያል:: ይህም ትምህርቱ ጥልቀት እያገኘና አይረሴ እየሆነ እንዲሄድ ለማድረግ ተለጣጣቂነት የጎደለው ይመስላል::

ከፊትና ከኋላ ባሉ የክፍል ደረጃዎች ማለትም በ2ኛና በ4ኛ ክፍሎች የተጠቀሱት ይዘቶችም ቢሆኑ በዝቅተኛ መጠን የቀረቡ በመሆናቸው ትምህርቱን በአጥጋቢነት ለማስረጽ የሚያስችሉ አይመስሉም:: ለዚህም ዋነኛው ምክንያተ በዝግጅቱ ወቅት በአጠቃላይ ለንግግር ክሂል የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን ነው::

4.6.5. የጽሑፍ መጠይቆች መልስ

ሀ. የአዘጋጆች መልስ

የጽሑፍ መጠይቆችን የሞሉት የደሴ መምህራን ኮሌጅ መምህራን ናቸው:: የሰጧቸው መልሶች የያዙት አጠቃላይ ሐሳብ እንደሚከተለው ቀርቧል::

1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ አለመዘጋጀቱንና በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተጠቀሱት የንግግር ክሂል መማሪያ ይዘቶች በበቂ መጠን አለመቅረባቸውን፣
2. የተመረጡት የንግግር ክሂል ማስተማሪያ ይዘቶቸ የተማሪዎችን የመምህራንና የትምህርት ተቋማትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ እነደሆነ እንዲሁም አቀራረቡ ሳና ማራኪነት ስላለው የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ማነሳሳት እንደሚችል፣
3. ይዘቶች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነትን በጠበቀ ሁኔታ አለመደራጀታቸውንና ይህም ትምህርቱን ለማስረጽ ችግር እንደሚያጋጠም ወዘተ. በመልሶቻቸው ገልጸዋል::

ለ. የመምህራን መልስ

ቀደም ሲል በተጠቀሱት ሦስት ወረዳዎች በሚገኙ ስድስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ለጽሑፍ መጠይቆቹ መልስ ሰጥተዋል:: /አባሪ ሦስት "ተ"ን ይመልከቱ/

የ12 መምህራን መልሶች የሚከተሉትን አራት አጠቃላይ ነጥቦች ይገልጻሉ

1. መማሪያ መጽሐፉ ሙሉ በሙሉ በመርሐ ትምህርቱ ተመሥርቶ እንዳልተዘጋጀና ከመርሐ ትምህርቱ ውጪ የተዘጋጁትም ይዘቶች ቢሆኑ የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ለማዳበር በበቂ መጠን እንዳልቀረቡ፣
2. የተመረጡት የንግግር ትምህርት ይዘቶች ሳቢና ማራኪነት ያላቸው በመሆናቸው የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት እንደሚያነሳሱ፣
3. የይዘቶች ተከታታያነትና ተለጣጣቂነቱ የላላ እንደሆነ፣
4. ትምህርቱን ተግባራዊ ለማድረግ የተማሪዎች የመምህራንና የትምህርት ተቋማት ሁኔታ አመቺ መሆኑን ገልጸዋል::

በዚህ መሠረት አዘጋጆቹና መምህራኑ የሰጡት መልስ በመጽሐፉ ግምገማ የተገኘውን ውጤት የሚያጠናክር ነው::

4.7. የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት አመራረጥ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ

የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ፣ በደብረ ብርሃን መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህራን ተሻሽሎ በ1997 ዓ.ም የተዘጋጀ ነው:: መጽሐፉ 90 ገጾች ያሉት ሲሆን በውስጡ በ19 ርዕሶች የተከፋፈሉ ምንባቦችና መልመጃዎች ተካተዋል:: መማሪያ መጽሐፉ ሲዘጋጅ የንግግር ክሂል ትምህርት አመራረጥ፣ አዘገጃጀትና አቀራረብ ምን እንደሚመስል መገንዘብ እንዲቻል በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ መዘጋጀቱን፣ አንጻራዊ በሆነ መልኩ በቂ የንግግር መለማመጃዎች መቅረባቸውን፣ ሳቢነትና ማራኪነት ባለው መልኩ ንዑሳነ የንግግር ክሂሎችን ማዳበር መቻላቸውን፣ የተማሪዎችን፣ የመምህራንንና የትምህርት ቤቶችን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ማስገባታቸውንና ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ባለው አካሄድ መቅረባቸውን እናያለን::

4.7.1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀ ስለመሆኑ

ለዚሁ የክፍል ደረጃ የቀረበው መርሐ ትምህርት በ/ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ኢንስቲትዩት በ1996 ዓ.ም የተዘጋጀ ነው:: 36 ገጾች ያሉት ሲሆን በእነዚህ ገጾች የተጠቀሱትን ይዘቶች ለማከናወን 131 ክፍለ ጊዜያት ተመድበዋል:: በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ የንግግር ክሂልን ለማስተማ የቀረቡትን ይዘቶችና ክፍለ ጊዜያት በሚቀጥለው ሠንጠረዥ እንመለከታለን::

ሠንጠረዥ አስራ ሶስት:- በ4ኛ ክፍል መርሐ ትምህርት ውስጥ የተጠቀሱ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች

ተ.ቁ	የቋንቋ ትምህርት ክፍል	ዝርዝር ዓላማ	ይዘት	ክ/ጊዜ	ገጽ	ምርመራ
1	ንባብ/ ማዳመጥና ንግግር	- የቃል ጽሑፉና የምልክት መመሪያዎችን ተረድተው ተግባራዊ ያደርጋሉ	ልዩ ልዩ መመሪያዎች	4	19-20	2 ክ/ጊዜያቶች ለንግግር
2	ንግግርና ጽሕፈት	- አንድን የንግግር ወይም የጽሑፍ ሀሳብ በራሳቸው አባባል ይገልጻሉ	ሀሳብን ከራስ አባባል መገለጽ/ ፖራፍሬዝ/	2	24	1 ክ/ጊዜያቶች ለንግግር
3	ማዳመጥና ንግግር	- ስርዓትን ጠብቀው ይጫወታሉ	ጭውውት	3	24-25	2 ክ/ጊዜያቶች ለንግግር
4	ማዳመጥና ንግግር	- ሥርዓትን ጠብቀው ይወያያሉ - በተሰጣቸው ርዕሰ ጉዳይ ተወያይተው መፍትሄ ያቀርባሉ - ሥርዓትን ጠብቀው ይከራከራሉ - በክርክር ሂደት እንደአቀራረባቸው አሸናፊ ወይም ተሸናፊ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገልፃሉ	- ውይይት - ክርክር	4	25-26	3 ክ/ጊዜያቶች ለንግግር ይመስላል
5	ንግግርና ጽሕፈት	- የተለያዩ ነገሮችን ተጠየቂያዊ በሆነ መልኩ ይወዳደራሉ - የድርጊትንና የጊዜን ቅደም ተከተል በተለያዩ ነገሮች አሰራር ይገልፃሉ - የመንስኤነና የውጤትን ግንኙነትና ልዩነት ይገልጻሉ - አንድን ነገር ተመልክተው ነው የሚል ወደመደምደሚያ ይለጣሉ - ይሆናል ወይም አይሆንም አያሉ ይደመድማሉ - አንድን ነገር ከሌላ ነገር ወይም ሁኔታ ጋር ያገናዝባሉ - በሀቅና በግል አስተያየት መንክል ያለውን ልዩነት አመልካች ምሳሌዎችን ያቀርባሉ	- ተጠያቂያው አገላለፅ - ማወዳደር - የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን በተለያዩ አሰራር - መንስኤና ውጤት - መደምደሚያ ውሳኔ ሀሳብ ላይ መድረስ - ማገናዘብ/ አናሎጂ - የሀቅና የግል አስተያየት መካከል ያለ ልዩነት ያብራራሉ	12	27-30	6 ክ/ጊዜያት ለንግግር ዝሂል
	ድምር			25		14

ከዚህ ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻው የንግግር ክሂል ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች ትምህርት ጋር የቀረበ ነው:: በመርሐ ትምህርቱ የተዘረዘሩትን ክንዋኔዎች በመፈተሽ ለንግግር ክሂል ሊውል የሚችለውን በመለየት ምርመራ በሚለው ረድፍ ተለይተው ሠፍረዋል:: ይህን መሠረት በማድረግ ከተሰጠው አጠቃላይ 131 ክፍለ ጊዜያት ውስጥ ለንግግር ትምህርት የዋለው ክፍለ ጊዜ 14 ነው:: ይህም ከመቶ ስሌት 10.68 እጁን (10.68%) ይይዛል:: ለስድስቱም የትምህርት ይዘቶች በአማካይ ሊደርስ ከሚችለው 21.83 ጥያቄ ብዛት ያነሰ ነው::

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱት የንግግር ክሂል ትምህርቶች ከመርሐ ትምህርት ተመሥርተው የቀረቡ መሆናቸውን፣ በመርሐ ትምህርት የተጠቀሱት የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ መጠቀሳቸውን ቀጥለን እንመለከታለን::

ስለዚህ መጀመሪያ ንግግርን ለማስተማር በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ የታቀዱት ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ መስፈራቸውን እንመልከት::

ሀ. በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ "ንግግርን ከንባብ ወይም ከማዳመጥ" ጋር ለማስተማር የቀረበው ይዘት "ልዩ ልዩ መመሪያዎች" የሚለው ነው:: ይህ ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ ከገጽ 28-32 "መመሪያን መከተል" በሚል አጭር ምንባብ ይጀምርና መልመጃዎች እንዲሠሩ ተደርጓል:: እነዚህ ጥያቄዎች /መልመጃዎች/ በአራት መልመጃዎች የተከፈሉ ናቸው ማለትም ከመልመጃ አሥራ አራት እስከ መልመጃ አሥራ ሰባት ያሉትን ያጠቃልላሉ:: የያዙትን ትዕዛዝ ቀጥሎን እንመልከት::

1. "መልመጃ አስራ አራት- በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::" ይልና 4 የምርጫ ጥያቄዎች ተሰጥተዋል:: በትክክል ማንበባቸውን ለማረጋገጥ የቀረበ ነው:: /ገጽ 28-29/
2. "መልመጃ አስራ አምስት- የሚከተለውን መመሪያ በጥንቃቄ አንብባችሁ ከሥሩ ያሉት ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ" ይልና ባለአንድ አንቀጽ ምንባብ ቀርቦ
   ሀ. "ከላይ ያለውን አንቀጽ መነሻ በማድረግ እንደመመሪያ የቀረቡትን ሐሳቦች ለይታችሁ በማውጣት ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ::
   ለ. በዘመኑ አስከፊ በሽታ ኤድስ ላለመያዝ የሚያስችል ሌላ ተጨማሪ መመሪያ ከጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን ጻፉና ለመምህራችሁ አንብቡላቸው::" /ገጽ 29/ በሁለቱም ጠያቄዎች እንዲለማመዱ የተፈለገው ጽሕፈትን ነው::
3. "መልመጃ አስራ አምስት- ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ጥያቄዎችን በትዕዛዛቸው መሰረት መልሱ::" /ገጽ 29-30/ ይላል:: ከዚህ ትዕዛዝ በኋላ 6 ጥያቄዎች ቀርበዋል::

1. "የትምህርት ቤታችሁን የጥፋተኛ ተማሪዎች የመቀጫ መመሪያ የምታውቁት ከሆነ በደብተራችሁ ላይ ጻፉት፣ የማታውቁተ ከሆነ ደግሞ ርዕሰ መምህራችሁን ጠይቃችሁ ጻፉና ለመምህራችሁ አንብቡላቸው::" ጽሕፈትን ለማለማመድ የቀረበ ነው::
2. "... በሽተኛው መድኃኒቱን ሐኪም ባዘዘው መሠረት ባይወስድ ምን ሊሆን እንሚችል ለመምህራችሁ አስረዱ::" በጽሑፍ ወይስ በንግግር አልተጠቆመም::
3. "ስለአንድ ... ጨዋታ ... መመሪያ በደብተራችሁ ላይ ጻፉ:: ..." ጽሕፈትን ለማለማመድ የቀረበ ነው::
4. "የክፍላችሁን ንጽህና መጠበቅ የሚያስችል መመሪያ በቡደን ሆናችሁ ጻፉ:: ..." ጽሕፈትን ለማለማመድ የቀረበ::

5. ጓደኞሞች ተዋደውና ተፋቅረው መኖር የሚያስችላቸውን መመሪያ በየግላችሁ ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻቸሁ አንብቡላቸው ... ጽህፈትን ለማለማመድ የቀረበ::
6. "... አበቦችንና አትክልቶችን እንዴት ማልማት እንደሚቻል የሚገልጽ መመሪያ በቡድን ሆናችሁ ጻፉ:: ..." ጽሕፈትን ለማለማመድ የቀረበ ነው::

ለ. "የሚከተሉትን ሥዕላዊ መመሪያዎች መሠረት በማድረግ ከሥራቸው ላሉት ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ::" /ገጽ 30-31/ ካለ በኋላ የምርጫ ጥያቄዎች ተሰጥተዋል:: የሚመለሱት በምን እንደሆነ አልተገለጸም::

ሐ. "ከላይ የቀረበውን የሥዕል መመሪያ ... እንዴት ማስረዳት እንደምትችሉ ለጓደኞቻችሁ ግለጹላቸው::" /ገጽ 31/ ንግግርን ለማለማመድ የቀረበ ይመስላል:: ምክንያቱም ለክፍል ጓደኞች የሚገልጽ ስለሆነ ለእያንዳንዱ በጽሑፍ ከመግለጽ በንግግር መግለጹ ቀላል ሆኖ ስለሚገኝ::

መ. "... በማስጠንቀቂያነት የሚጠቀምባቸውን ሶስት አባባሎች ... ጽፋችሁ ... አንብቡላቸው::" /ገጽ 31/ ጽህፈትን ለማለማመድ የቀረበ ነው::

ሠ. "መመሪያን ሳናከብር ሊመጣ የሚችልን አደጋ የሚገልጹ ሦስት አባባሎች ... ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ ... አንብቡላቸው::" /ገፅ 30/ ጽህፈትን ለማለማመድ የቀረበ ነው::

ረ. "ለክፍል ጓደኞቻችሁ ለታናሽ እህቶቻችሁና ወንድሞቻችሁ ... መመሪያዎችን በቡደነ ጻፉና ለመምህራችሁ አንብቡላቸው::" /ገጽ 31/ ጽህፈትን ለማለማመድ የቀረበ ነው::

"መልመጃ አስራ ሰባት- የሚከተሉተን ዐረፍተ ነገሮች በያዙት ሐሳብ መሠረት በማገጣጠም አንቀፅ ጻፉ::" /ገጽ 32/ በማለት መልመጃዎች ከቀረቡ በኋላ ለዚህ የቋንቋ ትምህርት ክፍል የተዘጋጀው ይጠናቀቃል:: ከተዘረዘሩት 27 ጥያቄዎች ውስጥ በግልጽ ለንግግር ትምህርት መሆኑ የተገለጸ ባይሆንም ወደዚያው የሚቀርበው አንድ መልመጃ ብቻ ነው:: ይኸውም ገጽ 31 መልመጃ አስራ ስድስት ሥር የቀረበው "ሐ" ነው:: ሌላዎቹ የጽሕፈት ክሂልን ለማዳበር የቀረቡ ናቸው:: ይህም ከመቶ እጅ 3.70 (3.70%) ብቻ ይይዛል::

ለ. ሁለተኛ ሆኖ በመርሐ ትምህርቱ የቀረበው ይዘት" ሐሳብን በራስ አባባል መግለጽ" የሚል ነው:: የጽሕፈት ክሂል ከንግግር ክሂል ጋር አብሮ የቀረበበት ክፍል ነው::

በመማሪያ መጽሐፉ ገጽ 48-49 መልመጃ አራት ላይ ቀርቧል:: ከመርሐ ትምህረቱ ላይ ለማውጣት እንደተቻለው ከመርሐ ትምህርቱ ተመሥርቶ የቀረበ ነው::

ለምሳሌ "የሚከተለውን ጽሑፍ በጥሞና አንብቡ:: ጽሑፉን ካነበባችሁ በኋላ በራሳችሁ አገላለጽ ታሪኩን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው::" /ገጽ 48፣ መልመጃ 24/ በሚል የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚያስችል መልኩ ቀርቧል::

ሐ. "ጭውውት" የሚለው ይዘተ በሦስተኛ ደረጃ ንግግርን ለማስተማር በመርሐ ትምህርቱ የቀረበ ነው:: የንግግር ክሂል ከማዳመጥ ክሂል ጋር እንዲዳብር ሆኖ የተዘጋጀበት ክፍል ነው:: በመርሐ ትምህርቱ የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች መሠረት ከተመደቡለት 4 ክፍለ ጊዜያት ውስጥ ለንግግር ክሂል ይሆናል ተብሎ የተገመተው 3 ክፍለ ጊዜ ነው::

ይህ የቋንቋ ትምህርት ክፍል በመማሪያ መጽሐፉ በገጽ 50 እና 51 ላይ ቀርቧል:: አባትና ልጅ ያደረጉት ጭውውት ከቀረበ በኋላ ለንግግር መለማመጃነት በተሰጠው መልመጃ አማካኝነት መልመጃ ሃያ ስድስተ ቁጥር 2 ላይ "ጥንድ ጥንድ በመሆን ከሚከተሉት ባንዱ ወይም እናንተ በመረጣችሁት ርዕሰ ጉዳይ ላይ በክፍል ውስጥ ጭውውት አድርጉ::

ሀ. በትምህርት ቤታችሁ ሥነ ሥርዓት ላይ፣

ለ. በእረፍት ጊዜያችሁ በምትሠሩትሥራ ላይ፣

ሐ. በክፍላችሁ ንጽህና አጠባበቅ ላይ፣

መ. በምትወዱት የትምህርት አይነት ላይ፣"

ተማሪዎች የንግግር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ በሚረዳ መልኩ ተሰናድቷል::

ስለዚህ ይህ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረበው ይዘት በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀ መሆኑን መረዳት ይቻላል::

መ. "ውይይትና ክርክር" በሚል የቀረበው የተማሪዎችን ማዳመጥና የንግግር ክሂል ለማዳበር በመርሐ ትምህርቱ የተዘጋጀው በመማሪያ መጽሐፉ ከገጽ 52 እስከ 53 ቀርቧል:: ተማሪዎች የውይይት የክርክር ሥርዓቶችን ጠብቀው እንዲወያዩና እንዲከራከሩ መልመጃዎች ተሰጥተዋል:: ገጽ 52 መልመጃ ሃያ ሰባት ተራ ቁጥር ላይ

"ከሚከተሉት ርዕሶች መካከል በአንዱ ላይ በቡድን ሆናችሁ ከዚህ በፊት ስለውይይት በተማራችሁት መሠረት ተወያዩ::

ሀ. የትምህርት ቤታችንን ንብረት እንዴት በጥንቃቄ መያዝ ይቻላል?

ለ. በአካባቢያችሁ የሚገኙ አቅመ ደካሞችን እንዴት መርዳት እንችላለን?

ሐ. የእረፍት ጊዜያችንን እንዴት እናሳልፍ?

መ. በአካባቢያችን ያለን የደን መመናመን እንዴት መከላከል ይቻላል?

ሠ. በአካባቢያችን የሚገኙ አሳሳቢ በሽታዎችን እንዴት መከላከል ይቻላል?"

እነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎች ውይይትን ለማድረግ የሚረዷቸው ሲሆኑ ክርክርን ለማካሄድ የሚያሟቸው ደግሞ ገጽ 53፣ መልመጃ ሃያ ሰባት፣ ተራ ቁጥር 2 ላይ፣

"ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ ወይም ራሳችሁ በመረጣችሁት ርዕስ ከተዘጋጃችሁ በኋላ በክፍል ውስጥ ክርክር አካሂዱ::

ሀ. ከገበሬና ከወታደር አገሩና የሚጠቅም ማነው?

ለ. ከሴት ልጅና ከወንድ ልጅ ወላጅን ይበልጥ የሚያገለግል ማነው?

ሐ. ከዕውቀትና ከሀብት የቱን ትመርጣለህ?

መ. ለአገር ልማት የሚጠቅመው መንገድ ወይስ ውሃ?" የሚሉ ጥያቄዎች ከቀረቡ በኋላ የውይይቱንና የክርክሩን ሥርዓት የሚገልጽ ማስታወሻዎች ከየመልመጃዎች ግርጌ ተቀምጠዋል::

ሠ. በመርሐ ትምህርቱ የንግግር ክሂል ለማስተማር የተመረጠው 12 ክፍለ ጊዜያት የተመደበለት "ተጠየቃዊ አስተሳሰብ" የሚል ነው:: በዚህ ክፍል የንግግር ክሂል ከጽሕፈት ክፍል ጋር በአንድ ላይ የቀረበበት ነው::

በዚህ የቋንቋ ትምህርት ክፍል /በንግግር/ ተማሪዎች እንዲያዳብሩ የሚፈልገው ሐሳቦችን እንዲያወዳድሩ የአሠራር ቅደም ተከተልን እንዲገልጹ የመንስኤና የውጤተ ግንኙነትና ልዩነትን እንዲያብራሩ ወዘተ ነው:: ይህን በመርሐ ትምህርቱ የተቀመጠው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በትክክል መቀመጡን ስንፈትሽ የሚከተለውን ውጤት እናገኛለን::

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ "ተጠየታዊ አስተሳሰብ"ን በተመለከተ መቅረብ የሚጀምረው ከገጽ 54፣ መልመጃ ሃያ ስምንት ነው:: ከተጠቀሰው ገጽና መልመጃ ጀምሮ የሚቀርቡትን ጥያቄዎች የንግግር ክሂልን ከፍ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርተው መዘጋጀታቸውን ስንመለከት ውጤቱ የሚከተለውን ይመስላል::

ለምሳሌ:-

1. "ከሚከተሉት ጥንድ ጥንድ ሐሳቦች መካከል ሁለቱን መርጣችሁ በምሳሌው መሠረት እያወዳደራችሁ እያነጻጸራችሁ በጽሑፍ ግለጹ::" /ገጽ 54፣ መልመጃ 28/
2. "የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በጽሑፍ መልሱ::" /ገጽ 57፣ መልመጃ ሃያ ዘጠኝ/
3. "በሚከተለው ምሳሌ መሠረት ቀጥሎ የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮች መንሥኤና ውጤት ለይታችሁ ጻፉ::" /ገጽ 58፣ መልመጃ ሰላሳ፣ ቁጥር 2/

4. “ከዚህ ቀጥሎ ጥንድ ጥንድ ሐሳቦች ቀርበዋል:: እነዚህ ጥንድ ጥንድ ሐሳቦች በምን በምን እንደሚመሳሰሉና እንደሚለያዩ በጽሑፍ ግለጹ::” /ገጽ 60፣ መልመጃ ሰላሳ አንድ፣ ቁጥር 2/

እነዚህ እንግዲህ የንግግርና የጽሕፈት ክሂሎችን ለማዳበር የተመረጡ ይዘቶች ውስጥ የተመረጡ መልመጃዎች ናቸው:: ከ1-4 የተዘረዘሩትን ትዕዛዞች ስንመለከት ሁሉም የጽሕፈት ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ናቸው:: ከተጠቀሱት ውጪ ያሉትም የእነዚህ ዓይነቶች ናቸው::

ከዚህ በላይ ከተራ ፊደል ሀ-ሠ በተዘረዘሩት የንግግር ክሂልን ለማዳበር በመርሐ ትምህርቱ የቀረቡና በመማሪያ መጽሐፉ ይካተታሉ ተብለው የሚታሰቡ ናቸው:: ይሁን እንጂ የመማሪያ መጽሐፉንና መርሐ ትምህርቱን አቀራረብ ስንመለከት

1. በመርሐ ትምህርቱ መሠረት በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት በሠንጠረዡ

   ተራ ቁጥር 2 የተመደበለት ክፍለ ጊዜ 1

   ተራ ቁጥር 3 የተመደበለት ክፍለ ጊዜ 2

   ተራ ቁጥር 4 የተመደበለት ክፍለ ጊዜ 3

   ድምር 6

2. በመርሐ ትምህርቱ መሠረት በመማሪያ መጻሐፉ ያልቀረበት በሠንጠረዡ

   ተራ ቁጥር 1 የተመደበለት ክፍለ ጊዜ 2

   ተራ ቁጥር 5 የተመደበለት ክፍለ ጊዜ 6

   ድምር 8

ከይዘቶቹ ብዛት አንጻር መርሐ ትምህርቱን መሠረት አድርገው የተዘጋጁት 3 መርሐ ትምህርቱን መሠረት ሳያደርጉ የቀረቡት ደግሞ 2 ቢሆኑም በርካታዎቹን የመማር ማስተማር ክፍለ ጊዜያት የሚሸፍኑት መርሐ ትምህርቱን መሠረት ያላደረጉ በመሆናቸውና ከመቶው 57.14 (57.14%) እጁን ስለሚይዙ ማለትም ከግማሽ በላይ ስለሆኑ የመማሪያ መጽሐፉ መርሐ ትምህርቱን ሙሉ በሙሉ መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ አይደለም ብሎ መደምደም ይቻላል::

4.7.2. የንግግር ክሂል መለማመጃዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በበቂ መጠን ስለመቅረባቸው

በዚህ ክፍል በመማሪያ መጽሐፉ የተዘጋጁ መልመጃዎች የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር ምን ያህል በበቂ መጠን ተዘጋጅተዋል የሚለውን በማንሳት ከሌሎች የቋንቋ ትምህርት ክፍሎች ጋር በማነጻጸር የተሰጠውን ትኩረት ለማየት ተሞክሯል:: የቀረቡት መልመጃዎች የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚረዱትን ንዑሳን የንግግር ክሂሎች ለማጎልበት

የሚያስችሉ መሆናቸውንና የተማሪዎችን፣ የመምህራንና የትምህርት ተቋማት ዳራ ባገናዘበ መልኩ መዘጋጀታቸውን ጭምር ፍተሻ ተደርጓል::

በዚህ መሠረት የተጠቀሱትን ነጥቦች መነሻ በማድረግ በሚከተለው መልኩ መጽሐፉ ተፈትሿል::

ከሌሎች የቋንቋ የትምህርት ክሂሎች አንጻር የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚያስችሉ መልመጃዎች በምን ያህል መጠን ተዘጋጅተዋል? የክሂሎቹን መለማመጃ ጥያቄዎች ብዛት በማወዳደርና የትኛው የበለጠ ትኩረት እንደተሰጠው በማነጻጸር ማዳመጥ፣ ንባበ፣ ጽሕፈት፣ ሰዋስውና ሥነጽሑፍ ከንግግር ክሂል አንጻር ያላቸውን የአቅርቦት መጠን ማየት ያስፈልጋል:: ስለዚህ በየመለማመጃዎቹ የትኛው የክሂል ዘርፍ ተደጋግሞ እንደመጣ ለመለየት እንዲቻል በሠንጠረዥ ለማሳየት ተሞክሯል::

ሠንጠረዥ አስራ አራት:- በሶስተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ክፍሎች መለመጃመጃ ጥያቄዎች

	የመለማመጃ ትምህርት ክፍል /ክሂል/	የጥያቄ ብዛት	ከመቶኛ የሚኖራቸው ድርሻ	የትኩረት ደረጃው	ምርመራ
1	ማዳመጥ	3	0.71%	6ኛ	
2	ንግግር	28	6.64%	5ኛ	
3	ንባብ	192	54.49%	1ኛ	
4	ጽሕፈት	91	21.56%	2ኛ	
5	ሰዋስው	73	17.78%	3ኛ	
6	ሥነ ጽሑፍ	33	7.82%	4ኛ	
7	ጠቅላላ	422	100%		

የእነዚህ የስድስቱ የቋንቋ ትምህርት ክሂሎች የተመደበላቸው ክፍለ ጊዜያት 422 ሲሆኑ አማካዩ ደግሞ 70.33 ክፈለ ጊዜያት ይሆናል:: ማዳመጥ፣ ንግግርና ሥነ ጽሑፍ ከአማካይ በታች የሆኑ የመለማመጃ ጥያቄዎች የቀረቡባቸው ናቸው::

ንግግርን ለማለማመድ የተዘጋጁት ጥያቄዎች በአጠቃላይ 28 ናቸው:: ከመቶው እጅ 6.64 /6.64%/ እጁን ብቻ የያዙ ናቸው:: ይህ የሚያመለክተው የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚያግዙ መለማመጃዎች በበቂ መጠን ተዘጋጅተው አለመቅረባቸውን ነው:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ ሁለት "ሰ" ን ይመልከቱ/

ከሌሎች የቋንቋ ክፍለ ትምህረቶች አንጻር ማዳመጥን ሳይጨምር ዝቅተኛውን 6.64% የያዘው ንግግር ነው:: ይህ የሚያሳየው ለንግግር ትምህርት የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ መሆኑን ነው::

4.7.3. የትምህርቱ ይዘቶችን ሳቢነትና ማራኪነት በተመለከተ

የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ከፍ ለማድረግ በቋንቋ ትምህርቱ ውስጥ ሳቢነትና ማራኪነት ያላቸው ሐፍረትን የሚያስወግዱ መለማመጃዎች በውይይት፣ በክርክር፣ በቃለ

ምልልስ፣ በጭውውት፣ በተረት፣ ወዘተ. መልክ መቅረብ ያለባቸው መሆኑንና ሲቀርቡም የተማሪዎችን፣ የመምህራንና የትምህርት ተቋማትን ሁኔታ ያገናዘቡ መሆን እንዳለባቸው ቀደም ባሉት ክፍሎች በተለይም በክለሳ ድርሳኑ ላይ ተጠቅሷል። ስለዚህም የመማሪያ መጽሐፉ እነዚያን ሁኔታዎች ያሟላ መሆን አለመሆኑን በዚህ ክፍል እንመለከታለን።

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ከፍ ለማድረግ የሚረዱ 28 የመለማመጃ ጥያቄዎች መቅረባቸውን ተመልክተናል። ከእነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ የንግግርን ንዑሳን ክሂሎች ለማዳበር የሚረዱትና በውይይት፣ በክርክር፣ በቃለ ምልልስ፣ በጭውውትና በተረት ወዘተ. መልክ ተዘጋጅተው የቀረቡት

1. በገጽ 27፣ መልመጃ 13፣ በተራ ቁጥር 6 ላይ የተጠቀሰው "የሚከተሉትን ተግባራት በተሰጣቸሁ መመሪያ መሠረት በክፍል በጋራ አከናውኑ።"
2. በገጽ 31፣ መልመጃ 16፣ ፊደል "ሐ" ላይ የተጠቀሰው "ከላይ በቀረበው የሥዕል መመሪያ ዓይነት በመመሥረት በቀላሉ ሊረዱ የማይችሉ ሰዎችን እንዴት ማስረዳት እንደምትችሉ ለጓደኞቻችሁ ግለጹላቸው።"
3. በገጽ 33፣ መልመጃ 15፣ ቁጥር 3 ላይ "መጻሕፍት ቤት መግባትና ማንበብ በሚሰጠው ጥቅም ላይ በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ።"
4. በገጽ 51፣ መልመጃ 26፣ በተራ ቁጥር 2 "ጥንድ ጥንድ በመሆን ከሚከሉት ባንዱ ወይም እናንተ በመረጣችሁት ርዕስ ላይ በክፍል ውስጥ ጭውውት አድርጉ።"
5. በገጽ 52፣ መልመጃ 27፣ በተራ ቁጥር 1 ላይ "ከሚከተሉት ርዕሶች መካከል በአንዱ ላይ በቡድን ሆናችሁ ከዚህ በፊት ስለውይይት የተማራችሁት መሠረት ተወያዩ።" /5 መለማመጃዎችን የያዘ/
6. በገጽ 53፣ መልመጃ 27፣ ተራ ቁጥር 2 ላይ "ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ ወይም በመረጣችሁት ርዕስ ከተዘጋጃችሁ በኋላ በክፍል ውስጥ ክርክር አካሂዱ።" /4 መልመጃዎች የያዘ/ የሚሉት ናቸው። እነዚህ መለማመጃዎች በቁጥር 15 ናቸው። አጠቃላይ የንግግር ክሂል መለማመጃዎች 28 ናቸው። ከ28 ውስጥ 15ቱ የተማሪዎችን ንዑሳን የንግግር ክሂሎች ለማዳበር በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅተው የቀረቡ ናቸው። ከቁጥር አንጻር /ከ28ቱ/ ሲታይም ከግማሽ በላይ ናቸው። ከመቶኛ ስሌት ሲሰሉም 53.57 እጁን /53.57%/ ይይዛሉ።

ስለዚህ በመጽሐፉ ውስጥ ተዘጋጅተው የቀረቡት የተማሪዎች ንዑሳን የንግግር ክሂል ለማዳበር የሚረዱት መለማመጃዎች ሙሉ በሙሉ በቂ ናቸው ማለት የሚቻል አይመስልም።

የቀረቡት መልመጃዎች የተማሪዎችን፣ የመምህራኑንና የትምህርት ተቋማትን ዳራ ያገናቡ ከመሆናቸው አንፃር ሲታይ ምን ይመስላል? የሚለውን ደግሞ በመቀጠል እንመለከታለን::

ከላይ ንዑሳን የንግግር ክሂሎችን ማዳበር የሚያስችሉ ናቸው ተብለው በምሳሌነት የተጠቀሱትንም ሆነ ከዚያ ውጪ ሆነው ያልተጠቀሱትን ስንመለከት ከተማሪዎች፣ ከመምህራንና ከትምህርተ ተቋማት ዳራ ውጪ የሆኑ አይደሉም:: ከተማሪዎች ዕውቀት፣ ዕደሜ፣ ገጠመኝ፣ ከመምህራን የስልጠና ሁኔታ፣ ከትምህርት ተቋማት የውስጥ ድርጅት አቋም አንጻር ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪዎች አይደሉም:: ሁሉም በእነዚህ ሶስት ክፍሎች ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ::

4.7.4. የንግግር ክሂል የትምህርቱ ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተከታታይነትንና ተላጣጣቂነትን በተመለከተ

በዚህ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የንግግር ክሂል መለማመጃዎች የቡድን ውይይቶች 13፣ በተናጠል የሚቀርቡ ንግግሮች 6፣ ጭውውቶች 4፣ ክርክሮች 4 ናቸው:: ከእነዚህ ውስጥ ባለፉት የክፍል ደረጃዎች ተጠቅሶ በዚህ የክፍል ደረጃ እንደ ቃለ ምልልስና ተረቶች የመሳሰሉት የንግግር ክሂልን ለማጎልበት የሚረዱ የንግግር ማቅረቢያዎች አልተጠቀሱም::

ስለዚህ የመማሪያ መጽሐፉ ዝግጅት የይዘቶችን ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ጠብቆ ከመደራጀት አንጻር ብዙ ጠንካራ ጎኖች ያሉት መሆኑን መገንዘብ ቢቻልም የተሟላ አይመስልም::

4.7.5. የጽሑፍ መጠይቆች መልስ

ለጽሑፍ መጠይቆቹ መልስ የሰጡት በደብረ- ብርሃን መምህራን ኮሌጅ የሚያስተምሩ አንድ አዘጋጅና ጥናቱ በሚያተኩርባቸው ሦስት ወረዳዎች በስድስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ 12 ተተኳሪ መምህራን ናቸው:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ አራት እና አምስትን ይመልከቱ/::

ሀ. የአዘጋጅ መልስ

1. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተዘጋጁት የንግግር ክሂል መማሪያ ይዘቶች በመርሐ ትምህርቱ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውንና የተማሪዎችን፣ የመምህራንና የትምህርተ ተቋማትን ዳራ ከግምት ውስጥ አስገብተው የቀረቡ እንደሆኑ፣

2. አቀራረባቸው ሳቢና ማራኪነት ያላቸው በመሆኑ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ማነሳሳት የሚችሉ እንደሆኑ፣
3. የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ሊያዳብሩ የሚችሉ የንግግር ትምህርት ይዘቶች በመጽሐፉ ውስጥ በበቂ መጠን እንደቀረቡ፣
4. የተመረጡት ይዘቶች ተማሪዎችን በልዩ ልዩ የንግግር ክሂል መለማመጃዎች እንዲሳተፉ የሚያደርጉ ተግባራትን ይዘው እንደቀረቡ አዘጋጅዋ መልሰዋል::

ለ. የመምህራን መልስ

1. በመማሪያ መጽሐፉ የተዘጋጁት የንግግር ክሂል መማሪያ ይዘቶች መርሐ ትምህርቱን መሰረት በማድረግ እንደተዘጋጁና የተማሪዎችን፣ የመምህራንና የየትምህርት ቤቶችን ሁኔታ ከግምት ውስጥ እንዳስገቡ፣
2. የአቀራረባቸው ሁኔታ ሳቢና ማራኪ በመሆኑ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ማነሳሳት እንደሚችሉ፣
3. በመጽሐፉ ውስጥ ተመርጠው የቀረቡት የንግግር ክሂል መለማመጃዎች አናሳ እንደሆኑ፣
4. መለማመጃዎች ቁጥራቸው አናሳ ቢሆንም ተማሪዎችን በልዩ ልዩ የንግግር ተግባራት በማሳተፍ የንግግር ችሎታቸውን ከፍ ለማድረግ የሚረዱዋቸው መሆናቸውን ገልጸዋል::

እነዚህን ከአዘጋጅዋና ከመምህራኑ የተሰጡትን መልሶች ከመማሪያ መጽሐፉ የግምገማ ውጤት ጋር ስናስተያያቸው ተደጋጋፊ አለመሆናቸውን እንገነዘባለን:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ ሶስትን ይመልከቱ/::

4.8. ከደረጃ 1-3 እና ከ1-4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ ተተኳሪ አመቻቾችና መምህራን ዳራ

ተተካሪ አመቻቾቹና መምህራኑ የተመረጡት በአማራ ብሄራዊ ክልል፣ በሰሜን ወሎ ዞን፣ በተመረጡ ሶስት ወረዳዎች /በሀብሩ በቆቦና በግዳን/ በሚገኙ በተመረጡ 5 አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች እና 6 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነው:: አጠቃላይ ዳራቸው ቀጥሎ ቀርቧል::

የአመቻቾቹና የመምህራኑ የትምህርት ደረጃ 10+1 ወይም 12+1 የማስተማር ስልጠና ያላቸው ናቸው:: የአገልግሎት ዘመናቸውም ከአንድ አመት እስከ 30 ዓመት የሚደርስ ነው::

አጠቃላይ ቁጥራቸው 76 ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች አመቻቾች 20 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን ደግሞ 56

ናቸው:: በአንድ ት/ቤት በየክፍል ደረጃዎቹ የተተካሪ መምህራን ቁጥር የሚለያይበት ምክንያት በዚያ ትምህርት ቤት በየክፍል ደረጃው የሚኖሩ መማሪያ ክፍሎች (Sections) ብዛት ምክንያት ነው::

ለምሳሌ ፊኖኖ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 1ኛ ክፍል ሁለት መምህራን ተተካሪ ሆነዋል:: 2ኛ ክፍል አንድ መምህር ብቻ ተተካሪ ሆኗል:: 3ኛ ክፍል ደግሞ ሁለት መምህራን ተተካሪ ሆነዋል:: የዚህ የቁጥር መለያየት ምክንያቱ በዚያ ት/ቤት 1ኛና 3ኛ ክፍሎች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት መማሪያ ክፍሎች አሏቸው:: 2ኛ ክፍል ግን የተማሪዎቹ ቁጥር አናሳ በመሆኑ ያለው መማሪያ ክፍል አንድ ብቻ ነው:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ አራት "ሀ"ን ይመልከቱ/::

4.9. በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ ሥር በሚገኙ ትምህርት ተቋማት የሚያገለግሉት /ከደረጃ 1-3/ እና /ከ1-4ኛ ክፍል/ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትን ያዘጋጁ ባለሙያዎች ዳራ

በመማሪያ መጻሕፍቱ እንደተገለጸው አዘጋጆቹ የደሴና ደብረ ብርሃን መምህራን ኮሌጅ መምህራን ናቸው:: አጥኝው ቃለ መጠይቆችን ሲሰበስብ በወሎ ዩኒቨርስቲም አንዲት አዘጋጅ ለማግኘት ችሏል:: የትምህርት ደረጃቸው ከመጀመሪያ እስከ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ይገኙበታል:: የሥልጠና መስካቸውም በተመለከተ አንድ በፔዳጎጂ፣ አንድ በሥነ ልሳን፣ አንድ በእንግሊዝኛ በዋና ትምህርት የተማሩ ሲሆኑ ሌሎቹ አማርኛን በዋና ትምህርት የተማሩ ናቸው::

መማሪያ መጻሕፍቱን ካዘጋጁት ውስጥ የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉት ሰባት ብቻ ናቸው:: በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች የሚያገለግሉትን በማዘጋጀታቸው ምክነያት ግን 19 የሆኑ ይመስላሉ:: በተለይ የደሴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅና ወሎ ዩኒቨርስቲ መምህራን ከደረጃ 1-3 እና 1ኛና 3ኛ ክፍል ላይ በተደጋጋሚ ተጠቅሰዋል::

ያገልግሎት ዘመናቸው ዝቅተኛው ዓመት 4 ሲሆን ከፍተኛው 33 ዓመት ነው:: በዕደሜም ደረጃ ከ28-52 ዓመት ይገኙበታል:: ከባለ 4 ዓመቱ ባለገልጋሎት ዘመን ቀጥሎ ዝቅተኛው ያገልግሎት ዘመን 15 ዓመት ነው:: አብዛኛዎቹ ወይም ስድስቱ ከ15-33 ዓመት ባለው የግልጋት ዘመን የሚጠቃለሉ ናቸው::

በዝግጅቱ ከተሳተፉት መምህራን ውስጥ 4ቱ በሌሎች የክፍል ደረጃዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት እንደተሳተፉ ገልጸዋል::

በዚህም መሠረት እነዚህ ሁሉ ተዳምረው አዘጋጆቹ ጥሩ የዝግጅትና የሥራ ተሞክሮ ያላቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል:: /ለበለጠ መረጃ አባሪ አምስት "ሀ" እና "ለ"ን ይመልከቱ/::

4.10. የመማሪያ መጻሕፍቱ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀት እና አቀራረብ በቃት በንጽጽር ሲተነተን

4.10.1. ደረጃ 1 ከ1ኛ እና 2ኛ ክፍሎች ጋር ሲነጻጻር

በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መርሐ ግብር ደረጃ አንድን ያጠናቀቀ ተማሪ በመደበኛው መረሀ ግብር 3ኛ ክፍል መግባት ስለሚችልና የ1ኛና የ2ኛ ክፍል ደረጃዎችን የሚመጥን ትምህርት በደረጃ አንድ ውስጥ አግኝቷል ተብሎ ስለሚታሰብ የ1ኛና የ2ኛ ክፍሎች መማሪያ መጻህፍት ከደረጃ 1 ጋር ይነጻጸራሉ (Amhara Regional Education Bureau 2003:11)::

በዚህ መሠረት የንግግር ክሂልን ትምህርት አመራረጥ አደረጀጀትና አቀራረብ በተመለከተ ንጽጽሩ የተካሄደው ደረጃ 1 ከ 1ኛና 2ኛ ክፍሎች ጋር ነው::

በተደረገው የእያንዳንዱ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ መሠረት በደረጃ አንድ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከሚከተሉት ማጠቃለያዎች ላይ ለመድረስ ተችሏል::

1. በሚቀርቡት የተለያዩ መሥፈርቶችና መገምገሚያዎች መሠረት በተገኘው ማጠቃለያ የደረጃ 1 የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀ ነው::
2. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚረዱት መለማመጃዎች ከሌሎች የቋንቋ ትምህርት ክፍሎች አንጻር ሲታይ በበቂ መጠን አልቀረቡም::
3. ምንም እንኳ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ መለማመጃዎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ቢሆኑም እነዚህ የተመረጡበትን፣ የተደራጁበትንና የቀረቡበትን ሁኔታ ስንመለከት አጥጋቢ ባይሆንም ሳቢነትና ማራኪነት ባለው መልኩ፣ የተማሪዎችን ንዑሳን የንግግር ክሆሎች ሊያዳብሩ በሚችልበት አቀራረብ፣ እንዲሁም የተማሪዎችን የመምህራንንና የትምህርት መስጫ ተቋማትን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የተመረጡ፣ የተደራጁና የቀረቡ ናቸው::

4. በመጽሐፉ የተናጠል ግምገማ እንደተገለጸው ከመማሪያ መጽሐፉ ቀድሞ የተዘጋጀ የክፍል ደረጃ መጽሐፍ የለም፤ ይሁን እንጅ በመጽሐፉ ውስጥና በቀጣዩ ደረጃ 2 ከመማሪያ መጽሐፉ ጋር የይዘቶች ተከታታያነትና ተለጣጣቂነት የተጠበቀ ነው::

በ1ኛና በ2ኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የታዩ የንግግር ክሂል ትምህርት መለማመጃዎች የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ የታዩ ማጠቃለያ ገጽታዎች በሚከተለው መልክ ቀርበዋል::

1ኛ ክፍል

1. የንግግር ክሂልን ለማዳበር የቀረቡት ይዘቶች በመርሐ ትምህርቱ ላይ የተመሠረቱ አይደሉም::
2. በዚህ የክፍል ደረጃ የንግግር ክሂል ትምህርት ትኩረት አልተሰጠውም:: ተማሪዎች በጭውውት፣ በተረት፣ በእንቆቅልሽ፣ በእንካስላንቲያ... አማካኝነት ንግግርን እንዲማሩ አልተደረገም::
3. የንግግር ክሂልን ለማዳበር ይረዳሉ ተብለው የቀረቡት መልመጃዎች በጣም አናሳ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በዚህ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ሕጻናትን ስሜት ሊስቡ የሚችሉ እንደ እንቆቅልሽ፣ እንካሰላንቲያና ሚና ጨዋታ ያልቀረቡበት በመሆኑ ትምህርቱ ሳቢነትና ማራኪነት የለውም:: ንዑሳን የንግግር ክሂሎችን ለማዳበር የሚያስችሉ መለማመጃዎችም የሉትም:: የተማሪዎችን፣ የመምህራንና የትምህርት ቤቶችን ሁኔታ አገናዝበው ከመቅረብ አንጻር የቀረቡትን ብቻ ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻል ይመስላል::
4. ተከታታይነትና ተለጣጣቂነታቸው በተመለከተም በሚቀጥሉት ክፍሎች በዚህ ክፍል ደረጃ የተነሱት ይዘቶች የሚገኙ ቢሆንም በራሱ በመጽሐፉ ውስጥ ያላቸው ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ግን የላላ ነው::

2ኛ ክፍል

1. በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱት የንግግር ክሂልን ለማዳበር ተዘጋጅተው የቀረቡት ይዘቶች ሙሉ በሙሉ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ አልተካተቱም:: መርሐ ትምህርቱን ሙሉ በሙሉ መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ መማሪያ መጽሐፍ አይደለም::
2. በዚህ የክፍል ደረጃ የንግግር ክሂልን ለማዳበር የተመረጡት መለማመጃዎች ቁጥር ከንባብና ከሰዋስው መለማመጃ ጥያቄዎች ቁጥር አንጻር ሲታይ አናሳ ቢሆንም

ለትምህርት ክፍሎች ሊደርስ ከሚችለው አማካይ የመለማመጃ ጥያቄዎች ቁጥር አንጻር በቂ የመለማመጃ ጥያቄዎች የቀረቡበት ነው::

3. የቀረቡት የንግግር መለማመጃ ይዘቶች ሰቢና ማራኪ በመሆናቸው የተማሪዎችን ንዑሳን የንግግር ችሎታዎች ለማዳበር የሚረዱ ናቸው::
4. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የንግግር ክሂልን ለማዳበር የተደራጁት መለማመጃዎች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ይታይባቸዋል::

እነዚህንና ከተተኳሪ መምህራንና አመቻቾች እንዲሁም መጻሕፍቱን ከአዘጋጁት የትምህርት ባለሙያዎች በተሰበሰቡት መረጃዎች መሠረት

1. ለአንደኛ ክፍል የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አጥኚው በመስፈርትነት ያወጣቸውን መመዘኛ ነጥቦች በሙሉ አያሟላም::
2. በሁለተኛ ክፍል የተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ በንጽጽሩ ተራ ቁጥር አንድ ከተጠቀሰው ውጪ ያሉትን መመዘኛዎች በሙሉ ያሟላል::
3. ለደረጃ አንድ የተዘጋጀው መጽሐፍ በንጽጽሩ ቁጥር 2 ከተጠቀሰው ውጪ ያሉትን መመዘኛዎች በሙሉ ያሟላል::

ስለዚህ የ1ኛና የሁለተኛ ክፍል በአንድ ወገን ስለሚታዩና የ1ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ መመዘኛዎቹን በሙሉ ያላሟላ በመሆኑ የ2ኛ ክፍልንም ወደ እሱ ይጎትተዋልና የደረጃ 1 የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አንጻራዊ በሆነ መልኩ የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚያስችል የተሻለ የንግግር ክሂል ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ይታይበታል::

4.10.2. ደረጃ 2 ከ3ኛ ክፍል ጋር ሲነጻጸር

ለደረጃ 2 በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በዚህ ጥናት የታዩ ገጽታዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል::

1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀ ነው::
2. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተዘጋጅተው የቀረቡት የንግግር ክሂል መለማመጃዎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ በበቂ መጠን የቀረቡ ናቸው ሲባል ከሁሉም የትምህርት ክፍሎች በበለጠ ሁኔታ ቀርቧል ለማለት አይደለም:: የቀረበው ከንባብና ከሰዋስው ትምህርት ክፍሎች ቀጥሎ በ3ኛ ደረጃ ነው:: ነገር ግን በሁሉም ትምህርት ክፍሎች የቀረቡት መለማመጃ ጥያቄዎች ብዛት 935 ሆኖ የትምህርት ክፍሎቹ የመለማመጃ ጥያቄዎች አማካይ 155.83 በመሆኑና ለንግግር ክሂል 159 መለማመጃዎች ተመርጠውና ተዘጋጅተው ስለቀረቡ የልዩነት መጠኑ ከአማካዩ የ3 ጥያቄዎች ብልጫ ያለው ስለሆነ

በመቶኛ ሲሰላም የአማካዩ 16.67% የንግግር ክሂል ደግሞ 17% በመሆኑና ልዩነቱ 0.34% በብልጫ በመሆኑ ተቀራራቢነት ያለው ሆኖ ስለተገኘ ነው::

3. በደረጃ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የንግግር ክሂል መለማመጃዎች ሳቢነትና ማራኪነት፣ ንዑሳን የንግግር ክሂሎችን የሚያዳብሩ፣ የተማሪዎችን፣ የመምህራንና የትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን ሁኔታ ያገናዘቡ ሆነው የቀረቡ ናቸው::
4. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት የንግግር ክሂልን ለማዳበር የተመረጡትና ተደራጅተው የቀረቡት መለማመጃዎች በመጽሐፉ ዝርዝር መገምገሚያ እንደተመለከተው ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት አላቸው::

ይህንን ጥናት ለማካሄድ በተመረጡት የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መገምገሚያ መሥፈርቶች አዎንታዊ የሆነ የግምገማ ውጤት የተገኘበት ይህ መማሪያ መጽሐፍ ነው::

ለ3ኛ ክፍል የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ቀደም ሲል በተናጠል በተደረገው ግምገማ መሠረት የታዩ ገጽታዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል

1. መማሪያ መጽሐፉ በመርሐ ትምህርቱ ላይ ተመርሥቶ የተዘጋጀ አይደለም::
2. በተደረገው ፍተሻ መሠረት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተመርጠውና ተዘጋጅተው የቀረቡት የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚያስችሉ መለማመጃዎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ አናሳ ሆነው ተገኝተዋል::
3. ተመርጠውና ተዘጋጀተው የቀረቡት የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚያስችሉ መለማመጃዎች ሳቢነትና ማራኪነት ባለው መልኩ፣ የተማሪዎችን ንዑሳን የንግግር ችሎታዎች በተሟላ መልኩ ከፍ ለማድረግ የሚረዱ ሆነው አልተገኙም:: ይሁን እንጅ የቀረቡት መለማመጃዎች የተማሪዎችን፣ የመምህራንና የትምህርት ቤቶችን ሁኔታ ያገናዘቡ ሆነው ተገኝተዋል::
4. የትምህርቱ ይዘት መለማመጃዎች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ይጎድላቸዋል:: ከዚህ ክፍል ደረጃ ቀድመው ባሉ የክፍል ደረጃዎችም ሆነ በመጽሐፉ ውስጥ ባሉ የንግግር ትምህርት ይዘቶች ተለጣጣቂነትና ተከታታይነታቸው ደካማ ነው::

ከላይ የተገለጹትንና ከመምህራን ከአመቻቾችና ከመማሪያ መጽሐፉ አዘጋጆት የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ የደረጃ 2 መማሪያ መጽሐፍ ከ3ኛ ክፍል መጽሐፍ የተሻለ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ አደረጃጀትና አቀራረብ ይታይበታል::

4.10.3. ደረጃ 3 ከ4ኛ ክፍል ጋር ሲነጻጸር

ለደረጃ 3 የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ቀደም ብሎ በዚህ ጥናት ውስጥ እንደተገለጸው የሚከተሉት ገጽታዎች ታይተውበታል፤

1. መርሐ ትምህርቱን መሠረት ያደረጉ የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚያስችሉ ይዘቶች ሙሉ በሙሉ ተመርጠውና ተዘጋጅተው አልቀረቡም፤
2. ከሌሎች የቋንቋው ትምህርት ክፍሎች አንጻር ሲታይ የንግግር ክሂልን ለማዳበር በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት መለማመጃዎች አነሰተኛ ቁጥር ያላቸው ናችው። ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ለሁሉም የቋንቋው ትምህርት ክፍሎች የተዘጋጁት መለማመጃዎች /ጥያቄዎች/ ቁጥር 515 ነው። ለእያንዳንዱ የትምህርት ክፍል አማካይ ድርሻው 85.83 ጥያቄዎች ያህል ነው። ለንግግር ክሂል ማለማመጃ የተዘጋጁት 60 ጥያቄዎች ናቸው። በ15.83 ጥያቄዎች ዝቅ ያለ ነው። ስለዚህ የንግግር ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ መለማመጃዎች በበቂ መጠን አልቀረቡም።
3. የመለማመጃዎቹ ሳቢነትና ማራኪነት፣ የተማሪዎችን፣ የመምህራንንና የትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን ሁኔታ ያገናዘቡ መሆናቸውን በተመለከተ መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት መለማመጃዎች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት የሚያነሳሱ፣ የተማሪዎችን፣ የመምህራንና የትምህርት ተቋማቱን ሁኔታ ያገናዘቡ መሆናቸው ተረጋግጧል። ንዑሳን የንግግር ክሂሎችንም ለማዳበር የተደረገው ዝግጅት የተማሪዎችን የመናገር ፍላጎት የሚያነሳሳ በመሆኑ በጠንካራ ጎን ታይቷል።
4. የንግግር ክሂልን ለማዳበር የተመረጡት መለማመጃዎች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነትን በተመለከተም በቀደሙት ደረጃዎች የነበሩና በዚህ ደረጃ ሠፋና ጠለቅ ብለው መቅረብ የነበረባቸው መለማመጃዎች አልቀረቡም። ስለዚህ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያንሳቸዋል።

ለ4ኛ ክፍል የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የሚከተሉት ገጽታዎች ታይተውበታል

1. ምንም እንኳ በርካታ መለማመጃዎች ማለትም 57% የሚሆኑት መርሐ ትምህርቱን መሠረት አድርገው የተዘጋጁ ቢሆኑም 43% መርሐ ትምህርቱን መሰረት ሳያደርጉ ተዘጋጅተው የቀረቡ በመሆናቸው መማሪያ መጽሐፉ መርሐ ትምህርቱን ሙሉ በሙሉ መሠረት ያደረገ አይደለም።

2. ሁሉንም የትምህርት ክፍሎች ተማሪዎች እንዲለማመዱባቸው የተመረጡና ተዘጋጅተው የቀረቡ 422 ጥያቄዎች በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ይገኛሉ:: ከእነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ በአማካይ የአንዱ ትምህርት ክፍል ድርሻ 70.33 ጥያቄዎች ናቸው:: ከመቶኛ ሲሰላም 16.67% ይሆናል:: የንግግር ክሂል ትምህርት ጥያቄዎችን ስናይ ብዛታቸው 28 ከመቶ ያላቸው ድርሻ 6.64% ነው:: ስለዚህ የንግግር ክሂል ትምህርትን ለማዳበር የሚያስችሉ መለማመጃዎች በበቂ ሁኔታ አልተዘጋጁም::
3. የቀረቡት መለማመጃዎች የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ትምህርት ለመማር ፍላጎታቸውን የሚያነሳሱ፣ ሳቢነትና ማራኪነት ያላቸው ሆነው አልቀረቡም:: ይሁን እንጅ የተማሪዎችን፣ የመምህራንና የትምህርት ቤቶችን ሁኔታ ያገናቡ ናቸው:: ንዑሳን የንግግር ክሂሎችን ሙሉ በሙሉ የሚያዳብሩ ናቸው ብሎ መደምደም አይቻልም::
4. የንግግር ክሂልን ለማዳበር የተመረጡት መለማመጃዎች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያንሳቸዋል:: ባለፉት የክፍል ደረጃዎች የተጠቀሱትንና የንግግር ክሂልን ከፍ ለማድረግ የሚረዱትን እንደተረት፣ እንቆቅልሽ፣ እንካሰላንቲያ የመሳሰሉትን አላካተቱም::

በዚህ መሠረት ከዚህ በላይ ለማነጻጸሪያነት የተጠቀምንባቸውን ነጥቦችና ከመምህራን፣ ከአመቻቾችና መጽሐፉን ካዘጋጁት የትምህርት ባለሙያዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ምንም እንኳ በሁለቱም መጻሕፍት የንግግር ክሂል ትኩረት ያልተሰጠው ቢሆንም የደረጃ ሶስት ከ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አንጻራዊ በሆነ መልኩ የተሻለ አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ አለው::

ክፍል አምስት

ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳብ

5.1. ማጠቃለያ

ለመደበኛውና ለአማራጩ ትምህርት መርሐ ግብሮች በአማራ ክልል ለማስተማሪያነት የዋሉት የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትን የንግግር ክሂል ትምህርት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረባቸው ምን እንደሚመስል በንጽጽር ተገምግመዋል። በንጽጽራዊ ግምገማው መሠረትም ጠቅለል ብሎ ሲቀርብ የሚከተሉትን ሐሳቦች ይዞ ይገኛል።

በመደበኛው ከ1-4ኛ ክፍል፣ በአማራጩ ከደረጃ 1-3 ከተገመገሙት መጻሕፍት ውስጥ ለ2ኛ ክፍልና ለደረጃ 2 የተዘጋጁት መማሪያ መጻሕፍት ከሌሎቹ የተሻለ የንግግር ክሂል ምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረበ ታይቶባቸዋል። ይህ ሲባል ግን እነዚህ ሁለት መጻሕፍትም ቢሆኑ የተሟላ አዘገጃጀት አላቸው ማለት አይደለም። ከሌሎቹ ጋር ሲነጻጸሩ የተሻሉ ናቸው ለማለት እንጅ።

የዚህ ጥናት ዓላማ ከሁለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች የተሻለ አዘገጃጀት ያለውን መለየት በመሆኑ ምንም እንኳ ከመደበኛው መርሐ ግብር የ2ኛ ክፍል የተሻለ ሆኖ ቢገኝም በአጠቃላይ ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የተዘጋጁት መማሪያ መጻሕፍት ከመደበኛዎቹ መማሪያ መጻሕፈት እንደሚሻሉ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል። የንግግር ክሂልን ለመማር የይዘት አመራረጥ አደረጃጀትና አቀራረባቸው አንጻራዊ በሆነ መልኩ ተሸሎ ተገኝቷል።

ቀደም ሲል የ2ኛ ክፍልንና የደረጃ 2ን መማሪያ መጻሕፍት በተመለከተ እንደተገለጸው የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መማሪያ መጻሕፍትም ቢሆኑ የንግግር ክሂልን ለመማር የተሟላ የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ አላቸው ማለት አይደለም። ንጽጽሩ ሲካሄድ አንጻራዊ በሆነ መልኩ የተሻለ አዘገጃጀት ይታይቶባቸዋል ለማለት ነው።

በሁሉም መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች አኳያ ሲታይ የተሰጣቸው ትኩረት አነስተኛ ነው። በተለይም ከንባብ፣ ከጽሕፈትና በአንዳንድ መጻሕፍት ውስጥ ከሰዋስው አንጻር ሲታዩ በጣም አናሳ ትኩረት ተሰጥቷቸው ይታያል።

በአንዳንድ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት በቂ ትኩረት እንደተሰጠው ሆኖ የቀረበበት ሁኔታ በትንተናው ላይ ተጠቅሷል። በዚህ አገላለጽ ለማስተላለፍ የተፈለገው ለሁሉም ክሂሎች የተዘጋጁት መለማመጃዎች እኩል ለክሂሎች እንዲከፋፈሉ ተደርጎ

ቢሆን ኖሮ በአማካይ ከሚደርሰው መለማመጃ መጠን ያነሱ መለማመጃዎችን ስላልያዙ እንጂ ከእነሱ የበለጠ ትኩረት የተሰጠው የክሂል ዘርፍ የለም ለማለት አይደለም።

በአጠቃላይ መማሪያ መጻሕፍቱ ሲዘጋጁ መርሐ ትምህርቱን መሠረት አድርጎ ያለመቅረብ፣ የተማሪዎችን የንግግር መማር ፍላጎት ሊያነሳሱና ንዑሳን የንግግር ክሂሎቻቸውን የሚያዳብሩ መለማመጃዎችን ተከታታይ አድርጎ በበቂ መጠን ያለማቅረብ ይታያል። አሳታፊና ሳቢ የሆነ ይዘቶችን ያለመምረጥ ችግር እንዳለም ለመረዳት ተችሏል።

በአነስተኛ ቁጥርና በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የቀረቡት ይዘቶች የተማሪዎችን እድሜና ደረጃ ያገናዘቡ፣ እምነትና ባህላቸውን የማይነኩ እንደሆኑ በግምገማው ለማረጋገጥ ተችሏል። ከመምህራን፣ ከአመቻቾችና ከትምህርት ተቋማት አካያም ትምህርቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችግሩ አይደሉም። መምህራንና አመቻቾች ከ10ኛ ወይም ከ12ኛ ክፍል በኋላ አንድ አመት የማስተማር ሥልጠና ያላቸው በመሆናቸው ለማስተማር ችግር እንደማያጋጥማቸው ይገመታል። የትምህርት ተቋማቱም ለንግግር ትምህርት የቀረቡት ይዘቶች የተለየ ወጪን፣ ተጨመሪ የሰው ኃይልን /ድጋፍን/ የማይጠይቁ በመሆናቸው ተግባራዊ ሲደረጉ የሚቸገሩበት ሁኔታ የሚያጋጥም አይመስልም።

5.2. የመፍትሔ ሐሳብ

በንጽጽር ከታዩት ሰባት መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ አንጻራዊ በሆነ አተያይ የደረጃ ሁለትና የሁለተኛ ክፍል የተሻለ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረበ ታይቶባቸዋል። ይሁን እንጂ እነዚህም ቢሆኑ በበቂ መጠን የንግግር ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ መለማመጃዎችን እንዳልያዙ በጥናቱ ተገልጿል። በትምህርት ክፍሎች /ክሂሎች/ አዘገጃጀት ሚዛናዊነት የማይታይባቸውን የመማሪያ መጻሕፍት ሚዛናዊ እንደሆኑ የሚረዱ የመፍትሄ ሐሳቦችን ለመጥቀስ ተሞክሯል፤

1. በመርሐ ትምህርቱ ላይ የቀረቡት አብዛኛዎቹ የቋንቋ ትምህርት ክፍሎች ይዘቶች ሚዛናዊነት ታይቷል። ይህን ሚዛናዊነት የጠበቀ አዘገጃጀት በመማሪያ መጻሕፍቱም ላይ መመሥረት ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግ የመጻሕፍቱ አዘጋጆች መርሐ ትምህርቱን መሰረት አድርገው የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች ቢመርጡ፣ ቢያደራጁና ቢያቀርቡ መማሪያ መጻሕፍቱ የተሻሉ ይሆናሉ።
2. ምንም እንኳ ሕጻናት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን መማራቸውን የሚቃወም የመጽሐፍ አዘጋጅ ባያጋጥምም በመጀመሪያዎቹ የክፍል ደረጃዎች ላይ ትኩረት መደረግ ያለበት ለንባብና ጽሕፈት ብቻ ነው የሚሉ አልታጡም። ይህ ደግሞ ከቋንቋ ትምህርቱ

አጠቃላይ ዓላማ የወጣ ነው:: የክፍል ደረጃዎቹ የቋንቋ መርሐ ትምህርት ዓላማዎች እንደሚገለጹት ተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎችን መማር ያለባቸው በእኩል ደረጃ ነው:: ነገር ግን ለአንዱ ክሂል ትኩረት ሰጥቶ ሌላውን ችላ ማለት በተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል:: ስለዚህ ለንግግር ክሂልም ተገቢ ትኩረተ ለመስጠት ጥረተ ቢደረግ::

3. መጻሕፍቱን የሚያዘጋጁት ባለሙያዎች በተወሰኑ ጊዜያት የልምድ ልውውጦችን ቢያደርጉ ያላቸውን ችሎታና ብቃት እያጎለበቱ ለመሄድ ያስችላቸዋል:: ችሎታና ብቃታቸው እየጎለበተ ሲሄድ ደግሞ የተሻለ መማሪያ መጻሕፍትን የማዘጋጀት ብቃት ይኖራቸዋል:: ስለዚህ የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች የልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ቢያመቻች የተሻለ ነው::

4. በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው እርከን ተማሪዎች እድሜያቸው ከ7-10 ዓመት የሚሆኑ ናቸው:: እነዚህ ሕጻናት የሚሰጣቸውን ትምህርት ሳቢና ማራኪ በሆነ መንገድ እንደሚሩ ለማድረግ አካባቢያዊ የሆኑ ይዘቶችን በመማሪያ መጻሕፍታቸው ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል:: በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ይህ ሁኔታ እንዲፈጠር በመማሪያ መጻሕፍት ሳቢነትና አዝናኝነት ያላቸው ይዘቶች ሊካተቱ ይገባል:: እንቆቅልሾች፣ ተረቶች፣ እንካሰላንቲያዎች፣ ሚና ጨዋታዎች፣ ቃለ ምልልሶች፣ ጥያቄና መልሶች፣ የቡድን ውይይቶች፣ ወዘተ. ሕጻናትን ሊያስደስቱ ከሚችሉ ይዘቶች ጥቂቶቹ ናቸው:: ስለዚህ እነዚህን ይዘቶች ማከተት ጥሩ የሆነ አዘገጃጀት ይሆናል::

5. በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚጠቀሱ ይዘቶች በአንድ የክፍል ደረጃ ላይ ብቻ ቀርበው በሌላዎቹ ሠፋና ጠለቅ ባለ ሁኔታ መቅረብ ካልቻሉ የሚያመጡት ለውጥ ዘላቂ አይሆንም:: በጥናቱ ውስጥ በተጠቀሱተ መጻሕፍት ውስጥም አንዳንድ የንግግር ክሂል መለመጃመጃ ይዘቶች በተወሰኑ ክፍሎች ብቻ ተጠቅሰው በሌላዎቹ ሲዘለሉ ተስተውለዋል:: ለምሳሌ የሚና ጨዋታ፣ ቃለ ምልልስ ሲደጋገሙ አይታዩም:: እነዚህ አቀራረቦች የንግግር ክሂልን ለማዳበር ያላቸው ሚና ከፍተኛ ስለሆነ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ባለው ሁኔታ እንዲቀርቡ ቢደረግ መልካም ነው::

6. መማሪያ መጻሕፍት አንዴ ከተዘጋጁ በኋላ ዝግጅቱ አበቃለት ማለት አይቻልም:: ተከታታይ የሆነ ግምገማ እየተደረገባቸው በየጊዜው እንዲስተካከሉ ማድረግ ያስፈልጋል:: በዚህም መሠረት የቀረቡት መጻሕፍት በተለያዩ የትምህርት ባለሙያዎች (በመምህራን፣

በአዘጋጆች፣ በሱፐር ቫይዘሮች እና በተማሪዎች) እንዲገመገሙ ቢደረግ በመጀመሪያው ዝግጅት የታዩ ስህተቶች እየታረሙ ይሄዳሉ:: በዚህ ጥናት ውስጥ ከተገመገሙት መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቅርብ ጊዜ ህትመት የሆነው 1997 ዓ.ም ነው:: መጽሐፉ ምንም መሻሻል ሳይደረግበት 3 እና 4 አመታት አገልግሏል:: በዝግጅቱ ወቅት የነበሩ ስህተቶች እንዳሉ ናቸው:: እነዚህን ስህተቶች ለማስወገድ ዝግጅቱን የሚያስተባብረው ክፍል በየጊዜው መጻሕፍቱን ቢያስገመግማቸው ስህተቶችን ለማረም ይጠቅመዋል ብሎ አጥኚው ያምናል::

ዋቢ መጻህፍት

መንግሥቱ ታደሰ (1997)። «በአዲስ አበባ መስተዳድር የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የማስተማር ዘዴ አተገባበር ግምገማ።» በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ ጥናት። በአማርኛ ማስተማር ዘዴ በማስተርስ ዲሪግ ማሚያ። (ያልታተመ)።

በሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩ የቋንቋዎች ትምህርት ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ቡድን (1996)። የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶች ከ1ኛና-4ኛ ክፍል። አዲስ አበባ፤ በት.መ.ማ.ማ.ድ።

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ት/ቢሮ /1993/። የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ደረጃ አንድ (ቦታው ያልተጠቀሰ)፤ አልፋ አታሚዎች።

---------- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ት/ቢሮ /1993/። የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ደረጃ ሁለት (ቦታው ያልተጠቀሰ)፤ አታሚዎች።

---------- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ት/ቢሮ /1993/። የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ደረጃ ሶስት (ቦታው ያልተጠቀሰ)፤ አታሚዎች።

በድሉ ዋቅጅራ (1996)። በሥነ-ጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተማያ ድርጅት።

ተስፋዬ ሽዋዬ/1981/። «ሥነ-ልሳንና ቋንቋን ማስተማር።» አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ /ያልታተመ/።

ተክለማርያም ፋንታዬ (1965)።ጥናተ ጥበብ ዘሥነ-ጽሑፍ (7ኛ እትም)። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ.ማተሚያ ቤት።

ትምህርት ሚኒስቴር /1994/። የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና አተገባበሩ። አዲስ አበባ፤ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርኘራይዝ።

ወንድወሰን አዳነ /1995/ «አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በስተማር የሥነ-ጽሑፋዊ ይዘቶች ፋይዳ አመራረጥና አደረጃጀት። አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር የተቀረጹትን የ7ኛና የ8ኛ ክፍሎች መርሃ ትምህርት ለማሻሻል በተዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ የቀረበ።» ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም ኢንስቲትዩት አዲስ አበባ፣ ጥቅምት 1995። (ያልታተመ።)

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ (1995)።አማራጭ የህፃናት መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ስትራቴጅ። ባህርዳር/ ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ/።

_____(1997):: የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የአፈፃፀም መመሪያ:: ባህርዳር፤ የተባበሩት አታሚዎች::

---------- (1998):: የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የአማርኛ ትምህርት ደረጃ አንድ የመማሪ መጽሐፍ:: አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት::

_____(1998):: የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የአማርኛ ትምህርት ደረጃ ሁለት የመማሪ መጽሐፍ:: አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት::

_____(1998):: የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የአማርኛ ትምህርት ደረጃ ሦስት የመማሪያ መጽሐፍ:: አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት::

_____(1998):: የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የአማርና ትምህርት ደረጃ አንድ የማስተማሪያ መጽሐፍ:: አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት::

_____(1998):: የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የአማርና ትምህር ደረጃ ሁለት የማስተማሪያ መጽሐፍ:: አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ በት::

_____(1998):: የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የአማርኛ ትምህርት ደረጃ ሦስት የማስተማሪያ መጽሐፍ:: አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት::

----------(1996):: አማርኛ መማሪያ አንደኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ቤት::

_____(1996):: አማርኛ መማሪያ ሁለተኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ቤት::

_____(1996):: አማርኛ መማሪያ ሦስተኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፤ቦሌ ማተሚያ ቤት::

_____(1996):: አማርኛ መማሪያ አራተኛ ክፍል:: አዲስ አበባ ቦሌ ማተሚያ ቤት::

_____(1996)::አማርኛ የመምህሩ መምሪያ 1ኛ ክፍል::አዲስ አበባ፤ቦሌ ማተሚ ቤት::

_____(1996)::አማርኛ የመምህሩ መምሪያ 2ኛ ክፍል::አዲስ አበባ፤ቦሌ ማተሚያ ቤት::

_____(1996)::አማርኛ የመምህሩ መምሪያ 3ኛ ክፍል::አዲስ አበባ፤ቦሌ ማተሚያ ቤት::

_____(1996):: አማርኛ የመምህሩ መምሪያ 4ኛ ክፍል::አዲስ አበባ፤ቦሌ ማተሚያ ቤት::

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት (1986):: አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፓሊሲ:: አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት::

Amhara Regional Education Bureau (2003). **The Amhara National Regional State Children's Alternative Basic Education Program Strategy.** Bahirdar: (Printing Press is not Mentioned).

Annsnow, Marguerite (1991). "Teaching Langauge through contnt" In Marinne Celce-Murcia (editors)**. Teaching English as a Secon or Foreign Langauge**. Boston: Heinle and Heinle. New burty house. (PP 315-325.)

Billows, F.L. (1964). **Techniques of Langauge Teaching**. London: Longmans.Botsman, P.Bl. (1971) "Collective Speaking with Older Learners." In W.R. Lee. **English Language Teaching**. Journal of English Langauge Teaching. vol. XXV., No. 1. (pp. 31-39.)

Botsman P.B. (1971) Collective Speaking with older learners "in W.R Lee". **English Language Teaching Journal of English Language.** Vol.XX VI. No. 1.. (pp.331-339).

Buny, Grace, W. (1995). "Course Design". In Matiru, I.B.A.P. Muaugi and Schlette (eds). **Teach Your Best: A Handook for University Lectures**. (pp. 123-156). German Foundation for International Development: Institue for Socio-cutural Studies (ISOSS), University of Kassel, Germany.

Burton, Graeme and Richard Dimbleby (1990). **Teaching Communication**. London: Routledge.

Brown, Gillian and Gorege Yule (1983). **Teaching the Spoken Language.** Cambridge: Cambridge University Press.

Bygate Martin (1995). **Speaking**. Oxford: Oxford University Press.

Celce-Murcia, Marianne (1991). "Teaching Methodology" Marianne Celce- Murcia (editors) **Teaching English as a Second or Foreign Language.** Botson: Heinle and Heinle. New Burty House (pp 3-11).

Cunningsworth Alan (1989). **Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials**. Oxford: Heinemann.

Cunningsworth Alan (1995). **Choosing Your Textbook**. Oxford: Heinemann.

Echeverria Ellen W. (1987). **Speaking on Issues: An Introduction to Public Communication**. New York: Harcourt Brace and Campany.

Florez, C. and A. Marry (1999). **Improving Adult English Langauge, Learners Speaking Skill**. New York: National Centr for ESL Litracy Education.

Grant, Neville (1987). **Making the Most of Your Textbook**. London: Longman.

Harmer, J. (2001). **The Practice of English Langauge Teaching**. (3rd ed). Malysia: Longman.

Knott, Mike and Peter Mutunga (1995). "Methods of Teaching and Learning." In Matiru I.B.A.P. Muaugi and Schlette (eds). **Teach Your Best: A Handook for University Lectures**. German Foundation for International Development: Institue for Socio-cutural Studies (ISOSS), University of Kassel, Germany. (pp 157-221).

Mackery, W. F. (1962). **Language Teaching Analysis**. London: Longman.

McDonough, J. and Christopher, Shaw (1994). **Material and Methods in ELT: A Teacher Guide**. Oxford: Blackwell.

Nolasco, Robandlois Arther (1989). **Conversation: Resource Book for Teachers**. Cambridge: Cambridge University Press.

Nunan, D (1988). **Syllabus Design**. Oxford: Oxford University Press.

Pronovost, Wilbert (1950) " A coordinated Program for Teaching Effective Speaking." In Stable URL, **The Elementary School Journal**. Vol. 51, No, 1 Sep., 1950 (pp 31-34)

Richards, Jack. C. (1994). **The Context of Langauge Teaching**. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J.C. and Theodore, S. Rodgers (2001). Approaches and Methods in Langauge Teaching (2nd ed.). Cambridge: Camgridge University Press.

Riggenbach, Heidi and Anne Lazaraton (1991). "Promoting Oral Communication Skills. In Celce-Murcia, Marianne (editor). **Teaching English as a Second or Foreign Langauge**. Boston: Heinle and Heinle. (pp. 126.)

Skierso, Alexandra (1991). "Textbook Selection and Evaluation." In Marinne Celce-Murcia (editor). **Teaching English as a Second or Foreign Langauge**. Boston: Heinle and Heinle.

Smith, B.O. and others (1950). **Fundamentals of Curriculum Development**. New York: Hascourt, Brace, Jouanuich, Inc.

Taba, H. (1962). **Curriculum Development: Theory and Practice**. New York: Harcout, Brace, Jouanuich, inc.

Ur, Penny (1996). **A Course in Langauge Teahing: Practice and Theory**. Cambridge: Cambridge University Press.

Widdowson H.G. (1992). **Teaching Langauge as Communication**. Oxford: Oxford University Press.

Wube Kassaye (2003). "Basic Education: Conceptualization, Planning and Implementation with Emphasis on the Ethiopian Practice." In MOE Public Relation Service (eds). **Educaional Journal.** Vol. 7. No. 15. Addis Ababa: Educational Material Printing and Distributing Press.

Yalden, J. (1987). **Principles of Course Design for Langauge Teaching**. Cambridge: Cambridge University Press.

አባሪዎች

አባሪ አንድ

"ሀ"

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ ሥር በሚገኙ በተመረጡ የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው እርከን በመደበኛው ወይም በአማራጭ መሠታዊ ትምህርት መርሃ ግብር አማርኛ ቋንቋን በሚያስተምሩ መምህራን (አመቻቾች/Facilitators) የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ::

<u>ውድ መምህር/ት</u>

የዚህ መጠይቅ ዓላማ በአንደኛ ደረጀ የመጀመሪያው እርከን የተዘጋጁ የመደበኛውና የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መርሃ ግብር የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት አዘገጃጀታቸውን በንጽጽር በመፈተሽ የተሻለ ወይም ደካማ አዘገጃጀት የተከተለውን በመለየት የተሻለ አዘገጃጀት ያለውን በሁሉም መርሃ ግብሮች ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ ከመምህራንና ከአመቻቹች ለጥናቱ ደጋፊ መረጃዎችን ለማግኘት ነው:: በዚህ መሠረት ጥያቄዎችን በጥሞና በማንበብ ተገቢውን መልስ እንዲሰጡ በአክብሮት እጠይቃለሁ:: ለሚደረግልኝም መልካም ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ::

1. የሚያስተምሩበት የትምህርት ተቋም ስም _____
2. የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ _____
3. ዕታ _____ 4. ዕድሜ _____
5. የአገልግሎት ዘመን _____ 6. የትምህርት ደረጃ _____
7. የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት ዓቢይ _____ ንዑስ _____
8. በዚህ ክፍል ደረጃ አማርኛ ቋንቋን ያስተማሩበት ዓመት (ብዛት) _____
9. አሁን በሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ ለመማሪያ የተዘጋጀው መጽሐፍ ላይ ግምገማ አድርገው ያውቃሉ? _____
   _____

   9.1. መልስዎ አዎ የሚል ከሆነ የንግግር ክሂልን በተመለከተ ያደረጉት ግምገማ ምን ይመስል ነበር? መጽሐፉን እንዴት አገኙት? አስተያየተዎን በአጭሩ ቢገልጹልኝ::

_____
_____
_____
_____

9.2. ግምገማ ካደረጉት በኋላ መጽሐፉ እንዲሻሻል ጥረት አድርገዋል? ተደርጐ ከሆነ መሻሻሉ የንግግር ክሂልን ለማስተማር ምን ያህል የተሻለ ሆኖ አገኙት?

_____
_____
_____
_____
_____

10. ቀጥለው ለቀረቡት የጽሑፍመጠይቆች አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋቸዋል። ትክክለኛ መልስ ይሆናል የሚሉትን የሚያመለክተውን ሆሄ በመክበብ ይመልሱ። የተለየ ሀሣብ ካለዎት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይጻፉ።

10.1. በሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ የንግግር ክሂል ትምህርት የቀረበው በየትኛው ሁኔታ ነው?

ሀ. ለብቻው ተለይቶ ሐ. የንግግር ክፍል ትምህርት አልቀረበም

ለ. ሌሎችን ክሂሎች ሲማሩ እግረ መንገዱን መ. መኖር አለመኖሩ አይለይም

ሠ. _____

10.2. የንግግር ክሂልን ለማስተማር የተመረጡት ይዘቶች ተከታታይነት፣ (አንዱ በሌላው ላይ እየተመሠረተ መሄድ)፣ ተለጣጣቂነት (ከአንዱ ደረጃ ወደሌላው ከፍ እያለና እያደረገ መሄድ) እንዴት ይታያል?

ሀ. በከፍተኛ ደረጃ ተከታታይና ተለጣጣቂ ናቸው።

ለ. በመጠኑ ተከታታይና ተለጣጣቂ ናቸው።

ሐ. በዝቅተኛ ደረጃ ተከታታይና ተለጣጣቂ ናቸው።

መ. ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት የላቸውም።

ሠ. _____

10.3. የንግግር ክሂል ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች አንፃር ሲታይ የተሰጠው ክፍለ-ጊዜ መጠን ምን ይመስላል?

ሀ. ከሁለም በበለጠ ሁኔታ ቀርቧል ሐ. ከሁሉም በዝቅተኛ ደረጃ ቀርቧል

ለ. በዕኩል ደረጃ ቀርቧል መ. ምንም አልቀረበም

ሠ. _____

10.4. የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ የሚያዳብሩ መለማመጃዎች በመጽሐፉ በምን ያህል ደረጃ ተዘጋጅተዋል?

ሀ. በብዛት ተዘጋጅተዋል ሐ. በዝቅተኛ መጠን ተዘጋጅተዋል

ለ. መጠነኛ ቁጥር ያላቸው ተዘጋጅተዋል መ. ምንም አልተዘጋጁም

ሠ. ----------

11. ከዚህ ቀጥሎ በሠንጠረዥ ውስጥ የሰፈሩ አስተያየቶች ቀርበዋል። በእነዚህ አስተያየቶች እርስዎ በምን ደረጃ እንደሚስማሙ በደረጃ መለኪያዎቹ ስር ይህንን ምልክት "X" ያስቀምጡ። የተለየ አስተያየት ያለዎት ከሆነም በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ ይግለጹ።

11.1. የሚከተሉትን የንግግር ንዑሳን ክሂሎች ለማዳበር መማሪያ መጽሐፉ ምን ያህል ረድቷል ይላሉ?

ተ.ቁ	ንዑሳን ክሂሎች	ለመማር ያበረከተው አስተዋፅኦ				
		በከፍተኛ ደረጃ	በመጠነኛ ደረጃ	በዝቅተኛ ደረጃ	ምንም	ሌላ አስተያየት አለዎት?
ሀ	ከሰው ፊት ቆሞ መናገር መቻል					
ለ	ፍርሃትን ማስወገድ					
ሐ	አይናፋርነትን ማስወገድ					
መ	ርዕሰ ጉዳይን ተከትሎ መናገር					
ሠ	ሀሳብን ሣይደጋግሙ፣ ሣያንዛዙና ማራኪ በሆነ ሁኔታ መግለፅ					
ረ	የአድማጭን ሁኔታ በመገንዘብ ማነቃቂያ ማቅረብ					
ሰ	አካላዊ አቀራረብን ማሣመርና ከንግግሩ ጋር ማስማማት (አለባበስ፣ የአካል ክፍሎች እንቅስቃሴ፣ ወዘተ.)					
ሸ	ድምፃቸው ለአድማጭ ሊሰማ በሚችል መልኩ መናገር እንዴችሉ ማበረታታት					

11.2. በአዘገጃጀቱ ጊዜ የሚከተሉት ጉዳዮች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በውል ትኩረት የተሰጣቸው ይመስለዎታል?

ተ.ቁ	ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች	ትኩረት የተሰጠባቸው ደረጃዎች				
		በከፍተኛ ደረጃ	በመጠነኛ ደረጃ	በዝቅተኛ ደረጃ	ምንም	ሌላ አስተያየት አለዎት?
ሀ	የተማሪዎችን ዳራ ማገናዘብ የቻለ					
ለ	የመምህራኑን ዳራ ማገናዘብ የቻለ					
ሐ	በመርሀ ትምህርቱ ዓላማዎች ላይ የተመሠረተ					
መ	ተቋማዊ ሁኔታዎችን ያገናንዘበ					

11.3. ተማሪዎች አሳታፊ በሚያደርጓቸው የመማር ተግባራት እንዲገቡ ለማድረግ የመማሪያ መጽሐፉ አመቺ ነው?

ተ.ቁ	አሣታፊ ተግባራት	የአሣታፊነቱ ደረጃዎች				
		በከፍተኛ ደረጃ	በመጠነኛ ደረጃ	በዝቅተኛ ደረጃ	ምንም	ሌላ አስተያየት አለዎት?
ሀ	በውይይት (በቡድን) መልክ ማሣተፍ					
ለ	ሀሳቦችን በመደገፍና በመቃወም መከራከር					
ሐ	ቃለ-ምልልስ ማድረግ					
መ	ጥያቄና መልስ ማካሄድ					
ሠ	በጭውውት መሣተፍ /ሚና ጨዋታ/					
ረ	ተረትን መተረት					
ሰ	በተናጠል መናገር					

አባሪ አንድ

"ለ"

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድህረ ምረቃ መርሀ-ግብር

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ ሥር በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው እርከን ትምህርት ተቅማት የሚያገለግለውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ባዘጋጁት ተሳታፊ ዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ።

<u>ውድ አዘጋጅ</u>

የዚህ ጽሑፍ መጠይቅ ዓላማ በአንደኛ ደረጃ ለመጀመሪያው እርከን በተዘጋጁት የመደበኛውና የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መርሀ ግብር መማሪያ መጻህፍት ላይ በንጽጽር ጥናት ሲደረግ ደጋፊ መረጃን ለማግኘት ነው። በዚህ መሠረት የቀረቡትን መጠይቆች በጥሞና በማንበብ ተገቢ ይሆናል የሚሉትን መልስ መስጠትዎ ለጥናቱ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነውና ትብብርዎ እንዳይለየኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ።

1. የሚሠሩበት መሥሪያ ቤት ስም ----------
2. ያለዎት የሥራ ድርሻ/መደብ----------
3. ዕታ ---------- 4. ዕድሜ ----------
5. የግልጋሎት ዘመን ---------- 6. የትምህርት ደረጃ ----------
7. የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት ዓቢይ ---------- ንዑስ ----------
8. ያዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የክፍል ደረጃ ----------
9. ከዚህ /ከእነዚህ/ መማሪያ መጽሐፍ /መጻህፍት/ ሌላ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት አዘጋጅተው ይውቃሉ? ----------
10. አዘጋጅተው ከሆነ የስንተኛ ክፍልን? ----------
    በተናጠል ነው ወይስ በጋራ? ----------
11. የመማሪያ መጽሐፉን ካዘጋጁ በኋላ ግምገማ አድርገውበት ያሉቃሉ? ----------
12. ግምገማ አድርገው ከሆነ የንግግር ክሂልን በተመለከተ ማሻሻያ እንዲደረግበት አድርገዋል? ----------
13. ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት የጽሑፍ መጠይቆች አማራጭ መልሶችን የያዙ ናቸው። ትክክለኛ መልስ ይሆናል የሚሉትን የያዘውን ሆሄ በመክበብ ይመልሱ። መልስዎ

ከአማራጮቹ ውጪ ከሆነ በመጨረሻ በተሰጠው ሆሄ አንጻር በሚገኘው ክፍት ቦታ ላይ ሀሳብዎን ይፃፉ።

13.1. የንግግር ክሂል ትምህርት በቋንቋው አፍፈት ለሆኑ ተማሪዎች ማስተማር ያስፈልጋል ይላሉ?
ሀ. አዎ ለ. አይደለም ሐ. ----------

13.2. ባዘጋጁት መጽሐፍ ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት የቀረበው በየትኛው ሁኔታ ነው?
ሀ. ለብቻው ተለይቶ ቀርቧል
ለ. ሌሎች ክሂሎች ሲቀርቡ እግረ መንገዱን የቀረበ ነው
ሐ.የንግግር ክሂል ትምህርት አልቀረበም
መ. ----------

13.3. ባዘጋጁት መጽሐፍ ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች የተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ደረጃ ምን ይመስላል?
ሀ. በከፍተኛ ደረጃ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ይታይበታል።
ለ. በመጠኑም ቢሆን ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ይታይበታል።
ሐ. በዝቅተኛ ደረጃ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት እንዲኖ ተደርጓል።
መ. ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት አይታይበትም።
ሠ. ----------

13.4. ከሌሎች ክሂሎች አንፃር ሲታይ የንግግር ክሂል ትምህርት ባዘጋጁት መጽሐፍ ውስጥ የሰጡት ትኩረት ምን ይመስላል?
ሀ. ከሁሉም በበለጠ ሁኔታ ቀርቧል። ሐ. ከሁሉም ባነሰ ደረጃ ቀርቧል።
ለ. በእኩል ደረጃ ቀርቧል። መ. ምንም አልቀረበም።
ሠ. ----------

13.5. የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ሊያዳብሩ የሚችሉ መለማመጃዎች ባዘጋጁት መጽሐፍ ውስጥ በምን ያህል ደረጃ ተዘጋጅተዋል?
ሀ. በብዛት ተዘጋጅተዋል ሐ. በዝቅተኛ ቁጥር ተዘጋጅተዋል
ለ. መጠነኛ ቁጥር ባላቸው መጠንተዘጋጅተዋል መ. ምንም አልተዘጋጁም
ሠ. ----------

14. በሠንጠረዥ ውስጥ አስተያየቶች ቀርበዋል። በአስተያየቶቹ በምን ደረጃ እንደሚስማሙ በደረጃ መለኪያዎቹ ሥር ይህንን "X" ምልክት ያስቀምጡ፤ የተለየ አስተያየት ካለዎት በተሰጠው ቦታ ላይ ይፃፉ።

14.1. የሚከተሉትን የንግግር ንኡሳን ክሂሎች ለማዳበር የሚያስችሉ ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካተዋል ይላሉ?

ተ.ቁ	የንግግር ንዑሳን ክሂሎች	የተካተቱበት መጠን				
		በከፍተኛ ደረጃ	በመጠነኛ ደረጃ	በዝቅተኛ ደረጃ	ምንም	ሌላ አስተያየት አለዎት?
ሀ	ከሰው ፊት ቆሞ መናገር መቻል					
ለ	የመናገር ፍርሃትን ማስወገድ					
ሐ	አይናፋርነትን ማስወገድ					
መ	ርዕሰ ጉዳይን ሳይለቁ መናገር					
ሠ	ሀሳብን ሳይደጋግሙና ሳያዛንፉ ማራኪ በሆነ ሁኔታ መግለፅ					
ረ	አቀራረብን ማሣመርና (አለባበስ) ከአነጋገር ጋር የሚሄድ የአካል እንቅስቃሴዎች ማድረግ					
ሰ	ድምፅን ከፍ አድርጐ መናገር					

14.2. መማሪያ መጽሐፉን በሚያዘጋጁበት ጊዜ የሚከተሉት ጉዳዮች በውል ትኩረት የተሰጣቸው ይመስለዎታል?

ተ.ቁ	ትኩረት የሚሰጥባቸው	የትኩረት ደረጃዎች				
		በከፍተኛ ደረጃ	በመጠነኛ ደረጃ	በዝቅተኛ ደረጃ	ምንም	ሌላ አስተያየት አለዎት?
ሀ	የተማሪዎችን ዳራ ያገናዘበ ነው።					
ለ	የመምህራንን ዳራ ያገናዘበ ነው።					
ሐ	በመርሀ-ትምህርቱ ዓላማዎች ላይ የተመሠረተ ነው።					
መ	ተቋማዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ነው ።					

14.3. ተማሪዎች አሣታፊ በሆኑ የንግግር ክንዋኔዎች እንዲሣተፉ በሚያስችል ሁኔታ መጽሐፉ ተዘጋጅቷል ይላሉ?

ተ.ቁ	አሣትፊ ተግባራት	የአሣትፊነት ደረጃዎች				
		በከፍተኛ ደረጃ	በመጠነኛ ደረጃ	በዝቅተኛ ደረጃ	ምንም	ሌላ አስተያየት አለዎት?
ሀ	በውይይት እንዲሣተፉ ማድረግ					
ለ	ሀሳቦችን በመደገፍና በመቃወም መከራከር ማስቻል					
ሐ	ቃለ ምልልስ ማድረግ ማለማመድ					
መ	ጥያቄና መልስን ማካሄድ					
ሠ	በጭውውት/በሚና ጨዋታ/ ማሣተፍ					
ረ	ተረት የሚተርቱበትን ሁኔታ ማመቻቸት					
ሰ	በቡድን ውይይት መሣተፍ					
ሸ	በተናጠል ንግግር ማቅረብ ማስቻል					

አባሪ ሁለት

«ሀ»

በደረጃ አንድ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ይዘቶች (ክፍሎች) መለማመጃ ጥያቄዎች መግለጫ

ተ.ቁ	ርዕስ	መልመጃዎቹ	የሚያተኩሩበት ክሂል	ገጽ	የጥያቄ ብዛት	ምርምር
1	ትምህርት አንድ የሆሄያትን ድምፅና ቅርጽ መለየት	የሆሄያት ድምፅ መለየት	ማዳመጥ	1-6	3	በ፣ሰ፣ሸ
		መልመጃ አንድ (ሆሄያት)	ንባብና ጽሕፈት	7	3	
		መልመጃ ሁለት (ቃላት)	ንባብና ጽሕፈት	7	3	
		መልመጃ ሦስት (ዐ.ነገር)	ንባብና ጽሕፈት	8	3	
2	ትምህርት ሁለት	የሆሄያት ድምፅ መለየት	ማዳመጥ	9-14	3	ለ፣አ፣ከ
		መልመጃ አንድ (ሆሄያት)	ንባብና ጽሕፈት	15	3	
		መልመጃ ሁለት (ቃላት)	ንባብና ጽሕፈት	15-16	8	
		መልመጃ ሦስት (ዐ.ነገር)	ንባብና ጽሕፈት	16	3	
3	ትምህርት ሦስት	የሆሄያት ድምፅ መለየት	ማዳመጥ	17-22	3	ጠ፣ሐ፣ጨ
		መልመጃ አንድ (ሆሄያት)	ንባብና ጽሕፈት	23	3	
		መልመጃ ሁለት (ቃላት)	ንባብና ጽሕፈት	23	5	
		መልመጃ ሦስት (ዐ.ነገር)	ንባብና ጽሕፈት	24	5	
4	ትምህርት አራት	የሆሄያት ድምፅ መለየት	ማዳመጥ	25-28	2	ተ፣ቸ
		መልመጃ አንድ (ሆሄያት)	ንባብና ጽሕፈት	29	2	
		መልመጃ ሁለት (ቃላት)	ንባብና ጽሕፈት	29	3	
		መልመጃ ሦስት (ዐ.ነገር)	ንባብና ጽሕፈት	30	5	
5	ትምህርት አምስት	የሆሄያት ድምፅ መለየት	ማዳመጥ	31-34	2	ረ፣ፈ
		መልመጃ አንድ (ሆሄያት)	ንባብና ጽሕፈት	35	2	
		መልመጃ ሁለት (ቃላት)	ንባብና ጽሕፈት	35	6	
		መልመጃ ሦስት (ዐ.ነገር)	ንባብና ጽሕፈት	36	6	
6	ትምህርት ስድስት	የሆሄያት ድምፅ መለየት	ማዳመጥ	37-40	2	ነ፣ኘ
		መልመጃ አንድ (ሆሄያት)	ንባብና ጽሕፈት	41	2	
		መልመጃ ሁለት (ቃላት)	ንባብና ጽሕፈት	41	5	
		መልመጃ ሦስት (ዐ.ነገር)	ንባብና ጽሕፈት	42	4	
7	ትምህርት ሰባት	የሆሄያት ድምፅ መለየት	ማዳመጥ	42-45	2	ዘ፣ዠ
		መልመጃ አንድ (ሆሄያት)	ንባብና ጽሕፈት	46	2	
		መልመጃ ሁለት (ቃላት)	ንባብና ጽሕፈት	46	5	
		መልመጃ ሦስት (ዐ.ነገር)	ንባብና ጽሕፈት	47	5	
8	ትምህርት ስምንት	የሆሄያት ድምፅ መለየት	ማዳመጥ	49-51	2	ገ፣ጐ
		መልመጃ አንድ (ሆሄያት)	ንባብና ጽሕፈት	52	2	
		መልመጃ ሁለት (ቃላት)	ንባብና ጽሕፈት	52	6	
		መልመጃ ሦስት (ዐ.ነገር)	ንባብና ጽሕፈት	53	3	
9	ትምህርት ዘጠኝ	የሆሄያት ድምፅ መለየት	ማዳመጥ	54-63	5	
		መልመጃ አንድ (ሆሄያት)	ንባብና ጽሕፈት		5	
		መልመጃ ሁለት (ቃላት)	ንባብና ጽሕፈት	64-65	6	
		መልመጃ ሦስት (ዐ.ነገር)	ንባብና ጽሕፈት	65	5	
10	ትምህርት አስር	የሆሄያት ድምፅ መየለት	ማዳመጥ	60-73	4	የ፣ደ፣ጀ፣ጰ
		መልመጃ አንድ (ሆሃያት)	ንባብና ጽሕፈት	74	4	
		መልመጃ ሁለት (ቃላት)	ንባብና ጽሕፈት	74	6	
		መልመጃ ሦስት (ዐ.ነገር)	ንባብና ጽሕፈት	75	5	
		መልመ				
11	ትምህርት አስራ አንድ	መልመጃ አንድ	ጽሕፈት	81	1	
		መልመጃ ሁለት ሀ-ሰ	ንባብ	81-82	7	
		መልመጃ ሦስት ሀ-መ	ንግግር	82-83	4	
		መልመጃ አራት ሀ-ሰ	ጽሕፈት	83-85	7	
		መልመጃ አምስት ሀ-መ	ጽሕፈት	85	4	
		መልመጃ ስድስት ሀ-ሸ	ጽሕፈት	86-87	8	
12	ትምህርት አስራ	መልመጃ አንድ 1-4	ጽሕፈት	88	4	

	ሁለት	መልመጃ ሁለት	ጽሕፈት	88	3	
		መልመጃ ሦስት	ጽሕፈት	89	6	
		መልመጃ አራት	ጽሕፈት	89-90	1	
13	ትምህርተ አስራ ሦስት	መልመጃ አንድ 1-4	ንባብ	91	2	
		መልመጃ ሁለት	ጽሕፈት	92	4	
		መልመጃ ሦስት ሀ	ንግግር	92	1	
		ለ-መ	ጽሕፈት	92-93	3	
		መልመጃ አራት	ጽሕፈት	94	6	
14	ትምህርት አስራ አራት	መልመጃ አንድ	ሰዋሰው	95	21	
		መልመጃ ሁለት	ጽሕፈት	96-97	8	
		መልመጃ ሦስት	ንባብ	98	8	
		መልመጃ አራት	ንባብ	99	8	
		መልመጃ አምስት	ንባብ	99	8	
		መልመጃ ስድስት	ሰዋሰው	100	1	
		መልመጃ ሰባት	ሰዋሰው	100	12	
		መልመጃ ስምንት	ሰዋሰው	101	10	
		መልመጃ ዘጠኝ	ሰዋሰው	101	5	
		መልመጃ አስር	ሰዋሰው	102	3	
		መልመጃ አስራ አንድ	ሰዋሰው	103	4	
		መልመጃ አስራ ሁለት	ሰዋሰው	103-104	-4	
15	ትምህርት አስራ አምስት	መልመጃ አንድ 1-5	ሰዋሰው	105	5	
		መልመጃ ሁለት	ሰዋሰው	106-107	10	
		መልመጃ ሦስት	ሰዋሰው	108-109	10	
16	ትምህርት አስራ ስድስት	መልመጃ አንድ	ንግግር	111	1	ሰላምታ
		መልመጃ ሁለት	ንግግር	111-112	2	
17	ትምህርት አስራ ሰባት	መልመጃ አንድ ሀ-ሠ	ንባብ	113	5	
		መልመጃ ሁለት ሀ-ሠ	ንባብ	113	5	
		መልመጃ ሦስት 3	ንባብ	114	1	
		ሀ	ሰዋሰው	114	5	
		ለ-1-5	ንባብ	114	5	
		ሐ-1-5	ንባብ	114	5	
		መ	ጽሕፈት	115	1	
		መልመጃ አራት	ንባብ	115	1	
		የተለያዩ ምንባቦች	ንባብ	116-126	8	
18	ትምህርት አስራ ስምንት	መልመጃ አንድ ሀ-ሠ	ንባብ	127	5	
		መልመጃ ሁለት 1-5	ንባብ	128	5	
		መልመጃ ሦስት	ሰዋሰው	129	2	
		መልመጃ አራት ሀ	ንባብ	129	7	
		ለ	ንባብ	129	5	
		ሐ-12	ንባብ	130	2	
		መልመጃ አምስት ሀ	ንባብ	131-132	1	
		ለ	ሰዋሰው	132	1	
19	ትምህርት አስራ ዘጠኝ	መልመጃ አንድ ሀ	ሰዋሰው	133	8	
		ለ	ሰዋሰው	134	4	
		ሐ	ሰዋሰው	134-135	5	
		መልመጃ ሁለት ሀ	ሰዋሰው	135	9	
		ለ	ሰዋሰው	136	4	
		ሐ	ንባብ	136	1	
		መ	ንባብ	137	1	
		መልመጃ ሦስት ሀ 1-7	ጹሕፈት	141-142	7	
		ለ 1-10	ሰዋሰው	142	10	
		ሐ 1-10	ሰዋሰው	143	10	
		መ 1-8	ሰዋሰው	143-144	10	
		ሠ 1-8	ሰዋሰው	144-1445	8	
		ረ 1-5	ሰዋሰው	145	5	
		ሰ	ንባብ	145	1	
		ሸ 1-8	ሰዋሰው	146	8	

20	ትምህርት ሃያ አንድ	መልመጃ አንድ 1.1-10 2.1-11 3.1-6	ሰዋሰው ሰዋሰው ሰዋሰው	147-148 148-149 150-151	10 11 6	
21	ትምህርት ሃያ ሁለት	መልመጃ ሀ 1-5 ለ ሐ መ 1-10 ሠ	ጽሕፈት ጽሕፈት ሰዋሰው ጽሕፈት ጽሕፈት	152 152 152-153 153 154	5 5 5 10 1	
	ወበራ /ጅጌ ደቦ/	መልመጃ አንድ ሀ-ለ መልመጃ ሁለት ሐ1-3 መልመጃ ሦስት መልመጃ አራት ሀ-ሐ መልመጃ አምስት መልመጃ ስድስት ሀ-ለ መልመጃ ሰባት ሀ- 1-4 መልመጃ ስምንት ሀ-ለ መልመጃ ዘጠኝ 1-4 መልመጃ አስር	ንባብ ንባብ ንግግር ንባብ ሰዋሰው ሰወሰው ጽሕፈት ንግግር ንባብ ንግግር	155-156 156-157 157 158-159 160 160 163 163 167 167	5 3 1 11 1 12 4 2 3 1	በግል ንግግር ማድረግ በሚና ጨዋታ
22	ትምህርት ሃያ ሦስት	መልመጃ አንድ ሀ-ለ ሐ መ መልመጃ ሁለት ሀ-ለ	ንግግር ጽሕፈት ጽሕፈት ንግግር ንግግር ጽሕፈት	168 168 169 169-170 170 170	2 11 4 7 4 4	የጊዜ ቅደም ተከተል - ሥዕሎችን ማየትና መናገር
		መልመጃ አንድ መልመጃ ሁለት	ንባብ ንባብ	172 174	4 6	
23	ትምህርት ሃያ አራት	መልመጃ አንድ 1-3 4-5 መልመጃ ሁለት እና 3 1 እና 2	ጽሕፈት ንግግር ንግግር ጽሕፈት	175 175 176 176	3 2 4 5	
24	ትምህርት ሃያ አምስት	መልመጃ አንድ መልመጀ ሁለት መልመጃ ሦስት መልመጀ አራት ሀ-ለ	ንባብ ንባብ ሰዋሰው ጽሕፈት	181 182 183 183	5 7 5 2	
25	ተረቶች እና እንቆቅልሾች	መልመጃ አንድ 1 2 3- ሀ-ሠ	ንግግር ማዳመጥ ንግግር ንባብ	191 191- 1911-192	1 1 5	ሥዕላዊ መግለጫዎች አዳምጦ መናገር
	ጭውውት	መልመጃ አንድ 4 መልመጃ ሁለት ሀ-ሐ መ- ሠ- 1 እና 4 2	ማዳመጥ ንግግር ንባብ ሰዋሰው ንግግር ማዳመጥ	192 192 196-197 197 198 198	1 1 13 4 3 1	ተረቶች ጭውውቶች

አባሪ ሁለት

«ለ»

በደረጃ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት ይዘቶች (ክፍሎች) መለማመጃ ጥያቄዎች መግለጫ

ተ.ቁ	ርዕስ	መልመጃዎች	ትምህርት	ገጽ	የጥያቄ ብዛት	ምርመራ
1	ትምህርት አንድ ያዳመጡትን መግለጽ	ሆሄያትንና ቃሉትን መለየት መልመጃ አንድ ሀ-ለ መልመጃ ሁለት ሀ-ለ	ማዳመጥ ማዳመጥ ማዳመጥ	1 1-2 2-3	14 19 14	
	ዝሆንና ድርጭት	መልመጃ ሀ---------- ሀ---------- ለ---------- ሐ----------	ማዳመጥ ንግግር ንባብ ንግግር	6 6 6 6	1 1 6 1	ተረት ተረት መተረት
	ሉባባ	መልመጀ አንድ 1-8 መልመጃ ሁለት	ማዳመጥ ንግግር ማዳመጥ ንግግር	8 8 8 8	8 8 1 1	ያዳመጡትን መናገር ተረት
2	ትምህርት ሁለት ንግግር ማድረግ	መልመጃ አንድ ሀ-ሐ	ንግግር	10-11	15	ማብራሪያ መስጠት
3	ትምህርት ሶስት የሆሄያትን ቅርጽ መለየት	መልመጃ አንድ ሀ-ሠ መልመጃ ሁለት 1-4	ንባብ ሰዋስው	12-13 13-14	26 40	
4	ትምህርት አራት የሆሄያት አቀራረጽና መሰመር አጠባበቅ	መልመጃ አንድ ሀ-ሐ መልመጃ አንድ ሀ-ሐ	ጽሕፈት ጽሕፈት	15 15-16	2 12	
5	ትምህርት አምስት የአማርኛ ቁጥሮች/አሀዞች	መልመጃ ሀ-ለ	ጽሕፈት	17	2	
	ትምህርት ስድስት ቃሉትን መመስረት	መልመጃ አንድ ሀ-ሸ	ሰዋስው	19-20	20	
7	ትምህርት ሰባት ቃላትን አጠብቆና አላልቶ ማንበብ	መልመጃ አንድ 1-ሀ 1-ለ 2-ሀ 2-ለ 3-	ንባብ ንግግር ጽሕፈት ንግግር ሰዋስው	24 24 24 24 24-25	1 1 1 1 12	ተረት ተረት
8	ትምህርት ስምንት ድምፅን ከፍ አድርጎ ማንበብ	መልመጃ አንድ ሀ ለ-- መልመጃ ሁለት 1-2 መልመጃ ሶስት ሀ-መ መልመጃ አራት 1-2 መልመጃ አምስት 1-2	ንባብ ንግግር ንባብ ንግግር ንባብ ጽሕፈት	26 26 27 28 28-19 29	2 1 15 4 19 2	ያነበቡት የመግለፅ የራስን ሀሳብ መግለጽ
9	ትምህርት ዘጠኝ አያያዝ ቃላት	መልመጃ አንድ ሀ መልመጃ ሁለት 1 መልመጃ ሶስት	ንባብ ሰዋስው ጽሕፈት	30 31 32	5 6 4	
10	ትምህርት አስር ሥርዓተ ነጥብ	መልመጃ አንድ መልመጃ ሁለት ሀ-ረ	ንባብ ጽሕፈት	34 34-35	5 16	
11	ትምህርት አስራ አንድ ገላጮች መለየት	መልመጃ አንድ 1-4	ሰዋስው	37-38	25	
12	ትምህርት አስራ ሁለት ዐረፍተ ነገር መጻፍ	መልመጃ አንድ መልመጃ ሁለት መልመጃ ሶስት	ሰዋስው ሰዋስው ሰዋስው	40-42 40-42 42	1 15 5	
13	ትምህርት አስራ ሶስት ጭውውት	መልመጃ አንድ ሀ-ለ መልመጃ ሁለት መልመጃ ሶስት	ንባብ ንግግር ጽሕፈት	44-45 45 46	10 3 4	ጭውውት
14	ትምህርት አራት	መልመጃ አንድ ሀ-ለ	ንባብ	48	10	

	ውይይት	ሐ መልመጃ ሁለት ሀ-ለ ሐ መልመጃ ሶስት	ሰዋስው ንግግር ጽሕፈት ንግግር	49 49 49 49	6 2 1 4	
15	ትምህርት አስራ አምስት ውጥን ታሪክ መጨረስ	መልመጃ አንድ መልመጃ ሁለት መልመጃ ሶስት 1 -2	ንባብ ጽሕፈት ጽሕፈት ንባብ	50-51 51 52 52	4 5 1 1	
16	ትምህርት አስራ ስድስት	መልመጃ አንድ መልመጃ ሁለት ሀ-ለ መልመጃ ሶስት	ንባብ ሰዋስው	54 54 56	5 19 3	
17	ትምህርት አስራ ሰባት ንባብን ከአላማ ጋር ማስተካከል ዓይናችን ካርታ አመካኝተው በሏት ስት	መልመጃ አንድ መልመጃ ሁለት	ንባብ ጽሕፈት	59 59-60	10 11	
		መልመጃ አንድ ሀ-ለ መልመጃ ሁለት 1-3	ንባብ ሰዋስው	61 61-62	10 26	
		መልመጃ አንድ መልመጃ ሁለት	ንባብ ንባብ	63-64 64-65	5 21	
		መልመጃ አንድ ሀ-ለ መልመጃ ሁለት ሀ-ለ	ንባብ ሰዋስው	67-68 68	10 20	
		መልመጃ አንድ ሀ-ለ መልመጃ ሁለት ሀ-ለ መልመጃ ሶስት ሀ-ለ	ንባብ ሰዋስው ንግግር	70 70-71 71	10 10 6	
18	ትምህርት አስራ ስምንት ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ትርጉም መስጠት	መልመጃ አንድ ሀ-ሐ መልመጃ ሁለት 1-2	ሰዋስው ሰዋስው	72-73 73-74	21 19	
19	ትምህርት አስራ ዘጠኝ ክርክር	መልመጃ አንድ ሀ-ለ መልመጃ ሁለት	ንባብ ንግግር	77 78	11 7	
20	ትምህርት ሃያ ከልዩ ልዩ መግለጫዎች የመረጃ ሀሳብ ማግኘት	መልመጃ አንድ ሀ ለ-1 እና 3 2 ሐ-1 2 መልመጃ ሁለት ሀ ለ መልመጃ ሶስት	ንባብ ንግግር ጽሕፈት ጽሕፈት ንግግር ንግግር ጽሕፈት ንባብ	79-80 80 80 81 81-82 82-83 83 83-84	4 2 1 1 4 5 2 6	ስዕልን፣አይቶ መናገር አጭር መልስ
21	ትምህርት ሃያ አንድ የመረጃ ምንጮች ሁለት መንገደኞች	መልመጃ አንድ መልመጃ ሁለት 1-5 6	ሰዋስው ንባብ ንግግር	85 86 86	5 5 1	ማብራሪያ መስጠት
		መልመጃ አንድ ሀ-ሐ	ንባብ	90-91	16	
22	ትምህርት ሃያ ሁለት ማስታወሻ መያዝ	መልመጃ አንድ -1 2 ሀ እናመ ለ-ሐ	ንባብ ጽሕፈት ንግግር	93 93 93	5 2 2	መናገር
23	ትምህርት ሃያ ሶስት ያዳመጡትን በራስ አባባለ ማቅረብ አይጥና ድመት ጎሩይ ወልደስላሴ የልጆች ጨዋታ	መልመጃ ሀ-ለ	ንግግር	96	2	ያለበትን መግለፅ
		መልመጃ ሀ-ሐ	ንግግር	98	7	
		መልመጃ	ንግግር	99	1	የቡድን ጨዋታ
24	ትምህርት ሃያ አራት ተጠየቃዊ አስተሳሰብ አንበሳና ቀበሮ	መልመጃ አንድ 1፣ 2ሀ፣3 2ሐ፣ 3ሀ-ሰ 2ለ----	ጽሕፈት ንግግር	100- 103 1003	14 1	ቅደም ተከተልን መግለፅ
		መልመጃ ሀ-ሐ መልመጃ ሀ፣ ሐ፣መ	ጽሕፈት ንግግር	103 104-	3 11	ነው አይደለም እያሉ

	ይመርና አማረ	ሐ---- ሠ---- 1-2 1-2	ጽሕፈት ማዳመጥ ንግግር ጽሕፈት	105 105 105- 106 106 107	1 15 11 2	መደምደም ነው እያሉ መደምደም
	ሁለት በጎችና ሁለት እየሎች	መልመጃ ሀ- ለ-መ ሐ	ንግግር ጽሕፈት ሰዋሰው	108 108 108	1 2 1	ምደባ ማድረግ
		መልመጃ ሀ ለ-ሠ	ንባብ ንግግር	111- 112 112- 114	13 20	በአጭሩ መናገር
